አዲስ ዘመን
ኢፕድ
ሐሙስ
81ኛ ዓመት ቁጥር 349 ነሐሴ 19 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# አሸባሪው ሕወሓት የሰላም አማራጭን አሻፈረኝ ብሎ ውጊያ መክፈቱን መንግሥት አስታወቀ

## - ቡድኑ ተኩስ ማቆሙን በይፋ አፍርሷል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ከመንግሥት በኩል የቀረቡለትን በርካታ የሰላም አማራጮች ወደ ጎን በመተው ተኩስ መክፈቱን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ትናንት ባወጣው መግለጫ፤ መንግሥት ተገዶ የገባበትን የሰሜኑን ጦርነት በሰላም ለመቋጨት ያስችላሉ ያላቸውን እርምጃዎች ሲወስድ ቢቆይም አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ከመንግሥት በኩል የቀረቡለትን በርካታ የሰላም አማራጮች ወደ ጎን በመተው ትናንት ንጋት ላይ ተኩስ ከፍቷል።

በዚህም የሽብር ቡድኑ ሕወሓት ከወረራቸው የአማራና የአፋር አብዛኞቹ አካባቢዎች ተገፍቶ እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ መንግሥት፤ ሙሉ የሠራዊትና ሎጂስቲክስ አቅም እያለው ወደ ትግራይ ክልል ከመግባት መቆጠቡን ጠቁሟል።

እንደዚሁም የተሳለጠና ያልተቋረጠ የሰብአዊ ድጋፍ ወደ ትግራይ ክልል እንዲገባ የተናጠል ተኩስ አቁም ማድረጉና ምቹ ሁኔታን መፍጠሩ፣ ለሰላም በር ይከፍታል በሚል እስረኞችን መፍታቱ እንዲሁም የሰላም አማራጭንም አሟጦ ለመጠቀም እንዲቻል የሰላም አማራጭ አብይ ኮሚቴን በይፋ ወደ ስራ አስገብቶ ግልጽ አቅጣጫንም ማስቀመጡን መግለጫው አስታውሶ፤ ሆኖም አሸባሪው ቡድን ከውጭ ደጋፊዎቹ ጋር በመሆን ጦርነቱን የመቀጠል ከፍተኛ ፍላጎትን ሲያንጸባርቅ ቆይቷል ነው ያለው፡፡

አሸባሪው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

# የኢትዮጵያን የአየር ክልል ጥሶ ለሽብር ቡድኑ የጦር መሳሪያ ሲያቀብል የነበረ አውሮፕላን በጀግናው አየር ኃይል ተመትቶ ወድቋል


ሜጀር ጀኔራል ተስፋዬ አያሌው

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን መዳከም የሚፈልጉና ለዚሁም ለዘመናት የሚንቀሳቀሱ ሕወሓትን በመደገፍ ላይ የሚገኙ ታሪካዊ ጠላቶች ንብረት እንደሆነ የሚታመን አውሮፕላን ለሽብር ቡድኑ የጦር መሳሪያ ጭኖ በሱዳን አልፎ የአየር ክልላችንን ጥሶ ሲገባ በጀግናው አየር ኃይል ተመትቶ ወድቋል። ሠራዊቱ የሀገሩን ሉዓላዊነት ለማስከበር ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ዝግጁ መሆኑም ተገልጿል።

በሀገር መከላከያ ሠራዊት የመከላከያ ህብረት ዘመቻ ዋና መምሪያ የመከላከያ ኃይል ስምሪት ኃላፊ ሜጀር ጀኔራል ተስፋዬ አያሌው እንደገለጹት፤ በሱዳን አድርጎ የኢትዮጵያን አየር ክልል ጥሶ በሁመራ ሰሜናዊ ክፍል በኩል ወደ ትግራይ ሊያልፍና ለሽብር ቡድኑ የጦር መሳሪያ ሊያቀበል የነበረ አውሮፕላን በጀግናው አየር ኃይል ትናንት ሌሊት አራት ሰዓት ላይ ተመትቶ ወድቋል።

ላለፉት በርካታ ወራት ከፍተኛ ወታደራዊ ዝግጅት ሲያደርግ የቆየው አሸባሪው ሕወሓት ካለፉት ሁለት


ለሽብር ቡድኑ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር
ደርባ ሲሚንቶ DERBA CEMENT



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ



Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት


ፎቶ - ዳኜ አበራ

# ‹‹ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር ኃላፊነት የሚሰማውና ተጽእኖ ፈጣሪ ሚዲያ መገንባት አስፈላጊ ነው››

-ፕሮፌሰር ብሩክ ኃይሉ
የጋዜጠኝነት መምህር

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበርና አገርን ለማሳደግ ኃላፊነት የሚሰማው ጤነኛና ተጽእኖ ፈጣሪ ሚዲያ መገንባት አስፈላጊ መሆኑን የጋዜጠኝነት መምህሩ ፕሮፌሰር ብሩክ ኃይሉ ገለጹ፡፡

ፕሮፌሰር ብሩክ ኃይሉ ዘጠነኛው የኢፕድ ስለኢትዮጵያ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይና ‹‹ሚዲያ ስለኢትዮጵያ›› በሚል ርዕሰ ጉዳይ ባለፈው ሳምንት በጎንደር ከተማ የፓናል ውይይት በተካሄደበት ወቅት ‹‹ሚዲያና ብሔራዊ ጥቅም›› የሚል የውይይት መነሻ ጹሁፍ ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ ሚዲያና ብሔራዊ

‹‹ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር
ከ3 ቁጥር
-15 ቁጥር




0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

## መንግሥት ለሠላም እያደረገ ያለው ጥረት በሕወሓት ቡድን እየተደናቀፈ መሆኑ ተገለጸ

ገጽ 4



አቶ ናሆም ስንታየሁ

# የልብ ሕሙማን ማዕከሉ በሕክምና ግብዓቶች ዕጥረትበሙሉ አቅሙ አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑን አስታወቀ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ለልብ ሕክምና የሚያስፈልጉ የሕክምና ግብዓቶች ዕጥረት በሙሉ አቅሙ አገልግሎት መስጠት እንዳልቻለ የኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማዕከል አስታወቀ። ማዕከሉ በአሁኑ ጊዜ በአንድ ሦስተኛ አቅሙ ብቻ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ገልጿል።

የኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማዕከል የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ኃላፊ አቶ ናሆም ስንታየሁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ማዕከሉ የተሟላ ሙያተኛ ቢኖረውም ለልብ ሕክምና በሚያስፈልጉ የሕክምና ዕቃዎች ዕጥረት የተነሳ የተሟላ አገልግሎት እየሰጠ አይደለም።

ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑት ለልብ ሕክምና አገልግሎት የሚያስፈልጉ የሕክምና ግብዓቶች ከውጭ የሚገቡ መሆናቸውን የጠቆሙ አቶ ናሆም፤ ማዕከሉ ቋሚ ገቢ ስለሌለው የሕክምና ግብዓቶቹን በሚፈለገው ልክ የማስገባት አቅም እንደሌለው ገልጸዋል።

በግብአት ዕጥረት የተነሳ ማዕከሉ በዓመት ለ500 ሕጻናት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ያመለከቱት አቶ ናሆም፤ በዚህ ዓመት አገልግሎቱን ለ750 ሕጻናት ለመስጠት አቅዶ የነበረ ቢሆንም ይገኛሉ ተብለው የታሰቡ እገዛዎች ባለመገኘታው ዕቅዱ ሊሳካ አልቻለም ብለዋል።

ማዕከሉ እስካሁንም በአገር ውስጥና በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ከመንግሥት መስሪያ ቤቶችና ከተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚያገኘው እርዳታ የሚተዳደር በመሆኑ የፋይናንስ አቅም ውስንነት እንዳለበት ተናግረዋል።

ማዕከሉ በቋሚነት ገቢ የሚያገኝበት መንገድ ባይፈጠርም ከመንግሥት በኩል በተለይም ከጤና ሚኒስቴር በርካታ ድጋፎችን እያገኘ መሆኑን ገልጸዋው፤ በቅርቡም ከኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ከጤና ሚኒስቴርና ከሮተሪ ጋር የአራትዮሽ የትብብር ስምምነት ተፈራርሟል። በዚህ ስምምነትም መሰረትም አንድ መቶ የሚሆኑ ሕጻናት ወደ ውጭ አገር ሄደው ሕክምና እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል።

በየቀኑ ከአስር እስከ አስራ ሁለት የሚሆኑ ሕጻናት ከሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ‹‹በሪፈር›› ወደ ማዕከሉ ይመጣሉ ያሉት ኃላፊው፤ አሁን ላይ ሰባት ሺህ 200 ሕጻናት ለሕክምናው ወረፋ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ። በየሳምንቱ ለሦስት ሕጻናት ሙሉ የልብ ቀዶ ጥገና ሕክምና እንዲሁም ለስድስት ሕጻናት በደም ስር የሚሰጥ ‹‹ፕሮሲጀር›› ሕክምና በአጠቃላይ በሳምንት ለዘጠኝ ሕጻናት ነፃ የህክምና አገልግሎት እንደሚሰጥ አስታውቀዋል።

ተቋሙ በተሻለ አቅም አገልግሎት እንዲሰጥ ማንኛውን ተቋምና የሕብረተሰብ ክፍል ድጋፍ እንዲያደርግ አቶ ናሆም ጥሪ አቅርበዋል።

የሕክምና ማዕከሉ የጀመረው ኢትዮጵያውያን ከአንድ ብር ጀምሮ በሚያደርጉት ድጋፍ ስለሆነ አሁንም በቀጣይነትም በተሻለ ደረጃ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማስቻል ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማዕከል ከስድስት ሺህ 500 በላይ ሕጻናት የልብ ሕክምና አገልግሎት በነጻ እንዲያገኙ ማድረጉ ተገልጿል።

# “ነጻ የንግድ ቀጠናው ለቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል”

**- አቶ ዋሲሁን በላይ**

**የምጣኔ ሀብት ባለሙያ**

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ነጻ የንግድ ቀጠና መጀመሯ ለቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ሲሉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዋሲሁን በላይ አስታወቁ። የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጠና ለጅቡቲ ወደብ ቅርብ መሆኑ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው የጎላ እንደሆነም ጠቁመዋል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዋሲሁን በላይ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ የጀመረችው ነጻ የንግድ ቀጠና ምርት በብዛት ለማምረትና ከውጭ ለማስመጣት አበረታች ተግባር ነው። የውጭ አምራቾች ነጻ እድሉን ለመጠቀም መዋዕለ ነዋያቸውን በአገሪቱ ለማዋል ያስችላቸዋል። ይህም ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንትን የሚያሳድግ ነው።

እንደ ባለሙያው ገለጻ፤ ነጻ የንግድ ቀጠናዎች የሚቋቋሙት መደበኛ የማምረት፤ ወደ ውጭ ሀገር የመላክና ከውጭ የማስገባት ስራዎችን ከተለመደው ክልከላና የአገልግሎት ክፍያ ነጻ ስለሚያደርግ ነው። ነጻ የንግድ ቀጠና ተብለው በተቋቋሙ ኢንዱስትሪ መንደሮች የሚገቡ አምራቾች፤ አስመጪዎችና ላኪዎች ከቀረጥ ነጻ የመሆን፤ የተለመዱ ረጃጅም ጉዳዮችን የማስፈጸም ሂደቶችን የማሳጠር፤ የብድር አቅርቦት፤ የተሻለ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት፤ የትራንስፖርት አገልግሎትና መሰል ማበረታቻዎች ይደረግላቸዋል። ከዚህ አኳያ የተጀመረው ነጻ የንግድ ቀጠና ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንትን ያሳድጋል።

የዓለም የንግድ ሥርዓት የሚከናወነው በተለመደው የገቢና ወጪ አሰራር መርህ ነው ያሉት አቶ ዋሲሁን፤ አንድ አገር የውጭ ንግድ ሲያከናውን በሂደቱ ውስጥ የመንግሥት ጥቅሞች እንዳሉ ጠቁመዋል። ይህም በገቢ፣ በውጭ ምንዛሬ፣ በሥራ እድልና የምርት አቅርቦት ረገድ ጠቀሜታ እንዳለውና የአቅርቦትና የፍላጎትን ጉዳይ ለማስተካከል እድል እንደሚሰጥ ጠቅሰዋል። ስለዚህ አብዛኛው የንግድ ሥርዓት የሚመራው በዚህ ሂደት ነው ሲሉም ገልጸዋል።

ነጻ የንግድ ቀጠና ቦታዎች ለአየር መንገድ፤ ለወደብ፤ ለባቡር መንገድ እና ለድንበር አቅራቢያ እንዲሆኑ ተደርገው ይቋቋማሉ ያሉት አቶ ዋሲሁን፤ የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጠና መቋቋም ከዚህ አንጻር ሲሆን እንደሚችልም ጠቅሰዋል። ኤክስፖርት የሚደረጉ ምርቶች ከወደብ ያላቸው ርቀት አጭር ነው በማለት፤ ከአዲስ አበባ ጂቡቲ ከማድረስ ከድሬዳዋ ጅቡቲ ማድረስ ቀላል እንደሆነም ነው ያነሱት። የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጠና መቋቋሙ ለኢኮኖሚው ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው አስታውቀዋል።

አቶ ዋሲሁን፤ በወጪ ንግድ ሥርዓት በመላክና በመቀበል ውስጥ መንግሥት ከፍተኛ ገቢ እንደሚያገኝ፤ የማዕከላዊ ገበያውንም ሁኔታ የሚያረጋጋበት ሂደት እንዳለ ጠቅሰዋል። ነጻ የንግድ ቀጠና ውስጥ ያሉ ጉዳዮች ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትንም ያሳድጋል ነው ያሉት። ከዚህ በተጨማሪ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ምርትን ለውጭ ገበያ ለማቅረብም ጥሩ እድል እንደሚያገኙና ከፍተኛ የማምረት አቅም እንዲኖራቸውም ጅምሩ መልካም



ፎቶ - ከፉ ደበ

አጋጣሚ እንደሆነ አመላክተዋል። ሂደቱ የአሰራር ሁኔታን እንደሚያዘምን፣ የመንግሥትን ገቢ የማሳደግ እድሉ ከፍተኛ እንደሆነ፣ መንግሥት ለሸመታ የሚያወጣውን የውጭ ምንዛሬ እንደሚቀንስለት ተናግረዋል።

አንድ ነጻ ንግድ ቀጠና ብቻውን ትልቅ ተጽእኖ አይፈጥርም ያሉት ባለሙያው፤ የድሬዳዋ የነጻ ንግድ ቀጠና ለኢኮኖሚው መሠረታዊ ባይባልም አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለውም አመላክተዋል። የመጀመሪያው እንደመሆኑ ብዙ ልምድ ተወስዶበት ማስፋፋት እንደሚገባም መክረዋል።



አቶ አላምረው ይረዳው



አቶ ማሙሸት አማረ



አቶ መልካሙ ሹምዬ

# አሸባሪው ሕወሓት የሰላም አማራጭን በመሸሽ ዳግም ጦርነት በማወጁ ሕዝቡና ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ በጽኑ ሊያወግዙት ይገባል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት የመንግሥትን የሰላም አማራጭ በመሸሽ ዳግም ጦርነት በማወጁ አጠቃላይ ሕዝቡና ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ በጽኑ ሊያወግዙት እንደሚገባ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ተናገሩ።

የሽብር ቡድኑ ዳግም ጦርነት መጀመሩን በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ትናንት ባወጣው መግለጫም ይፋ አድርጓል።

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን)፣ የአገው ብሔራዊ ሸንጎ እና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ፓርቲ አመራሮች በወቅታዊ ጉዳይ ዙሪያ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

የፓርቲዎቹ አመራሮች በሰሜን ኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት መንግሥት የጀመረውን የሰላም አማራጭ በመተው አሸባሪው ሕወሓት ሰላም እንደማይፈልግ አረጋግጧል ነው ያሉት።

አሸባሪ ቡድኑ በተለይም የትግራይ ክልል ወጣቶችና አጠቃላይ ሕዝቡን ለማያባራ እልቂትና የከፋ ችግር በመዳረግ የራሱን ህልውና ለማስቀጠል እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

በሰላማዊ መንገድ ተወያይቶ ሰላም ማምጣትና ለሕዝብ ማሰብ የሕወሓት ባህሪ አለመሆኑን የሚጠቅሱት ፖለቲከኞቹ ድብቅ ሴራ እና የጦርነት አማራጭ የሚከተለው መርህ መሆኑን አስረድተዋል።

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) ምክትል ሊቀ-መንበር መልካሙ ሹምዬ፤ አሸባሪው ቡድን ካለው የቆየ ባህሪ አንጻር ቀድሞውንም ቢሆን ለሰላማዊ ውይይት ደንታ የማይሰጥ መሆኑን ይናገራሉ።

በተለያዩ አጋጣሚዎች ሰላም ወዳድ በመምሰል የሚያሰራጨው መረጃ ዓለም አቀፉን ማሕበረሰብ ለማሳሳት የሚጠቀምበት ስልቱ ስለመሆኑ አንስተዋል።

አሁን ላይ የመንግሥትን የሰላም አማራጭ ባለመቀበል ጦርነት መክፈቱ ለሰላም ቦታ የማይሰጥ መሆኑን ማረጋገጫ ነው ብለዋል።

የአገው ብሔራዊ ሸንጎ ሊቀ-መንበር አቶ አላምረው ይርዳው፤ ሕወሓት ከአመሰራረቱ ጀምሮ እስከአሁን የትግራይን ሕዝብ ለችግር እየዳረገ ያለ ቡድን መሆኑን ተናግረዋል።

ከግትር አቋሙ የተነሳ በተለይም የክልሉን ወጣቶች በአስገዳጅ ወደ ጦርነት በመማገድ ለሞት፣ ለችግርና ስቃይ እየዳረገ መሆኑን ገልጸዋል። የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ፕሬዚዳንት ማሙሸት አማረ በበኩላቸው አሸባሪው ሕወሓት በተለምዶው ድርድር፣ ንግግር እና ውይይት የማይመርጥ የጥፋት ስብስብ ስለመሆኑ ይናገራሉ።

በመሆኑም በተለይም በግድ ተጭኖባቸው ያሉ የትግራይ ሕዝብ የዚህን ቡድን እኩይ አስተሳሰብ ሊታገሉት ይገባል ነው ያሉት።

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) ምክትል ሊቀ-መንበር መልካሙ ሹምዬ፤ የትግራይ ሕዝብ የሰላም አማራጭን ባለመቀበል ለሌላ ጦርነት እየተዘጋጀ ያለውን ቡድን ከራሱ ላይ አሽንቀንጥሮ መጣል አለበት ብለዋል፡፡

እንደ ለኢዜአ ዘገባ፤ ቡድኑ እያደረገ ላለው የጦርነት ዝግጅት ሕዝቡ በአንድ ድምጽ ሊያወግዘውና ሊቃወመው እንደሚገባ ገልጸዋል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በትናትናው እለት ባወጣው መግለጫ አሸባሪው ሕወሓት የመንግሥትን የሰላም አማራጭ ወደጎን በመተው ሰሞኑን ሲፈጽም የሰነበተውን ትንኮሳ ገፍቶበት ትናንት ንጋት ላይ በምስራቅ ግንባር በቢሶበር፣ በዞብል እና በተኩለሽ አቅጣጫዎች ከለሊቱ 11 ሰአት ጀምሮ ጥቃት መፈጸሙን አስታውቋል።

በመሆኑም አሸባሪ ቡድኑ በይፋ ጦርነት በመክፈት የተኩስ ማቆሙን በይፋ ማፍረሱን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገልጿል።

# ‹‹ጫና በበረታበት ወቅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውጤት ማስመዝገቡ የአመራሩን ችግር የመሸከም አቅም ያሳያል››

- ዶክተር ዱጋሳ ሙሉጌታ
በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ጫና በበረታበት ወቅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ መቻሉ የአመራሩ ችግርን የመሸከም አቅምና ቁርጠኝነት እንደሚያሳይ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ፣ መምህርና ተመራማሪ ዶክተር ዱጋሳ ሙሉጌታ ገለጹ።

ዶክተር ዱጋሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ጫና በበረታበት ወቅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተሻለ ውጤት ማስመዝገቡ ችግርን መሸከም የሚችልና ቁርጠኛ አመራር ካለ መሻገር እንደሚቻል ማሳያ ነው።

"ኢትዮጵያ ትበታተናለች፣ ቶሎ አገር ለቅቃችሁ ውጡ"፤ በተባለበት ማግስት ጠንካራ አመራር በመስጠትና ተከታዮችን በማፍራት በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን ማስፋት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ከውድቀት በመማር መነሳት መቻሉ ተፈጥሯዊ ነው፣ በሁሉም ዘርፎች ባይሳካም እንኳን መጥፎ መንገድ ላይ አለመሆናችንን ያሳያል። በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን ማስፋት፣ መልካም ተሞክሮዎችን ማስቀጠል እና ኮሚቴው በግምገማው የለያቸውን ክፍተቶችም ፈጥኖ ማረም አስፈላጊ ነው።

የማክሮ ኢኮኖሚ ቡድን ጥሩ ተመልክቶ ነው የገመገመው፤ ድሮ ከነበረው አንድ በመቶም ሆነ አምስት በመቶ ለውጥ መጣ ከተባለ ዕድገት መኖሩን ያሳያል፣ ልዩነት ቢኖርም የኢትዮጵያ መንግሥት የገለጸውን ዕድገት የዓለም ባንክም አረጋግጧል ብለዋል።

ይህ የሚያሳየው ዕድገት መኖሩን ነው። ምናልባት የተጋነነ ካለም መረጃውን ማጥራት ይቻላል። በወጪ ንግድ፣ በሬሚታንስ፣ በመስኖ ስንዴ ምርት፣ በችግኝ ተከላ የተገኙ ስኬቶችን በውጤታማነት ማስቀጠል እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል።

ትግበራውን ወደሕዝብ ማውረድ፣ ሕግና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን መገምገም እንደሚገባም ጠቅሰዋል። ለመፍትሄ ሁሉም ሃሳብ እንዲያዋጣ ዕድል መፍጠር እንደሚገባም ተናግረዋል።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ የትምህርት ፖሊሲውን አገር በቀል በሆነ ቅኝት ከልሶ በሥነ ምግባር የታነጸ ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስተርጓሚና ሕግ አስፈጻሚ ትውልድ ለማፍራት በትኩረት መስራት ይገባል።

ግምገማው በተጨባጭ በተሰጣቸው ልክ በውጤታማነት የሰሩትን ለመመልከት እና ውጤቱን መሰረት በማድረግ ለማበረታታ ያስችላል። መቻቻል፣ በእውቀት መንፈስ በመተጋገዝ የሚተገበር ከሆነ አገር በቀል እውቀት ያድጋል፤ የማክሮ ኢኮኖሚውም ለውጥ ያሳያል ብለዋል። በሚገባው ልክ ያልተሰራውን ጉድለቱን ለማሻሻል እንደሚያግዝም አመልክተዋል።

የእንጦጦ መናፈሻ፣ የአንድነት እና የወዳጅነት ፓርኮች፣ ወንጪ፣ ጎርጎራ እና የኮይሻ ፕሮጀክቶች የቱሪስት መስህብ ሆነዋል። የህዳሴ ግድብም በኢኮኖሚ ለውጥ ማስገኘታቸውን አመልክተዋል።

በገበያ ኢኮኖሚ ዕድገት ሁሉንም ማሳካት አይቻልም። በግምገማ ማበረታታት፣ ያልተሳካውን የሚታረምበትን እቅጣጫ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

በአገር ውስጥ የበቀሉ፣ ያልታዩ፣ ስራ ላይ ያልዋሉትን ጥቅም እንዲሰጡ መንግሥት በሪፎርሙ ውስጥ አገር በቀል ኢኮኖሚ በሚል እንዲተገበር ማድረጉ ተገቢ ነው።


ፎቶ ፡- በአዩብ ተፈሪ

አውሮፓውያን የአስተዳደር ሥርዓትን ከገዳ ሥርዓት ተሞክሮ ወስደው የፕሬዚደንትን ምርጫ የጊዜ ቆይታን ወስነው ተግባራዊ ማድረጋቸውንም አስታውሰዋል። የአውሮፓ ሕብረትና መሰል የአንድነትና ሕብረት ስራቶች በአገር ውስጥ ደቦ፣ ጅጌና ወንፈል ተብሎ ሲሰራበት ቆይቷል። በቴክኖሎጂ በመደገፍ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ እንደሚገባም ነው ያመለከቱት።



# የደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር በግንባር ለሚገኙ የኢትዮጵያ ሠራዊቶች የስንቅ ድጋፍ አደረገ

አዲስ አበባ፡- የዞን አስተዳደሩ በስሩ የሚገኙ ወረዳዎችን በማስተባበር 34 ሙክት በግ እና ከ100 ኩንታል በላይ ደረቅ ሬሽን በጥቅሉ ከአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የስንቅ ድጋፍ አደረገ።

የስንቅ ድጋፉን የደቡብ ወሎ ዞን አስተዳዳሪ ዶክተር አብዱ ሁሴን ለሰሜን ወሎ ዞን አመራሮች ያስረከቡ ሲሆን ዋና አስተዳዳሪው በርክክቡ ወቅት የስንቅ ድጋፉ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር አብዱ ሁሴን ገለፃ ድጋፉ የተደረገበት ዋናው ምክንያት አሸባሪው፣ አውዳሚው እና ሰላም ጠሉ የትግራይ ወራሪ ሃይል ያለጦርነት እስትንፋስ ስለሌለው በመንግሥት የቀረበለትን የሰላም ጥሪ አሻፈረኝ ብሎ ሰሞኑን የጦርነት ጉሰማዎችን ሲደልቅ መቆየቱን በማውሳት ትናንት የተኩስ አቁም ስምምነቱን በመጣስ በይፋ ጦርነት ከፍቶብናል ብለዋል። ይሁን እንጂ አሸባሪው ቡድን የመጨረሻ የጥፋት ካርዱን የመዘዘ በመሆኑ በተባበረ ክንዳችን መትተን እንቀብረዋለን ሲሉም ነው የተናገሩት።

በባለፈው ወረራ በስፋት የተጎዱት የሰሜን ወሎ እና የደቡብ ወሎ አካባቢዎች መሆናቸውን ያስታወሱት ዋና አስተዳዳሪው የሽብር ቡድኑ ባለበት ተመትቶ እንዲወገድ ለማድረግ እርስበርስ መደጋገፍ በማስፈለጉ ይህን ድጋፍ ይዘን መጥተናል ሲሉ መግለጻቸውን ከአማራ ብልጽግና ፓርቲ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የድጋፍ ማሰባሰቡን ሂደት በአስተባባሪነት የመሩት የደቡብ ወሎ ዞን ሴቶችና ሕጻናት ማ/ጉዳይ መምሪያ ሃላፊ ወ/ሮ ቤተልሄም ብርሃኑ በበኩላቸው ድጋፉ አሁንም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የገለጹ ሲሆን በዚህ ስንቅ የማሰባሰብ ሂደት ውስጥ ሁሉም የደቡብ ወሎ አመራር መሳተፉን ነው የገለጹት።

# በአዲሱ በጀት ዓመት የአርብቶ አደሩን ኑሮ ለማሻሻል የሚያስችሉ 220 ፕሮጀክቶች ይገነባሉ

አዲስ አበባ፡- በአዲሱ በጀት ዓመት ድርቅን በዘላቂነት ለመቋቋምና የአርብቶ አደሩን ማሕበረሰብ ኑሮ ለማሻሻል የሚያስችሉ 220 ፕሮጀክቶችን በ5 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ለመገንባት እየሰራ መሆኑን የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር ገለጸ።

ሚኒስቴሩ ከተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ከተወከሉ የፕሮጀክቱ ስትሪም ኮሚቴ ጋር በእቅዱ የአፈፃፀም አቅጣጫ ላይ በአዳማ እየተወያየ ነው። በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የፕሮጀክቱ አስተባባሪ አቶ ሰይድ ይመር እንደገለጹት፤ በአርብቶ አደሩ አካባቢ የተከሰተውን ድርቅ ለመቋቋም በአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ 73 የውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ ተከናውኗል።

ከአንድ ሺህ 800 በላይ ሄክታር መሬት ላይ የለማን የእንስሳት መኖ በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች ተደራሽ መደረጉንም ተናግረዋል።

በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት የውሃ፣ የመንገድ፣ የእንስሳት ጤና ኬላዎችና የእንስሳት ገበያ ማዕከላት በአስቸኳይ የአደጋ ጊዜ ምላሽ በመገንባት ለአገልግሎት ማብቃት መቻሉን ጠቅሰዋል።

ፕሮጀክቱ በሰውና በእንስሳት ሊደርስ የነበረውን ጉዳት መቋቋም መቻሉን የገለጹት አቶ ሰይድ በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች የእንስሳት መድሃኒት በተሻለ ደረጃ ተደራሽ ማድረግ መቻሉን ጠቅሰዋል።

በተያዘው የበጀት ዓመት ድርቅን በዘላቂነት ለመቋቋም 120 የውሃ ግንባታን ጨምሮ 220 ፕሮጀክቶች እንደሚከናወኑ አስታውቀዋል።

በተለይ ለመስኖ የሚውል የውሃ ልማት፣ የመንገድ፣ የእንስሳት ጤና ተቋማት፣ የመኖ ልማትና ማከማቻ መጋዝኖች፣ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ የእንስሳት ግብይት ማዕከላት፣ የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያ ሰርቶ ማሳያ ማዕከላት ግንባታ እንደሚገኙበት አብራርተዋል።

ለፕሮጀክቶቹ ማስፈፀሚያ 5 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር መመደቡን ጠቅሰው፣ ፕሮጀክቶቹ ድርቁ እያስከተለ ያለውን ተፅዕኖ ለመቋቋም ቁልፍ ሚና እንዳላቸው ነው ያስረዱት።

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ኢንዲሪያስ ጌታ እንዳሉት የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለመለወጥ በ7 ክልሎች ላይ ተስፋ ሰጪ ስራዎች እየተሰሩ ናቸው።

በተለይ አርብቶ አደሩ ከእንስሳት ሀብት ልማት ባሻገር አማራጭ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው የተሻሻሉ የእንስሳት ፣ የቦቆሎ፣ የማሽላና የስንዴ ዝርያዎች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ሠርቶ ማሳያ ማዕከላትና ማስፋፊያ ላይ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን አመልክተዋል።



አቶ ሰይድ ይመር

በዚህም በመቶ ወረዳዎች የሚገኙ ከ1 ሺህ 730 በላይ ቀበሌዎች ላይ እየተሰራ መሆኑን ኢዜአ ዘግቧል።

በፕሮጀክቱ 70 በመቶ የሚሆነውን ሴቶችና ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ግብ ተቀምጦ እየተሰራ መሆኑን ነው ያብራሩት።

በአርብቶ አደሩ አካባቢ ድርቅና ውስን የፀጥታ ችግሮች ማነቆ እንደነበር ጠቅሰው በአሁኑ ወቅት የተፅዕኖዎቹ መቀነስ በመቻላቸው በአዲሱን የበጀት ዓመት ዕቅዱን ለማሳካት ርብርብ ይደረጋል ነው ያሉት።

በመድረኩ ላይ ሰላም ሚኒስቴር፣ ከጤና፣ ከውሃና ሌሎች ተቋማት የተወከሉ የኮሚቴው አባላት ተገኝተዋል።

# መንግሥት ለሠላም እያደረገ ያለው ጥረት በሕወሓት ቡድን እየተደናቀፈ መሆኑ ተገለጸ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ሠላም ለመፍጠር እያደረገ ያለውን ጥረት ውሃ የሚችልስበት ተግባር በአሸባሪው ሕወሓት በኩል እየታየ ነው ሲሉ በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሱራፌል ጌታሁን ገለጹ። የሽብር ቡድኑ አሁንም የጦርነት ትኮሳ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ ሱራፌል ጌታሁን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሠላም ማንኛውንም አይነት አማራጮችን ለመጠቀም ዝግጁ መሆኑን ገልጸዋል። በአንጻሩ የሕወሓት ቡድን የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎችን እያስቀመጠ ለሠላሙ መዳተትና ሂደቱ እንዳይሳካ እያደረገ መሆኑን እንደታዘቡ ጠቅሰዋል። በተለይ የሽብር ቡድኑ አፈቀላጤ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን እየተናገሩት ያለው ጉዳይ የሰላም ንግግሩ ማጣጣል ከጀመረ ውሎ አድሯል። ይህ ደግሞ ለትግራይ ሕዝብ ሠላም ደንታ እንደሌለው ያሳያል ብለዋል።

በሰላማዊ ውይይት የፖለቲካ አለመግባባቶችን መፍታት ያስፈልጋል ያሉት መምህሩ፤ በተጨባጭ በሕወሓት በኩል ያለው አቋም ይህንን እያሳየ እንዳልሆነ፤ ከዚህ በተቃራኒ የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ለሠላም ውይይቱ እንቅፋት መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንደ መምህሩ ገለጻ፤ የአፍሪካ ሕብረት ለማሸማገል በሚያደርገው ጥረት የሕዋሓት ቡድን ያሳየው አቋም የሚያሳዝንና አሳፋሪ ነው። የሕብረቱ መቋቋም ሠላምና ጸጥታን ለማረጋገጥ፣ ልማትን በማረጋገጥ ለፖሊሲ ድጋፍ ለማድረግ እንዲሁም ሕብረቱ በዋነኛነት በአገራት መካከል በተለይ ከጸጥታ ጋር ተያይዞ በውጭም በውስጥም ያሉ ችግሮችን መፍታት ነው። ሆኖም የሕወሓት አቋም በኢትዮጵያ ላይ የነበረውን የሕብረቱን ሚና ያጎደለ ነው።

አሸባሪው ሕወሓት ለሠላም ቅድመ ሁኔታ መሆን አለበት ብሎ የራያንና የወልቃይትን ጉዳይ ያነሳበት ሁኔታም ተገቢ እንዳልሆነ ተናግረዋል። ምንም እንኳን ሕገ መንግሥቱን እነርሱ ቢያረቁትና እናውቃለን ቢሉም ተጻራሪ በሆነ መልኩ በተለይ በራያና የወልቃይትን ሕዝብ የማንነት ጥያቄ በማንሳቱ ሲጨቁኑት፣ ሲገድሉትና ሲያሳድዱት እንደነበርም አንስተዋል።

ቡድኑ ለሠላም ዝግጁ እንዳልሆነ ነገር ግን ሠላም ፈላጊ መስሎ በመታየት ዓለም አቀፉን ማሕበረሰብ እያደናገረ እንደሆነም አስገንዝበዋል። ይህንን አቋም ደግሞ ምዕራባውያን እየደገፉ እንዳሉና ባለፈው ወደ ትግራይ የሄደው ቡድን ያወጣው መግለጫ ለዚህ ማሳያ እንደሆነ አመላክተዋል።

መምህሩ አክለው እንደገለጹት፤ መንግሥት በአንጻሩ በትግራይ ክልል ያለ ገደብ የህክምና ግብዓትን ጨምሮ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች እንዲሁም ጥሬ ገንዘብ እንዲደርስ አድርጓል። ይህ ክረምት እንዳያልፋቸው ለአርሶ አደሩ ማዳበሪያ ጭምር እንዲደርስ ማድረጉም በቀላል የሚታይ ሁኔታ አይደለም። ይህ በመንግሥት በኩል ምን ያህል የክልሉ ሁኔታ እንደሚያሳስበው የሚያሳይ ተግባር ነው። ይህም ሆኖ እስካሁን ሕወሓት በኩል ፉከራና ትንኮሳ እንደቀጠለ ነው።

አሸባሪው ሕወሓት በባህሪው ለሠላም ክፍት አይደለም ያሉት መምህሩ፤ ቡድኑ አሁንም ለጦርነት የእየተዘጋጀና ትነኩሳ እያደረገ መሆኑን አመልክተዋል። የአሸባሪው ሕወሓት አመራሮች ራሳቸውን ለማቆየት ለትግራይ ሕዝብ ጠላት የመፍጠር ሥራን ሲያከናውኑ እንደነበሩ በመግለጽ ቡድኑ እስካለ ድረስ የትግራይ ሕዝብ ሠላም እንደማያገኝ ተናግረዋል።

በዓለም አቀፍ ሕግ የሚከለከሉትን ጥፋቶች የፈጸሙትን ሽፋፍነው በማለፍ የተለያዩ መግለጫ እያወጡ መንግሥትን በመወንጀል የሠላሙን መንገድ ውሃ እየቸለሱበት ነው ብለዋል።



**አቶ ሱራፌል ጌታሁን**

መንግሥት የሽብር ቡድኑ ለሠላም እንቅፋት እየሆነ እንዳለና ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ የማሳወቅ ሂደቱን ማጠናከር እንዳለበት ጠቁመዋል። ቡድኑ ወደ ሠላም ድርድር እንዲመጣ ጫና እንዲደረግበት ማድረግ እንደሚገባም ነው የመከሩት።

## ‹‹ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር ኃላፊነት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ጥቅም የማይለያዩ ናቸው። የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበርና አገርን ለማሳደግ ኃላፊነት የሚሰማው ጤነኛና ተጽእኖ ፈጣሪ ሚዲያ መገንባት አስፈላጊ ነው። ለዚህም የግልም ሆነ የመንግሥት ሚዲያዎች የሚዲያ አቅም በመገንባት ሕግና ሥርዓቱን አክብረው መስራት የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባል።

ሚዲያዎች የጋዜጠኝነት ሙያ በሚጠይቀው ልክና አግባብ ሥራቸውን መሥራት ከቻሉ ዓለም ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ መድረስ ይቻላል ያሉት ፕሮፌሰር ብሩክ፤ ሚዲያ ባለ ሁለት ሰይፍ ነው፤፡ በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ በአገር ግንባታ ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፤ በአግባቡ ካልተያዘ ደግሞ አገር ያፈርሳል ብለዋል።

‹‹ዓለም እንደ ቴንስ ኳስ ናት›› እንደሚባለው በአንድ ቦታ የተከሰተ ሁነት በሚዲያ አማካኝነት በደቂቃ ውስጥ ዓለምን ያስተጋባል። በአገር ሰላም፣ ደህንነት፣ ልማት እና ሌሎች ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ሚዲያ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸው፤ ብሔራዊ ጥቅምና ሚዲያ የተቆራኙ በመሆናቸው ሚዲያዎች ብሄራዊ ስሜትና ሃላፊነትን ተላብሰው መስራትን እንደሚኖርባቸው ተናግረዋል።

እንደ ፕሮፌሰር ብሩክ ገለጻ፤ ሚዲያው በምርጫ ሥልጣን የያዙ መንግሥታት ስራቸውን በሚገባ መስራትና አለመስራታቸውን የሚከታተልና ለሕዝብ የሚያሳውቅ በመሆኑ ጥንቃቄ በተሞላበት ስራውን ሊያከናውን ይገባል። ምክንያቱም ሚዲያ አወንታዊ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ ሲውል ውጤታማ ያደርጋል፤ ነገር ግን በአሉታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ከዋለ ደግሞ ጉዳት የሚያስከትል ይሆናል።

የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚጎዱ ጉዳዮችን መመከትና ብሔራዊ ጥቅምን ማስከበር የሚቻለው ሚዲያው፣ ምሁራን፣ ተመራማሪዎች፣ መንግሥት፤ ሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶች በቅንጅት መስራት ሲችሉ ነው። እንደ አገር ብሔራዊ ጥቅማችንን ለማስከበር በተደራጀ ሁኔታ በብቃት መስራት ይጠይቃል ብለዋል።

የግሉና የመንግሥት ሚዲያዎች በአገር ጉዳይ ላይ አብረው ሊሰሩ ይገባል ያሉት ፕሮፌሰር ብሩክ፤ በተደራጀ መንገድ መስራት ባለብን ልክ መስራት ባለመቻላችን ኢትዮጵያ ተበድላ እንደበደለች ስትወቀስ እንደነበርም አውስተዋል።

ሚዲያ ከብሔራዊ ደሕንነት፣ ከኢኮኖሚና ከማሕበራዊ ዕድገትን ለማፋጠን የሚያስችል በመሆኑ መንግሥት ሚዲያውን በማጠናከር የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም እንዲከበር መስራት አለበትም ነው ያሉት።

ኢትዮጵያም እንደ አደጉት አገራት እንድትሆን ከተፈለገ ሕዝብ፣ መንግሥትና ሚዲያውን አስተሳስሮ መስራት አስፈላጊ ነው ያሉት መምህሩ፤ የሚዲያ መጠናከርም ለመንግሥት መጠንከር ወሳኝ ነው። ምክንያቱም መንግሥት አጀንዳውን ለሕዝብ የሚያቀርበው በሚዲያ መሆኑን አብራርተዋል።

ሁሉም የሚያድገው ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን ሲወጡ ነው። አንድን ማሕበረሰብ መለወጥ ካስፈለገ ኃላፊነት የሚሰማው ጤነኛ ሚዲያ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ደግሞ የግሉም ሆነ የመንግሥት ሚዲያዎች በአገር ጉዳይ ላይ አቋም ወስደው አብረው መስራት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ፕሮፌሰር ብሩክ ገልጸዋል።

## የኢትዮጵያን የአየር...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሳምንታት ጀምሮ ኃይሉን ለውጊያ ሲያስጠጋ ነበር። በየጊዜውም ተኩስ እየከፈተ የሀገር መከላከያን ሲተነኩስ መቆየቱንም ነው ያነሱት።

ቡድኑ መንግሥት የዘረጋውን የሰላም አማራጭ ከቁብ ሳይቆጥርና የሰላም ሂደቱ ቴክኒካሊ ፈርሷል ብሎ መግለጫ ባወጣ ማግስት ትናንት ነሐሴ 18 ቀን 2014 ዓ.ም ሌሊት 11 ሰዓት ላይ በቆቦ ግራና ቀኝ ባሉ አካባቢዎች፣ በዞብል ተራራ፣ በቢሶበርና በወትወት ውጊያ መክፈቱን ገልጸዋል።

በዚህም የተኩስ አቁም ስምምነቱን ማፍረሱን ጠቅሰው፤ የሽብር ቡድኑ እየላከ ያለው ጀሌ በሀገር መከላከያ ሠራዊትና በጸጥታ ሃይላችን እየተለበለበ ነው ብለዋል።

እንደ ኢዜአ ዘገባ፤ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስደፈር የሽብር ቡድኑን እየጋለቡ ያሉ ሃይሎች ቢኖሩም የሀገር መከላከያ ሠራዊትና ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን ለማስከበር በተጠንቀቅ ላይ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በቀጣይም የሽብር ቡድን ሀገር የማፍረስ ህልሙን ትቶ ወደ ሰላማዊ መፍትሔ ካልመጣ እስከመጨረሻው እርምጃ ለመውሰድ ሙሉ ዝግጅት መደረጉን ጠቅሰዋል፡፡

አሁን የመከላከል እርምጃ እየተወሰደ ሲሆን በቀጣይም የማጥቃት እርምጃዎች እንደሚኖሩ ነው የጠቀሱት።

## አሸባሪው ሕወሓት የሰላም አማራጭን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በደቡብ ትግራይ በኩልም ተደጋጋሚ ሙከራ ቢያደርጉም መንግሥት ሙከራቸውን እያከሸፈ ዋናው መፍትሔ የሰላም መንገዱ ነው በሚል ጉዳዩ እንዳይባባስ ማድረጉ በመግለጫው ተነስቷል።

ሆኖም ከመንግሥት በኩል የቀረቡለትን በርካታ የሰላም አማራጮች ሁሉ ወደ ጎን በመተው የሽብር ቡድኑ ሕወሓት ታጣቂ ቡድን ሰሞኑን ሲፈጽም የሰነበተውን ትንኮሳ ገፍቶበት ትናንት ንጋት ላይ በምስራቅ ግንባር በቢሶበር፣ በዞብል እና በተኩለሽ አቅጣጫዎች ከለሊቱ 11 ሰአት ጀምሮ ጥቃት መፈጸሙን መንግሥት በመግለጫው አስታውቋል።

በወሰደው እርምጃም ተኩስ ማቆሙን በይፋ አፍርሷል ያለው መግለጫው፤ የፈጸመው ጥቃትም ሆነ እሱን ተከትሎ ያወጣው መግለጫ አስቀድሞ ለትንኮሳው ሲዘጋጅ እንደነበር ግልጽ ማሳያ ነው ብሏል።

ጀግናው የኢፌዴሪ የመከላከያ ሠራዊትና መላው የጸጥታ ሃይል ከሽብር ቡድኑ የተሰነዘረውን ጥቃት በተቀናጀ መልኩ በድል እየመከቱት ይገኛሉም ነው ያለው መግለጫው።

የትግራይ ሕዝብ ችግሮችን ለመፍታት ሰላማዊ አማራጭ ዛሬም፤ ነገም ብቸኛው መፍትሄ መሆኑን መግለጫው አስታውቆ፤ መንግሥት የተሳለጠና ያልተቋረጠ የሰብአዊ ድጋፍ ወደ ትግራይ ክልል እንዲገባ የተናጠል ተኩስ አቁም ማድረጉና ምቹ ሁኔታን መፍጠሩ፣ ለሰላም በር ይከፍታል በሚል እስረኞችን መፍታቱ፣ የሰላም አማራጭንም አሟጦ ለመጠቀም እንዲቻል የሰላም አማራጭ አብይ ኮሚቴን በይፋ ወደ ስራ አስገብቶ ግልጽ አቅጣጫንም ማስቀመጡ፤ አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ቁሳቁሶች ወደ ትግራይ እንዲጓጓዝ ማድረጉ እና በአሸባሪው ቡድን የወደሙ አገልግሎት መስጫዎችን በመጠገን በሶስተኛ ወገን በኩል ስራ ለማስጀመር እንቅስቃሴ እያደረገ እንደሚገኝ ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል ብሏል በመግለጫው፡፡

ቡድኑ ከበባውን እንሰብራለን፣ መተማመኛችን ክንዳችን ነው፣ የትግራይ መሬቶች ተወረዋል፣ እናስለቅቃለን፣ ወዘተ በሚል ፉከራ ታጅቦ ባለፉት ስድስት ወራት የተለያዩ ትንኮሳዎችን ሲያደርግ መቆየቱን መግለጫው አውስቶ፤ በምዕራብ በኩል በተደጋጋሚ ሞክሮ ሽንፈትን ተከናንቦ ተመልሷል፤ በደቡብ ትግራይ በኩልም ተደጋገሚ ሙከራ ቢያደርግም መንግሥት ሙከራውን እያከሸፈ ዋናው መፍትሔ የሰላም መንገዱ ነው በሚል ጉዳዩ እንዳይባባስ ማድረጉን መግለጫው አብራርቷል።

ሆኖም ከመንግሥት በኩል የቀረቡለትን በርካታ የሰላም አማራጮች ሁሉ ወደጎን በመተው የሽብር ቡድኑ ሕወሓት ታጣቂ ቡድን ሰሞኑን ሲፈጽም የሰነበተውን ትንኮሳ ገፍቶበት ትናንት ንጋት ላይ በምስራቅ ግንባር በቢሶበር፣ በዞብል እና በተኩለሽ አቅጣጫዎች ከለሊቱ 11 ሰአት ጀምሮ ጥቃት ፈጽሟል። በወሰደው እርምጃም ተኩስ ማቆሙን በይፋ አፍርሷል፡፡ የፈጸመው ጥቃትም ሆነ እሱን ተከትሎ ያወጣው መግለጫ አስቀድሞ ለትንኮሳው ሲዘጋጅ እንደነበር ግልጽ ማሳያ መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታውቋል፡፡

ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችንና መላው የጸጥታ ሃይላችን ከሽብር ቡድኑ የተሰነዘረውን ጥቃት በተቀናጀ መልኩ በድል እየመከቱት እንደሚገኙ መግለጫው ገልጾ፤ የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ከአሸባሪው ቡድን ለመጠበቅም በወትሮ ዝግጁነት ሁሉም የጸጥታ ሃይላችን በተጠንቀቅ መቆሙንም አስታውቋል።

ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል እንደሚባለው ቀድሞም በተካኑበት የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ስራ ራሳቸው ተንኩሰው ራሳቸው እየጮሁ ይገኛሉ ያለው መግለጫው፤ ለሰላም እጁን የዘረጋውን መንግሥት በሃሰት በመወንጀል “ድርድሩ አስቀድሞ ከሽፏል” በሚል ለተለያዩ ወገኖች ጦርነቱ እንደማይቀር ሲያደርጉ የነበረውን ቅስቀሳ በማጠናከር የትግራይን ወጣት ዳግም ሊማግዱት በይፋ አውጀው ወደ ጦርነት መግባታቸው በመግለጫው ተጠቅሷል፡፡

እንደ መግለጫው ማብራሪያ ፤ ሰሞኑን ዓለም አቀፍ አጫፋሪዎቻቸው ካሸለቡበት ብቅ ብቅ ማለታቸውም የጦርነት ዝግጅቱን በፕሮፓጋንዳ ዘመቻ የማጀብ አካል መሆኑ ግልፅ ሆኗል። ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ የትግራይን ወጣት ለማስጨረስ ሕወሓት የሚያደርገውን የጦርነት ጉሰማ እንዲያቆም ጠንካራ ግፊት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በሀገር ውስጥም ሆነ በመላው ዓለም የምትገኙ ኢትዮጵያውያን ከዚህ የጥፋት ሃይል የሚሰነዘረውን ጥቃት ለመመከትና ኢትዮጵያን የመበተን ግልጽ ዓላማ የያዘውን ይህንን የሽብር ቡድን የጥፋት ሙከራ ለማምከን በጋራ እንድንቆም መንግሥት ጥሪውን እንዳቀረበ መግለጫው አስታውቋል።

የሁሉም ኢትዮጵያውያን ጥያቄ መፍትሄ ማግኘት የሚችለው በሰላማዊ መንገድ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ ዛሬም ነገም የሰላም አማራጭ የመጀመሪያ መፍትሔ እንደሆነ መንግሥት ፅኑ እምነት አለው ያለው መግለጫው፤

ሆኖም አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በትንኮሳው ከገፋበት፤ መንግሥት ሀገር የማዳን ሕጋዊ፣ ታሪካዊና ሞራላዊ ግዴታ ስላለበት እንዲሁም የሽብር ቡድኑ ወደደም ጠላም ወደ ሰላም አማራጭ እንዲመጣ ለማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል፤ ይህንን ለማስፈጸም ደግሞ መንግሥትና መላው የፀጥታ ሃይላችን ከነሙሉ ብቃትና ቁመናቸው በተጠንቀቅ ላይ መሆናቸውን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መግለጫ አስታውቋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## አሸባሪው ሕወሓት ለሰላም የተዘረጋውን የኢትዮጵያ እጅ ነክሶ ጦርነት ከፍቷል!

ኢትዮጵያ በርካታ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት፣ ሊሰራ የሚችል የሰው ኃይልና ምቹ አየር ጸባይ ቢኖራትም በየዘመናቱ በሚነሱ ጦርነቶችና ግጭቶች ያላትን እምቅ ሀብት ሳትጠቀምበት ቆይታለች፡፡ ሀገሪቱን የገጠሟት የጦርነት ታሪኮች ከሰላም ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንዳታገኝ እንቅፋት ሆነውባታል፡፡ ይህንኑ በመረዳትም በተለይ ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በሀገሪቱ ሰላምና ጸጥታን ለማረጋገጥ በመንግሥት በኩል ትልቅ ፍላትና ቁርጠኝነት ቢኖርም አሸባሪው ሕወሓትና መሰል የጥፋት ቡድኖች ከውጭ ባዕዳን ኃይሎች ጋር በመቀናጀት ኢትዮጵያን የጦር አውድማ ለማድረግ በብዙ ሲሰሩ ተስተውለዋል፡፡

እኔ የማልመራት ሀገር ትበታተን ብሎ የጥፋት ዕቅዶችን እየነደፈ፣ እያስፈጸመና እየፈጸመ ዕድሜውን ለማራዘም ሲውተረተር የኖረው የሕወሓት አሸባሪ ቡድን ከጥንስሱ ጀምሮ ከሰላም ይልቅ ጦርነትን ዋነኛ ስልቱ አድርጎ ዘመናትን ተሻግሯል፡፡ የቡድኑ ታሪክ ሲገለጥም የሰላምን አማራጭ ተጠቅሞ ችግሮችን የፈታበት ታሪክ አይገኝም፡፡

ከሕወሓት ጽ/ቤት መስከረም 30 ቀን 2013 የወጣው «በጥብቅ የሚያዝ ሰነድ» ላይ በግልጽ እንደሰፈረው ሕወሓት ድርድርን እንደዋነኛ ስልት የሚጠቀመው እንደ ጊዜ መግዣ እንጂ ለሰላም ሲል አለመሆኑን እንዲሁም የችግሮች ሁሉ መፍቻ የጦር የበላይነት መሆኑን ያውጃል፡፡

የሽብር ቡድኑ ከጥንስሱ ጀምሮ የመጣበት መንገድ ከተለያዩ አካላት ጋር ከመወያየትና ችግሮችን በጋራ ከመፍታት ይልቅ በወዳጅና ጠላትነት በመፈረጅ የመጠፋፋት ዘር መዝራት ነው፡፡ ሀገሪቱንም ሲያስተዳድር በቆየባቸው 27 ዓመታት ለዘመናት አብረው የኖሩ ሕዝቦችን በማቃቃርና የበዳይ ተበዳይ ትርክት በመፍጠር ኢትዮጵያ በቀውስ አዙሪት ውስጥ እንድትቆይ ያለመታከት ሰርቷል፡፡ አሉ የሚባሉ ችግሮችም በሰላምና በውይይት ይፈቱ የሚሉ ጠያቂዎችንም በማፈን የሰላም መንፈስ ከሕዝብ ውስጥ እንዲጠፋም ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ጽዋው ሞልቶም በኢትጵያውያን የጋራ ክንድ ከሥልጣኑ ከተባረረ በኋላም ከለውጡ መንግሥት የቀረቡለትን ተደጋጋሚ የሰላም አማራጮች በመግፋት ጦርነትን አማራጭ አድርጓል፡፡ የሰላም ዘንባባ ይዘው ወደ መቀሌ የተጓዙ የኃይማኖት አባቶችንና ታዋቂ ሰዎችን አሳፍሮ በመመለስ ለሰላም ያለውን ጥላቻ በአደባባይ አሳይቷል፡፡ በመጨረሻም የሰሜን ዕዝን ከጀርባው በመውጋት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጦርነትን አውጇል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የተከፈተበትን ጦርነት በአስደናቂ ፍጥነት በመቀልበስ ቡድኑን ድባቅ መትቷል፡፡ መቀሌን ጨምሮ መላውን ትግራይን በጥቂት ቀናት የተቆጣጠረው የመከላከያ ሠራዊት ሰኔ 21 ቀን 2013 ለትግራይ ሕዝብ ሰላምና ልማት በማሰብ ትግራይን ለቆ ወጥቷል፡፡ የትግራይ ሕዝብ ሰብዓዊ አቅርቦት እንዳይቋረጡበት እስከ 100 ቢሊዮን ብር የሚደርስ የፍጆታ ቁሳቁስ አስቀምጦ በመውጣትም ለሕዝብ ያለውን ወገንተኝነት አሳይቷል፡፡

ሆኖም ከጦርነት ውጪ ዕድሜውን የማራዘም አማራጭ የሌለው የሽብር ቡድኑ ለሰላም የተዘረጉ እጆችን እንደገና በመግፋትና በአንዳንድ የውጭ ኃይሎች በመታገዝ ዳግም ወረራ በመፈጸም ጦርነት ከፍቶ እስከ ደብረሲና በመምጣትም በአማራና በአፋር ክልሎች ላይ በቃላት የማይገለጹ ግፎችን አድርሷል፡፡ በርካታ ቁጥር ያለውን ሕዝብ አፈናቅሏል፣ ገድሏል፣አረጋውያንን ሳይቀር ደፍሯል፡፡

የቡድኑን አጸያፊ ተግባራት በቃ በማለትም የኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይሎች አሸባሪው ቡድን የከፈተውን ጦርነት በመመከት ቡድኑን እያሳደዱ አከርካሪውን ሰብረውታል፡፡ በጦርነቱ መሸነፉን ሲያውቅም የትግራይን ሕዝብ እንደመያዣ በመጠቀም በክልሉ ርሃብ እንደተከሰተ ለማስወራት በብዙ ደክሟል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ ከላው ቀናኢነት በመነጨ መጠነ ሰፊ ሰብአዊ እርዳታዎችን በማድረስ ላይ ይገኛል፡፡ ከምግብና መድሃኒት አቅርቦት በተጨማሪም ቡድኑ ለጦርነት እንደሚያውለው እየተገመተም ጭምር ለትግራይ ሕዝብ ሲባል ከ2 ሚሊዮን ሊትር በላይ ነዳጅም ወደ ትግራይ እንዲገባ አድርጓል፡፡

የትግራይ ሕዝብ ስቃይ እንዲያበቃና ሰላም በሀገሪቱ እንዲሰፍን በማሰብም መንግሥት ብዙ ርቀት በመጓዝ በየትኛውም ስፍራ፣ በማንኛውም ጊዜ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ለመነጋገር ዝግጁ መሆኑን አስታውቋል፡፡ ይህ የሆነው በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) በይፋ እንዳስታወቁት የኢትዮጵያ መንግሥት ሶስት ዓመት ከመዋጋት አስር ዓመት ቁጭ ብሎ መነጋገርን ስለሚመርጥ ነው፡፡

ይሁንና ካለፈው ጥፋቱ የማይማረውና አንድ ትውልድ በጦርንት ሙሉውን ቢያልቅ ግድ የማይሰጠው አሸባሪ ቡደን ነሐሴ 18/2014 ዓ/ም ከሌሊቱ 11 ሰዓት ዳግም በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ከፍቷል። ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ባወጣው መግለጫ "ከመንግሥት በኩል የቀረቡለትን በርካታ የሰላም አማራጮች ሁሉ ወደጎን በመተው የሽብር ቡድኑ ሕወሓት ታጣቂ ቡድን ሰሞኑን ሲፈጽም የሰነበተውን ትንኮሳ ገፍቶበት ነሐሴ 18/2014 ዓ/ም ንጋት ላይ በምስራቅ ግንባር በቢሶበር፣ በዞብል እና በተኩለሽ አቅጣጫዎች ከለሊቱ 11 ሰአት ጀምሮ ጥቃት ፈጽሟል። በወሰደው እርምጃም ተኩስ ማቆሙን በይፋ አፍርሷል፡፡ የፈጸመው ጥቃትም ሆነ እሱን ተከትሎ ያወጣው መግለጫ አስቀድሞ ለትንኮሳው ሲዘጋጅ እንደነበር ግልጽ ማሳያ ነው። ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችንና መላው የጸጥታ ኃይላችን ከሽብር ቡድኑ የተሰነዘረውን ጥቃት በተቀናጀ መልኩ በድል እየመከቱት ይገኛሉ። የዜጎችን ሰላምና ደሕንነት ከአሸባሪው ቡድን ለመጠበቅም በወትሮ ዝግጁነት ሁሉም የጸጥታ ሃይላችን በተጠንቀቅ ቆሟል" ብሏል።

ሁልጊዜም ቢሆን የሰላም አማራጮችን የሚሸሸው የሽብር ቡድኑ የተለያዩ ሰበቦችን በመደርደር የሰላም ውይይቱን እየገፋ ቆይቶ ለትግራይ ሕዝብ ሲባል የተሰጡ የሰላም ዕድሎችንም በማምከን ጦርነት መክፈቱ የቡድኑን ጦር አምላኪነትና ሰላም ጠልነት ያሳየ በመሆኑ ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ይህ ቡድን በጥፋት ተግባሩ እንዳይቀጥል ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ቆሞ በቃህ ሊለው ይገባል!

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ድርጊቱንም ዜናውንም የመሥራት አባዜ

በይናገር እውነቱ

ድሮ ያነበብኩት አንድ መጽሐፍ ነበር፡፡ ሰውዬው አንድ ታዋቂ ጋዜጣ ማዘጋጀት ፈለገ፡፡ ጋዜጣው ማንም ያላገኘውን ዜና ማግኘትና ቀድሞ ዜናውን ማግኘት አለበት ብሎ ወሰነ፡፡ ይሄንን ለማድረግ የተከተለው ስልት ‹ተግባሩንም ዜናውንም መሥራት› የሚል ነበር፡፡ መኪና ለመጥለፍ ያቅዳል፤ ዜናውን ሠርቶ ወደ ማተሚያ ቤት ይልክና ሊወጣ ሲል መኪናው ይጠልፈዋል፡፡ ተግባሩንም ዜናውንም ስለሚሠራው ማንም አይቀድመውም፤ ማንም አያገኘውም፡፡ አውሮፕላን ጠልፏል፣ ፋብሪካ አቃጥሏል፣ ባንክ አስዘርፏል፤ ሰዎች አስገድሏል፡፡ በዚህ ሁሉ ጊዜ ዜናውን አስቀድሞ እንደ ፊልም ስክሪፕት ራሱ ይጽፍና ጋዜጣውን ካዘጋጀ በኋላ ነበር ድርጊቱንም ራሱ ይፈጽመዋል፡፡

መጀመሪያ አካባቢ ሰዎች ሁሉ በአድናቆት የሚያነቡት ጋዜጣ ሆነ፡፡ ሌሎች ሚዲያዎች ሪፖርተሮቻቸውን ወቀሱ፡፡ የሌሎች ጋዜጣ ደንበኞችም እየፈለሱ ወደዚህ ጋዜጣ ሄዱ፡፡ ነገሩ ግን ከዚህም በላይ አስደናቂ መሆን ጀመረ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ድርጊቱና ጋዜጣው በተመሳሳይ ሰዓት መውጣትና መፈጸም ጀመሩ፡፡ ይባስ ብሎም ጋዜጣው ከድርጊቱ ቀድሞ መውጣት ጀመረ፡፡ ይሄን ጊዜ ብልሆች ተጠራጠሩ፡፡ የተወሰኑ አካላት ምርመራ ጀመሩ። በመጨረሻም ደረሱበት፡፡ የጋዜጣው ቀዳሚነትና ብቸኛ የዜና ምንጭነት ምክንያት፣ ድርጊቱንም ዜናውንም አንድ ሰው ስለሚሠራው መሆኑ ታወቀ፡፡ ያው ዘብጥያው ይመቻችለታል እንግዲህ፡፡

የሕወሓትም ነገር እንዲሁ ነው፡፡ ሕወሓት ተነካሁ፣ ተመታሁ፤ ተጠቃሁ ማለት ጀምሯል። ለዚህ ኡኡታው መቅድም ነበረው፡፡ መጀመሪያ ድርድሩ አይሳካም አለ። ቀጥሎ ደግሞ ቅድመ ሁኔታ አስቀመጠ፡፡ ቀጠለና በምዕራብ በኩል ተጠቃሁ አለ፡፡ ከዚያ የተናጠል የተኩስ አቁሙ ፈርሷል አለ። አስከትሎ ደግሞ በየአገሩ ያሉ ተከፋይ የነጭ ሠራዊቱን ማንጫጫት ጀመረ፡፡ የበጋ ስንዴን ከመቃወም ጀምረው የኢትዮጵያ አየር መንገድን እስከ ማሳጣት ተረባረቡ፡፡ በመጨረሻም ዛሬ ጦርነት ተከፈተብኝ አለ፡፡ እስክስታው ቀድሞ ስለመጣ፣ ዘፈኑ እንደሚከተል ይጠበቅ ነበር፡፡

> **ለመሆኑ ሕወሓት ለምን ቀድሞ ጮኸ? መልሱ ቀላል ነው። ድርጊቱንም ዜናውንም ራሱ ስለሠራው ነው፡፡ እንደ ፊልም ጽሑፍ አስቀድሞ ዜናውን አዘጋጀ። ከዚያ የተለመደ ትንኮሳውን ጀመረ፡፡ በዚህ የተነሣ ዜናውና ትንኮሳው በተመሳሳይ ሰዓት ተፈጸመ፡፡ አንዳንዶች ምሥጢር መጠበቅ ያቃታቸው ወዳጆቹ ደግሞ፣ ከተግባሩ በፊት ዜናውን ለቀቁት። ተጠቃሁ ከማለቱ በፊት ገደልን ብለው ፕሮፓጋንዳውን አበላሹበት**

ለመሆኑ ሕወሓት ለምን ቀድሞ ጮኸ። መልሱ ቀላል ነው፡፡ ድርጊቱንም ዜናውንም ራሱ ስለሠራው ነው፡፡ እንደ ፊልም ጽሑፍ አስቀድሞ ዜናውን አዘጋጀ፡ ፡ ከዚያ የተለመደ ትንኮሳውን ጀመረ፡፡ በዚህ የተነሣ ዜናውና ትንኮሳው በተመሳሳይ ሰዓት ተፈጸመ። አንዳንዶች ምሥጢር መጠበቅ ያቃታቸው ወዳጆቹ ደግሞ፣ ከተግባሩ በፊት ዜናውን ለቀቁት፡፡ ተጠቃሁ ከማለቱ በፊት ገደልን ብለው ፕሮፓጋንዳውን አበላሹበት፡፡

ከዚህ በፊትኮ ‹ከኢትዮጵያ የፖለቲካ መሪዎች ጋር እየተገናኘን ነው› ብሎ መግለጫ ሰጥቶ ነበር፡፡ ታዲያ በድብቅ ተገናኘን ካላችሁ በይፋ ለመገናኘት ለምን ከበዳች። ለምን የድርድሩን መንገድ ፈራችሁት። ‹በሽታው እንዲታወቅ የማይፈልግ ሰው ሐኪም ቤት አይሄድም› ሆኖባችሁ ካልሆነ በቀር፡፡ ሕዝቡስ አያሳዝናችሁም። ትግራይን ያለ ትውልድ ማስቀረት አያሳዝናችሁም። ሁለት ጊዜ ያደረጋችሁት ጦርነት መጨረሻው ‹እንትን ይግባ፣ እንትን ይለቀቅ፣ እንትን ይሰጠን› ብሎ ከመለመን የዘለለ ምን አመጣላችሁ።

ይልቅ ወደ ድርድሩ ጠረጴዛ ወርዳችሁ ለሕዝቡ አገልግሎት ስለሚለቀቅበት መንገድ፣ እርዳታው ያለ እንከን ስለሚቀርብበት መንገድ፣ ሕዝቡ ከሌላው ወገኑ ጋር ስለሚገናኝበት መንገድ አትመከሩም። ‹የአገልግሎቶች ጉዳይ ፖለቲካዊ ሳይሆን የአፈጻጸም ችግር ነው። እንዴት እንፈጽመው በሚለው ላይ እንምከር› ስትባሉ፣ ለሕዝብ ስትሉ ሲኦልስ ድረስ መሄድ አልነበረባችሁም። መቀሌ የተቀመጡ ፕሮፓጋንዲስቶቻችሁን ‹አንተ ከቆቦ፣ አንተ ከወልድያ፣ አንተ ከራያ፣ አንተ ከወልቃይት ነኝ ብለህ ተናገር› እያላችሁ ለውጭ ሚዲያ ስላስተላለፋችሁ መሬት ላይ ያለው ነገር ይቀየራል።

እነዚህ ሚዲያዎችኮ ኢትዮጵያ አረንጓዴ ስትለብስ አታሳዩኝ፣ ኢትዮጵያ በስንዴ ምርት ስትጥለቀለቅ አትጥሩኝ፣ ኢትዮጵያ ድል ስታደርግ አትንገሩኝ፣ ኢትዮጵያ ግድቧን ስትሞላ አትቀስቅሱኝ ሲሉ ነበር፡፡ ሁለታችሁም ከጦርነት ብቻ ስለምታተርፉ የአጋምና ቀጋ ወዳጅነት ፈጥራችሁ፣ የሕዝቡን መከራ አበዛችሁበት፡፡ ችግሩንም ዜናውንም አብራችሁ እየሠራችሁ የጅራፉን ነገር ደገማችሁት፡፡

በተለያዩ ጊዜያት በመከላከያ ሠራዊቱ ላይ ትንኮሳዎች ተፈጽመዋል፡፡ ነገር ግን ትንኮሳዎቹን ከመመከት ባለፈ መከላከያው ከምንም ነገር ታቅቦ ሲጠብቅ ነበር፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ መንግሥት ዋናው የመፍትሔ አማራጩ የሰላሙ መንገድ መሆኑን አቋም ስለያዘ፡፡ አሁንም እንኳን ይሄንን አቋሙን አልቀየረም፡፡ ‹ጥላቻ ሕይወቴ፣ ጦርነት ርስቴ፣ ውሸት እስትንፋሴ፣ ዕብሪት ደመ ነፍሴ› ብሎ የሚያምነው ሕወሓት ግን፣ አጉራ ጠናኝ ብሏል፡፡

ለሰላም የተዘረጉ እጆች አሁንም አልታጠፉም፤ አይታጠፉም፡፡ እነዚህን እጆች ደጋግሞ መውጋት ግን፣ የሰላም እጆች ሌላ ነገር እንዲጨብጡ ያስገድዳቸዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# «እረኛዬ !» የአገራዊ ምክክሩ ፍኖተ ካርታ ...!?

በእዝነ ህሊናችሁና በምናባችሁ የያሬድ ሹመቴ ግጥምና ዜማ የሆነውን፤ ታደለ ፈለቀ ማለፊያ አድርጎ ያቀናበረውን ግርማ ተፈራና ራሔል ጌቱ ሽጋ አድርገው ያዜሙትን "የእረኛዬ"ይዛችሁ ተከተሉኝ፡፡ በነገራችን ላይ ይህ ድንቅ ስራ ቴዲ አፍሮ የክቡር ዶ/ር ሀዲስ አለማየሁን ዘመን ተሻጋሪ ስራ "ፍቅር እስከ መቃብር"ን ከ10 ደቂቃ ባልበለጠ ክሊፕ በ"ማር እስከ ጧፍ" ማለፊያ አድርጎ ያበረከተልንን ስራ ያስታውሰናል። ያሬድ ሹመቴም በ48 ክፍሎች የተላለፈውን የአገራችንን ተከታታይ ድራማ ታሪክን የቀየረውን፤ ከዚህ በኋላ መነሻም መለኪያም ሆኖ የሚያገለግለውን "እረኛዬ"ን ከስድስት ደቂቃ ባልበለጠ ክሊፕ ቅንብብ አድርጎ አቅርቦልናል። እናመሠግናለን።

"የእረኛዬ" ተከታታይ ድራማ በአርትስ ቴሌቪዥን ሲተላለፍ ባጅቶ ባለፈው አርብ ነሐሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም ሲጠናቀቅ በአእምሮዬ ሁለት ምናባዊ አሻራዎችን አኖረ። የመጀመሪያዊ የአገራችንን ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ በኪን አዋዝቶና አስውቦ ያቀረበ፤ ሁለተኛው ደግሞ ላለምነው አገራዊ ምክክር ፍኖተ ካርታ የሚሆን ዳና ትቶልን መሔዱ። እንደ እናና የሚሰበስበንና የሚጠብቀን እረኛ የሚያስፈልገን ሰዓት ላይ ነንና ከዚህ አንጻር ዘመኑንም ሆነ ትውልዶችን የዋጀ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ወደ ተወሰኑ ሌሎች የአገራችን ቋንቋዎች ቢተረጎምና ቢተላለፍ ለአገራዊ ምክክሩ መልመጃና እርሾ ሊሆን ይችላል ብዬ አምናለሁ። ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይም ሆነ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ለደራሲዎቹና ተዋናዮች እውቅና ቢሰጧቸው ተገቢ ነው ብዬም አምናለሁ።

እዚህ ላይ ሳይነሳ መታለፍ የሌለበት ትልቅ ጉዳይ፤ በቴሌቪዥን በአስር ሚሊዮኖች የሚገመት ተመልካች፤ በዩቲውብ ከሦስት ሚሊየን በላይ ሕዝብ የተከታተለውን ይሄን ፋና ወጊ ድራማ መጠናቀቅ አስመልክቶ፤ ሚዲያዎቻችን ዛሬም ከስብሰባ አዳራሽ፣ ከልማት ዘገባ፣ ከፕሮቶኮል ዜና፣ ከአኃዝ ፍቅር፣ የመሪን ጥላና ዳና ከመከተል ክፉ አባዜ ባለመላቀቃቸው "እረኛዬ"ን ከተለያየ ማዕዘን አንጻር በዘረፉ ሊቃውንት ሊያስተረጉሙልን፣ ሊያስበይኑልንና ሊያስተነትኑልን ሲገባ፤ እንደለመዱት ባላየ ባልሰማ አልፈውታል። ለከፈላቸው ዩኒቨርሲቲ ግን የተማሪ ምረቃ በቀጥታ በማስተላለፍ ከአለም የመጀመሪያ ናቸው። ይህ ክፉ አባዜና ከሳጥን ወጣ ብሎ ያለማሰብ መርገም ፊት ሊነሳ ይገባል። ሌላው "እረኛዬ"ን ስፖንሰር ለማድረግ ሲጓደዱ የነበሩ የግልም ሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በራሳቸው ሊያፍሩ፤ ስፖንሰር ያደረጉ ደግሞ በራሳቸው ሊኮሩ ይገባል። በቀጣይ ግን እንደ"እረኛዬ"ያሉ ታላላቅ ዘመን ተሻጋሪ ስራዎችን የሚደግፍ ራሱን የቻለ ፈንድ ሊቋቋም ይገባል።

በebs የ"Tech Talk With Solomon" አዘጋጅና የ"ግርምተ ሳይቴክ" ደራሲ ሰለሞን ሙሉጌታ ካሳ፤ "እረኛዬ! የኢትዮጵያችንን ጠቢንና ፍቅሯን፣ ለቅሶዋንና ሳቋን፣ የኋላዋንና የፊቷን፣ ስህተቷንና እርማቷን፣ ጨለማዋንና ብርሃኗን፣ ፍርሃቷንና ድፍረቷን፣ ሃዘኗንና ደስታዋን፣ ድካሟንና ብርታቷን፣ ጥፋቷንና ልማቷን፣ ውሸቷንና እውነቷን፣ ደዌዋንና ፈውሷን፣ ስብራቷንና ጥገናዋን፣ መካንነቷንና ወላድነቷን፣ መርገሟንና በረከቷን፣ ስቃይዋንና ፍሰሃዋን፣ ወከባዋንና እረፍቷን፣ ስቃይዋንና ሰላሟን፣ ድህነቷንና ባለጸግነቷን፣ በደሏንና ምህረቷን፣ ጥርጣሬዋንና እምነቷን፣ ቁዘማዋንና ሃሴቷን፣ መውደቅና መነሳቷን፣ ጠላቷንና ወዳጇን፣ ቂሟንና ይቅርታዋን፤ ማጣቷንና ማግኘቷን፣ ሞቷንና ትንሳኤዋን ቁልጭ አድርጎ አሳየን! ፍቅር ከጥላቻ፣ ምህረት ከህይወት፣ ይቅርታ ከቂም፣ ብርሃን ከጨለማ፣ በደልን መሸፈን ከበቀል ምን ያህል አብልጠው ሃያልና አሸናፊ እንደሆኑ በእረኛዬ ግዙፍ የተስፋ መስኮት ውስጥ ይታያሉ!፡፡ ድርሰቱ ለአገር መርህ ሊሆን የሚችል፣ መልዕክቱ በልቦና ቢያድር አገር የሚዋጅ፣ ሃሳቡ ቢተገበር ትውልድ የሚያድን፣ ትወናው እንደ ጥበብ ጥግ ተቆጥሮ ሁሌም የሚሞገስ፣ ደራሲያኑ፣ ተዋንያኑ፣ የሙዚቃና የፊልም ባለሞያዎቹም ክብር የሚያሰጣቸው ብቻ ሳይሆን የአገር ጀግኖች የሚያስብላቸው ነው!፡፡ እረኛዬ — የኢትዮጵያ የመዋጀት ተስፋ መስኮት! Great job Arts Tv World!" ሲል ገልጾታል።

ደራሲና ጋዜጠኛ ቴውድሮስ ተክለአረጋይ እንዲሁ በፌስቡክ ሰሌዳው "የሚያስቀናው የእናና አሟሟት" በሚል ርዕስ፤ እኔ ከሕይወት በሞት እቀናለሁ። ከሞትም አሟሟት ይዋብብኛል። የሰው ልጅ ወትሮም ለሞት የተፈጠረ ነው። እስከ ዘለዓለማዊው ሞት ባለው መንገድ ላይ ለአጭር ጊዜ እዚህ ዓለም ይኖራል። ይህ ዓለም ወደ ሞት የምናዘግምበት መንገድ እንጂ መኖሪያችን አይደለም። ችግሩ ግን መኖርን እንለምደውና ሞት ያስፈራናል። እናና ሞተች። በሞቷ ተዋበች። ምንም እንኳን ለሞቷ ምክንያት ሆኖ የመጣው የሌሎች ጠብ፣ የጉልበተኞች እርግጫ ሳሯን እናናን ቢወስዳትም፣ እናና ለሞት ቅርብ ነበረች። እናና ለግል ሕይወቷ ጉጉ አልነበረችም። ለሌሎች ቤዛ የሆነ ሕይወት ነበራት። ብዙዎች የእናና ሞት አሳዝኗቸዋል። አበሳጭቷቸዋል። ውበቱም እሱ ነው። የእናና ሕይወት ለሞት ቅርብ ነው። እናና ሳትሆን ለ"እረኛዬ" መስዋዕት የሆነችው "እረኛዬ" ነው የተሰዋላት። ሁሉም ገጸባህሪያት ተሰብስበው ለእናና የመንፈስ ልዕልና ባርኔጣቸውን አንስተው ነው "እረኛዬ" የተጠናቀቀው። ማን ነው ከእንግዲህ በ"እረኛዬ" ድራማ ላይ ሀውልት ሆኖ የቆመው? እናና ናት። ምረጡ ብትባሉ ማንን መሆንን ነው የምትመርጡት? እኔ እናናን መሆንን እመርጣለሁ። በሕይወት ካሉት ይልቅ ለሌሎች ጥርሷን ነክሳ፣ ጉዳቷን አሳንሳ፣ እንደዚያ ምድር እስኪጠባት የምትሮጠዋ ሴት ቅዝዝ እንዳለች፣ ጉዳቷን ሌሎች እንዳይሰሙ ሕይወቷን በጥርሷ ነክሳ ሄደች።

እናና በሕይወት ብትኖር ለራሷ ካልሆነ ለእኛ ምን ይፈይድልናል? ብዙዎች አለን እኮ ለመኖር ለመኖርማ። ለማንም ምንም ሳናደርግ ምንም ሆነን የምንኖር። እናና ግን በሞቷ ከእኛ በላይ ትኖራለች። አብነት መንደር ውስጥ እያንዳንዱ ነዋሪ ልብ ውስጥ ሀውልት አላት። እሱ ነው ቁምነገሩ። መኖር ማለትም እሱ ነው፤ አለመሞት አይደለም። የእናና መንገድ መጨረሻው እንዲህ ነው። በሕይወት የሚሞቱበት ሳይሆን በሞት የሚኖሩበት ነው። የቴዎድሮስ (የቋራው)፣ የማርቲን ሉተር፣ የክርስቶስ አይነት የቤዛነት ሞት ነው ሞቷ። የሰሜን ሸዋዎቹ አባትና ልጅ ጀግኖች ሞትን እንረሳዋለን ? የእሸቴ ሞገስ ድምጽ ከጆሯችንስ ሆነ ከልባችን ይወርዳል? "ለዚህ ጀግንነትስ እንኳን ሞቱ" አላልንም? እኔ ብያለሁ። ከብዙ ሰው ሕይወት የእሸቴ የጀግንነት ሞት እንዳስቀናኝ አለ። ከመኖራቸው ሞታቸው ነው ልባችንን ከፍ ያደረገው። ለመኖር እኮ ባንዳም ሆኖ መኖር ይቻላል። " እረኛዬ " ላይ ለእኔ እጅግ የተዋበው አጨራረስ የእናና ሞት ነው። ሞት ትንሳኤ ነው። ሞት ፈውስ ነው ፤" ሲል ግሩም አርጎ ገልጾታል፡፡

የአማርኛው ቢቢሲ ደግሞ ሸጋ አድርጎ የሔሰበትን መጣጥፍ ላጋራችሁ፤ እረኛዬ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ በአርትስ ቴሌቭዥን በአራት ምዕራፎች በ48 ክፍሎች ሲተላለፍ ቆይቶ አርብ ነሐሴ 13/2014 ዓ.ም. ተጠናቋል። ይህ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ በአዜብ ወርቁ፣ በቤዛ ኃይሉ እንዲሁም በቅድስት ይልማ የተጻፈ ሲሆን፣ ያዘጋጀችው ደግሞ ከደራሲዎቹ መካከል አንዷ የሆነችው ቅድስት ይልማ ነች። እነዚህ ሦስት ደራሲያን ለፊልም ጽሁፍ እንዲሁም ዝግጅት እንግዳ አይደሉም። በስማቸው በርከት ያሉ ሥራዎች ሰፍረው ይገኛሉ። በጥምረት ግን ሲሰሩ ይህ የመጀመሪያቸው ነው። እረኛዬ ተከታታይ የቴሌቭዥን ድራማ መቼቱን ያደረገው ከከተማ ግርግር ርቆ፣ ሕይወት ስክን ብላ በምትፈስበት ገጠር ውስጥ ነው። ይህ አብነት የተሰኘ የገጠር መንደር በምናብ የተፈጠረ ነው። ይህች የገጠር መንደር ኢትዮጵያን እንድትመስል ተደርጋ ነው የተሳለችው። በዚህ መንደር በፍቅር ተሳስበው የሚኖሩ ዘመዳሞች እና ጎረቤታሞች ፍቅራቸውን የሚነቀንቅ ተቀናቃኝ መጥቶባቸዋል። ይህ ተቀናቃኝ ባለሀብት ነው። በሀብቱ ብዛት መሬታቸውን ሊነጥቅ የቋመጠ፣ ለዚህም በቀኝ በግራው፣ በፊት በኋላው ግለሰቦችን ያሰለፈ ነው። ይህ ባለሀብት የሚነጥቃቸው መሬት ይምሰል እንጂ ከመሬቱ ጋር የተሰፋ ማንነት፣ ባሕል እና ትውፊት አብሮ አለ። የአብነት መንደር ነዋሪዎች ይህንን የኖረ ባሕላቸውን፣ ማንነታቸውን ለመከላከል በገበሬ አቅማቸው ይውተረተራሉ፡፡

በድራማው የመጀመሪያ ክፍል ላይ የምናያቸው እና በኋላም በታሪኩ ውስጥ በተደጋጋሚ በአርዓያ ሰብነት የሚጠቀሱት አብዬ በቃሉ ከአካባቢው ሁሉ የተለዩ ግለሰብ ነበሩ። መለየታቸው ለመልካም ነው። ሕብረት ይወዳሉ፤ ድንበር አይፈልጉም። አገራዊ እውቀቶች ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው እንዲተላለፉ አጥብቀው ይሻሉ። ለእርሱም ትምህርት ቤት ከፍተው የአብነትን ነዋሪዎች ያስተምሩ ነበር። ነገር ግን ልጃቸው ከጋብቻ ውጪ አርግዛ የሠርጓ ዕለት በመውለዷ በድንጋጤ ሕይወታቸው አለፈ። አገሬው ጉድ አለ፤ የአቶ በቃሉ ሕልም ተዳፈነ። ቤተሰቡ አንገቱን ደፋ። ልጃቸው ወጋየሁም ጨርቄን ማቄን ሳትል ሌሊቱን ማንም ወደማያውቃት አገር ተሰደደች።

የአብነት መንደር ወግ ባሕል ልማድ የተጣሰው ዋነኛ ተቆርቋሪ በሆኑት አብዬ በቃሉ ልጅ፣ ወጋየሁ ነው። በኋላ ግን የጠፋው ወግ ባሕል ልማድ በእርሳቸው የልጅ ልጅ እንደ አዲስ ሲያንሰራራ እንመለከታለን። በአንድ ማህጸን ያደሩት ዳዊት እና መንግሥቱ በተለያዩ ወላጆቻቸው እጅ ማደጋቸው፣ የተለያየ ባሕርይ እና ማንነት ሰጥቷቸው የማይግባቡ ዥንጉርጉሮች አድርጓቸዋል። ያደሩበት ማህፀን፣ ተካፍለው የጠቡት ጡት ያቆየላቸው እንጥፍጣፊ ፍቅር ያለ አይመስልም። እረኛዬ በእነዚህ ገፀ ባሕሪያት በኩል የአገርኛ እውቀቶች እንዲያብቡ፣ ባሕል ወግ ልማድ እንዳይጣስ፣ ፍቅር ይቅርታ የኑሮ አምድ እንዲሆኑ ደጋግሞ ይወተውታል።

በበርካቶች ዘንድ ትኩረትን ያገኘው ለዚህ ይሆን? ድራማውን የተከታተሉ ሁለት ግለሰቦች አነጋግረናል ይላል ቢቢሲ። ገሸሽ ያደረግነውን ማንነት ፍለጋ በእረኛዬ ድራማ ላይ የምናያቸው የማምረቻ መሳሪያዎቹ፣ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ፣ ወዘተ የራሳቸው የሆነ ቱባ ሥነ ውበታዊ ገጽታ አላቸው። በአሰራራቸው የአገርኛ ጥበብ አሻራ ታትሞባቸው ይገኛል። በድራማው ላይ የሚታዩት የሰላምታ ልውውጦች፣ የግብይት ልማዶች፣ የጋብቻ ሥርዓቶች፣ የአምልኮ ትውፊቶች፣ የለቅሶ ልማድ ሁሉ የየራሳቸው ውበትና መስህብ እንዲኖራቸው ተመልካችን እንዲያማልሉ ሆነው ተቀርፀዋል። በድራማው ላይ በእረኞች እና በኮማሪቷ ማስረሻ፣ የሚገጠሙ ግጥሞች የማኅበረሰቡን ማንነትና ስሜት ከማንጸባረቅ ትይዩ የቆሙ፣ ሥነ ጽሑፋዊ ቴክኒክ ተላብሰው የቀረቡ ናቸው። ይህም የማዝናናት ለዛቸውን አጉልቶ፣ አይረሴና ተጨባጭ አድርጓቸዋል። ድራማው አካብቶ ያቀርብልን የማኅበረሰቡ ጠቅላላ የተሞክሮ ዕውነታ ባሕላዊ ማንነትን የሚያጎሉ ቅርሶች የተዝናኖት ፋይዳ ጨምረውለታል። የደራሲዎቹ የተጠባቢነት አቅም ልኩ የሚመዘነው ደግሞ እነዚህን አጣጥሞ በማቅረብ ብቃቱ ላይ የተመሰረተ መሆኑን የባላገሩ ቴሌቪዥን የፕሮግራም ዳይሬክተር የሆነው ሲራክ ተመስገን ይናገራል።

የቲያትር እና የፊልም መምህር የሆነው አንተነህ ሠይፉ በበኩሉ፣ እረኛዬን የወደድንበትን ምክንያት ሲያነሳ አስቀድሞ የሚጠቅሰው መቼቱን ነው። በኢትዮጵያ የፊልም እና የተከታታይ ድራማ ታሪክ መቼታቸውን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያደረጉ ሥራዎች በቀላሉ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እና ተወዳጅነት ማግኘታቸውን በማንሳት እረኛዬም ይህ እንደረዳው ይገልጻል። የዚህ ተከታታይ ድራማ ደራሲና አዘጋጅ የሆነችው ቅድስት ይልማ ቀዳሚ ሥራ የሆነው 'ረቡኒ'ን በምሳሌነት ያነሳው አንተነህ፣ በተመሳሳይ መልኩ መቼቱን ገጠር በማድረጉ ተወዳጅነትን አትርፎ እንደነበር ያስታውሳል። አንተነህም ሆነ ሲራክ፣ እረኛዬ ተከታታይ ድራማ፣ ያነሳው ታሪክ ወደ ጥንታዊ ማንነት፣ ገሸሽ ወዳደረግናቸው ባሕላዊ እሴቶቻችን መመልከቱ በተመልካች ዘንድ ተወዳጅነት ለማግኘቱ አስተዋጽኦ ማድረጉ ላይ ይስማማሉ። አክለውም ታሪኩ የተዋቀረበት እና ገጸ ባህሪያቱ የመጡበት ዓለም፣ ከማኅበራዊ ከሌሎች እሴቶቻችን ጋር መሳ ለመሳ መሆኑ ተቀባይነት ለማግኘት አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ይናገራሉ። ዳይሬክተሯም ገጸ ባህሪያቱ የተቀዱበት ማኅበረሰብን ማንነት ለማጉላት የተጠቀመችባቸው ነባር እሴቶችም አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን አንተነህ አክሎ ይገልጻል። ገጸ ባህሪያቱ በምናብ በተፈጠረ መንደር፣ አብነት፣ ልቦለዳዊ ኑሯቸውን መስርተዋል። የማኅበረሰቡን ኑሮ አይኑሩ እንጂ፣ ለኑሮው መስታወት ሆነው የራሱ የዕለት ተለት ገመና መልሶ እንዲመለከት አድርገውናል፡፡

በድራማው ውስጥ የማኅበረሰቡን እንከን፣ ሠላም የማጣት፣ የመናቆር፣ ይቅር ማለት አለመቻል ፍጥጥ ብሎ እንዲታይ አድርጓል። ለዚህም እንቆቅልሽ ብሎ በመጠየቅ ከራስ መልስ እንደመጠየቅ አይነት ነው። ደራሲዎቹ በገጸ ባህርያቱ ሕይወት በኩል እንቆቅልሽ ብለው ይጠይቃሉ። ተመልካቹም ፍንጮቹን እየተከተለ የሕይወትን እንቆቅልሽ የመፍታት ድርሻን ይወስዳል። አንተነህ ይህንን ሃሳብ ሲያጠናክር "ወቅቱን የሚገልፁ፣ ሰው ልብ ውስጥ ያለውን፣ በአደባባይ መተንፈስ መናገር የማይችለውን ነገር በድራማ መልክ ስለማንነታችን፣ ስለ እርስ በእርስ ግንኙነታችን ስለአናኗራችን አሁን ስላለው ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ በጥሩም ይሁን በመጥፎ ያነሳሳል" ይላል።

ላለው ወቅታዊ ፖለቲካዊ ሁኔታ ጥያቄ ነው ያለውን ድራማው ያነሳል፤ ሲራክም ሆነ አንተነህ በድራማው በኩል የራሳችን ገበና፣ ከአደባባይ ርቀን በማጀታችን የምናወራው ነገር ሲቀርብልን፣ መተንፈሻ ፋካ ሆኖን በማገልገል ተወዳጅነትን አትርፏል ይላሉ። ሲራክ አክሎም ዳይሬክተሯ ቅድስት አገሪቷ ያሉባትን ችግሮች፣ አገር በቀል በሆነ እውቀት ውስጥ መፍትሔ መፈለግን እንደ ስልት ይዛዋለች ይላል። የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የወንዶች ዓለም ነው በሚለው ሀሳብ አንተነህና ሲራክ ይስማማሉ። አብዛኞቹ ታሪክ ነጋሪዎችና ፀሐፊዎች ወንዶች በመሆናቸው በወንድ ዐይን ነው ዓለሙን የሚያሳዩን ይላል አንተነህ።

የምንኖረውን የአባታዊ ሥርዓት፣ በምንታደመው የጥበብ መድረክ ላይም የምናየው ሕይወት የወንዶች ምናብ ውጤት ነው በማለት ያክላል ሲራክ። "ዓለሙን፣ ሕይወትን፣ አገርን የሚተረጉሙት በወንድ መነጽር ነው" ይላል አንተነህ። የእረኛዬ ደራሲዎች ግን ከዚህ ተቃራኒ ዕድል ነበራቸው። እንዲህ ሴቶች በድርሰትም በዝግጅትም ሰብሰብ ብለው መምጣታቸው እንደ እረኛዬ አይነት በሥርዓተ ጾታ ላይ ጥንቁቅ የሆነ ድራማ እንድናገኝ ረድቶናል ይላል ሲራክ። ለዚህም ነው የእረኛዬ ሴት ገጸባህሪያት የድራማው ደምና አጥንት ሆነው ነው የተሳሉት። የአብነት መንደር ሕይወት በጫንቃቸው ነው። የአብዬ በቃሉ አደራ በደም ሥራቸው ይፈሳል። የትምህርት ቤት ደጃፍ ባይረግጡም፣ የፊደል ዘር ባይለዩም ሕይወትን፣ በዙሪያቸው የተንሰራፋውን ዓለም በገባቸው ልክ የሚተረጉሙ እና እርሱንም አጽንቶ ለማቆም የሚታገሉ ናቸው። የእረኛዬ ሴት ገጸ ባህሪያት ለከተማ ሕይወት ባዳ ሆነው፣ የቀለም ዘር ሳይለዩ ለመብታቸው የሚቆሙ ናቸው የሚለው ደግሞ አንተነህ ነው።

በዚህ ሃሳብ ሲራክም ይስማማል። "በእረኛዬ ድራማ ላይ ልፍስፍስ ሴት አትታይም፤ ከወንዶች እኩል የምትገዳደር ሴት እናገኛለን" ሲል ያክላል። አንተነህ ሲያክልበት ደግሞ "ለእህቷ ለጓደኛዋ መብት የምትቆም ሴት... ልጆቿን ሕልውናዋን ለመመለስ የምትታገል ሴት... ቤቷን ብቻ ሳይሆን አካባቢዋን አጽንቶ ለማቆም የምትታገል እናት" ማየታችን በሴት ደራሲያን የመጻፉ ትሩፋት መሆኑን ያስረዳል። የድራማው ደራሲያን ሴት መሆናቸው ወንዶች የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ሲጽፉ የሚያጎዱሉት ነገር ቁጭት እና እልህ አለባቸው የሚለው አንተነህ፣ ጠንካራ ሴት ገጸ ባህሪያትን በመሳል ረገድ እንደተዋጣላቸው ይመሰክራል። ደራሲያኑ እንዲሁም ዳይሬክተሯ ሴቶች መሆናቸው "ለሚገባቸው ሚና የሚታመኑ ጠንካራ ገጸ ባህሪያትን" ጠንካራ ሴቶች እንድናይ አድርጎናል ሲል ይገልጻል። የእረኛዬ ሴት ገጸ ባህሪያት ከእነርሱ ሕይወት ይልቅ የሚኖሩበት ማኅበረሰብ ሕልውና ያሳስባቸዋል።

በዋና ገጸ ባህሪይነት የተሳሉት ሴቶች ሁሉ ከራሳቸው በላይ ሰንደቅ ሆኖ የሚውለበለብ ዓላማ አላቸው። የእናና ገጸ ባህሪ ደግሞ ለሞቷ ሰበብ የሆነውን የጥቅም ፈላጊዎች ጠብ፣ ለመኖሪያ ቀዬዋ ነዋሪዎች ቀጣይ የጠብ ጥንስስ መነሻ እንዳይሆን በመመሸግ፣ መስዋዕት እስከመሆን ትደርሳለች። በእረኛዬ ድራማ ላይ የተሳተፉት ተዋንያንም ቢሆኑ ስምና ዝና ያላቸው፣ ክህሎትም ቢሆን ጠንቅቀው የተካኑ መሆናቸው ለተወዳጅነቱ አስተዋጽኦ ማድረጉን አንተነህ እና ሲራክ የሚስማሙበት ጉዳይ ነው። "ከእረኛዬ ድራማ የተመቸኝ አንድ ነገር ቢኖር ገጸ ባህሪ አሳሳሉ እና ተዋናይ መረጣው ነው" ይላል ሲራክ።

እረኛዬ ድራማ "የደርቢ ስብስብ ይመስላል" የሚለው ደግሞ አንተነህ ነው። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ በድራማው ላይ ወሳኝ ስፍራ የያዙት ተዋንያን ስምም ዝናም ያላቸው መሆናቸውን ነው። በእርግጥ በድራማው ላይ አዳዲስ ፊቶች የታዩ ቢሆንም እንደ አበበ ባልቻ፣ ሙሉዓለም ታደሰ፣ ድርብ ወርቅ ሠይፉ፣ ሳያት ደምሴ፣ ኩራባቸው ደነቀ፣ አማኑኤል ሐብታሙ፣ ቃልኪዳን ጥበቡ እንዲሁም ሠለሞን ቦጋለ ያሉ ተዋንያንን ማሳተፉ አድናቂዎቻቸውን ወደ ድራማው በመጥራት ረገድ አስተዋጽኦ ማድረጉን ይጠቅሳል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ተዋንያኑ የተወከሉበትን ገጸ ባህሪ በሚገባ መጫወታቸው፣ ተደራሲያንን ወደ ታሪኩ ጎትቶ በማስገባት ረገድ የላቀ ሚና እንደነበረው ያነሳል።

ብሔራዊ እርቅና መግባባት ለአገራችንና ለሕዝባችን ! አሜን ።

# ወቅታዊ

# ‹‹ስድርድር ቅድመ ሁኔታ ማብዛት የሰላምን መንገድ መዝጋት ነው››

**- አቶ ሙዑዝ ገብረ ህይወት**
**የሰላም አምባሳደር**

አስመረት ብስራት

በአገር ላይ ሰላም ለማስፈን፤ ጥላቻና ጦርነትን ለማቆም፤ ቂምና ቁርሾ እንዲሽር ማድረጊያ ዋናው መድሀኒት እርስ በእርስ መነጋገር ብቻ ነው። በባህላችንም ችግሮችን ለመፍታት የምንጠቀመው ሽምግልናን ነው። ጸብን በእርቅ ለመደምደም ከሽምግልና የበለጠ መፍትሄ አይኖርም። እናም ከሰዎች መካከል ተጽዕኖ ፈጣሪ፣ ታዋቂና አዋቂ፣ ተወዳጅ፣ አንደበተ ርዕቱእ፣ አስተዋይ ሰው ተመርጦ አንተም አንቺም ተው ባይ ሽማግሌ ይሰየማል። ይሄ ለግለሰቦች ለቡድኖች ብቻ ሳይሆን ለአገርም ያስፈልጋል። በአገርም ጉዳይ ላይ ይሰራል። አገራችን ዛሬ የገጠማትን የሰሜኑን ችግር ለመፍታትም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች የሚታዩትን አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ ለማጠናቀቅ የምክክር ኮሚሽን አቋቁማ ወደ ስራ ገብታለች። ለንግግር ዝግጁ መሆኗንም ደጋግማ አስታውቃለች።

በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ችግሮች ሲፈጠሩም ከጦርነት የሚያተርፍ የለምና ወደ ጦርነት አይገባ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ይፈቱ በሚል በተለያዩ ጊዜያት ሽማግሌዎች ወደ መቀሌ አቅንተዋል። የሰላም እናቶች የአገራችንን ሰንደቅ አላማ አንግበው፣ በእንባ እየተራጩ፣ በጉልበታቸው ጭምር ተንበርክከው ለሽምግልና አደባባይ ቆመዋል። ታዋቂና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ጭምር ሰላም ለህዝባችን ሰላም ለአገራችን ይሁን ብለው ሽምግልናው ተቀባይነት እንዲያገኝ ተማጽነዋል። ሆኖም ከሕወሓት በኩል የተገኘው ምላሽ ሽምግልናውን ያከበረ አልነበረም። መልዕክተኞችን በቅንነት የተቀበለ አልነበረም። በመሆኑም ወደ ተፈራው ጦርነት ተገባ።

ዛሬም ሕወሓት ለሰላም ዝግጁ መሆኑን እያሳየ አይደለም። በማንኛውም ቦታ በማንኛውም ሰዓትና ሁኔታ ለሰላም ለመነጋገር ዝግጁ መሆኑን መንግስት ቢያሳውቅም ሕወሓት ግን ለሰላም መንገዱ አደናቃፊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን እየደረደረ፤ ለሰላም የተዘረጉ እጆችን እየረጋገጠ ይገኛል። ከሰላም ይልቅ የጦርነት ጉሰማን ወደፊት በማምጣት ላይ ነው። ይሄ ለአገርም ለህዝቡም አይበጅም፤ አገር የምታድገው፣ የምታተርፈው ከጦርነት ሳይሆን ከሰላም ነውና የሰላም እጆች ከየትኛው ቦታዎች እንዲዘረጉ ያስፈልጋል። ሽምግልና ለሁሉም አትራፊ ነውና በአገራዊ የሽምግልና ባህላችን አገራችን ከመፍረስ፤ ህዝባችንን ከብተና እናትርፍ ሲሉ ሀሳባቸውን ያካፈሉን ለሽምግልና ትልቅ ቦታ የሚሰጡት እናም ለረጅም ጊዜ ሰውና ሰው በማስታረቅ ለሰላም ሰርቻለሁ። በሽምግልናም ረጅም አመት ቆይቻለሁ ያሉን የዛሬው «የወቅታዊ አምድ» እንግዳችን የሰላም አምባሳደሩ አቶ ሙዑዝ ገብረ ህይወት ናቸው።


ፎቶ-አዩብ ተፈሪ

የሰላም አምባሳደር፤ የሰብአዊ መብት እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ተሟጋቹ አቶ ሙዑዝ ገብረ ህይወት አሁንም በአገራችን ሰላም እንዲሰፍን እየተንቀሳቀሱ ያሉ ግለሰብ ናቸው። የተወለዱት በትግራይ ክልል ኢሮብ አሲምባ ተራራ በሚባለው አካባቢ ነው። በተወለዱበት ኢሮብ አካባቢ በነበረው ትምህርት ቤት እስከ ሰባተኛ ክፍለ ከተማሩ በኋላ ወደ አዲግራት በመሄድ እስከ አስረኛ ክፍል ተምረዋል። ከዛ የተለያዩ የትግራይ ክፍሎች በመዘዋወር አስራ ሁለተኛ ክፍልን አጠናቅቀዋል። የመንግስት ስራ ከያዙ በኋላ በማታ ትምህርት ክፍለጊዜ ተምረው ዲፕሎማ ብሎም በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ይዘዋል።

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ላይ በመመረጥ ከአርባ ሁለቱ አንዱ ቀጥሎም ከአስራ አራቱ አንዱ ለመሆን ችለው ነበር። በአገሪቱ ሰላም ለማምጣት አገራዊ መግባባት ላይ እንዲደርስ ምን ስራዎች መሰራት አለባቸው? በሕወሓትና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል ስላለው የእርቅ ሁኔታ፤ የትግራይ ህዝብ በወደፊት እጣ ፈንታ ላይ ምን መወሰን እንደሚገባውና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ቃለምልልስ አድርገናል፤ መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፤ በአገሪቱ ውስጥ ያለው ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ መንግስት ከሕወሓት ጋር የሰላም ምክክር ለማድረግ ኮሚሽን አዋቅሮ የሰላም ድርድሩ በየትኛውም ቦታና በማንኛውም ሰዓት ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ገልጿል፡፡ በሕወሓት በኩል ደግሞ የሚታየው ነገር ለሰላም ዝግጁ መሆን ሳይሆን ለሰላም ደንቃራ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን እያስቀመጡ ነው። ለድርድር የተወከሉት ሰዎችም አልተገለጹም፤ ሕወሓት ፍላጎት እውን ሰላምን መፈለግ ነው ብለው ያስባሉ ? ይህን ሁኔታ እንዴት አዩት?**

**አቶ ሙዑዝ፡-** የተወለድኩበት አካባቢ በርካታ የፖለቲካ ቡድኖች የሚንቀሳቀሱበት አካባቢ ነበር። በልጅነቴ ወደ ፖለቲካው እንድቀላቀል ምክንያት የሆነኝ ይህ ነው። በወቅቱ ሌላ ከሕወሓት ጋር የተፈጠረ በምስራቅ ትግራይ ጋሃት የሚባል አንድ ድርጅት ነበር። ያኔ የሁለቱ የፖለቲካ አስተሳሰብን ለማስታረቅ በሚል በሌሊት ወደ ካምፕ በመጠራት አጥፍተዋቸዋል። ይሄ የልጅነት ትዝታዬ ነው። ከዛም ኢህአፓ ጋር ለውይይት ተገናኝተው ተጠፋፍተዋል፡፡ ሌሎችንም የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለያየ ጊዜ በሀሳብ አለመግባባት ላይ ሲደረስ በርካታ እኩይ ተግባሮችን እየፈጸሙ አልፈውታል። ከዚህ ከቀደመው የሕወሓት ባህሪ ስንነሳ አሁንም ለሰላም ዝግጁ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል። ነገር ግን የሕወሓት የቀደመ ባህሪው ለእርቅ ያልተመቸ ቢሆንም፤ አሁን ግን ለህዝቡ ሲባል አንድ ወደ ሚያደርግ የውይይት ተግባር ውስጥ መግባት አለበት።

በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የሚያውቁት ኮሚቴ ተዋቅሮ በይፋ ሥራም ተጀምሯል፡፡ በኢትዮጵያ በኩል ሙሉ ዝግጁነት አለ፤ በሕወሓት በኩል ግን የሰላም ድርድሩን ተቀብለናል ቢሉም እስካሁን ኮሚቴ አላዋቀሩም፡፡ ለድርድሩም ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ እንዲጓተት የማድረግ ሥራ እየሠሩ ነው የሚገኙት።

ምንም እንኳን ሕወሓት በሽብር ተግባር ገብቶ አገርና ህዝብ እያመሰ ቢሆንም በክልሉ ምንም የማያውቁ ሰላማዊ ዜጎች አሉና ህዝቡ እንዳይራብ እርዳታና መድሀኒት እንዲደርስ እየተደረገ ነው። ይሄም ለነዋሪው በትክክል ይደርሰው ይሆን የሚል ስጋት አለኝ። ሆኖም ቀለቡ ለወገኖቻችንና ለቤተሰቦቻችን የሚደርስ ከሆነ መልካም ነበር። ነገር ግን የሚጓጓዘውን እርዳታ የህዝቡን ህይወት ከመታደግ ይልቅ ለእራሳቸው ሰራዊት ቀለብ እያዋሉት ነው።

እነዚህ ሰዎች ፈጣሪ ካልታረቃቸው በስተቀር በምንም አይነት ሁኔታ ሰላም አይፈልጉም። አሁንም ጦርነት እያወጁ ነው። ጦርነት ደግሞ በአፋቸው ነው እንጂ፤ ምንም ማድረግ እንደማይችሉ ቢገጥሙም እንደማያሸንፉ ያውቁታል። አቅማቸውን አሟጠዋል። እስከ ደብረ ብርሃን ደርሰው ብዙ የትግራይ ወጣትን አስፈጅተው ተመልሰዋል። በቀጣይም ከዚሁ ሽንፈታቸው ውጪ የሚያመጡት ድል አይኖርም። ይሄንን ተረድተው ለህዝቡ ሲሉ ግን አሁንም የሰላሙን መንገድ ቢመርጡ የሚል አስተያየት አለኝ። ጦርነት ህዝብን ጨራሽ ንብረት አውዳሚና አክሳሪ ነው። ነገም ቢሆን የትግራይ ህዝብ ጥያቄ ማንሳቱ አይቀርም፤ አሁንም የትግራይ እናቶች ልጆቻቸውን እየጠየቁ ናቸው። የሚሰጣቸው ምላሽ ግን በግንባር አሉ ከማለት ያለፈ አይደለም።

ለሰላም ድርድር ሲቀረብ ፊት ለፊት ተቀምጦ ይሄ ይደረግልን፤ ይሄ ይሁንልን የሚሉትን ሀሳብ ከሁለቱም ወገን መስማት ሲገባው በቅድሚያ በቅድመ ሁኔታ መንገዱን አጥሮ ለሰላም በራችን ክፍት ነው ማለት ተገቢ አይደለም። ለድርድር ቅድመ ሁኔታ ማብዛት የሰላምን መንገድ እንደመዝጋት የሚቆጠር ነው።

በትግራይ መድሃኒት የለም፤ ምግብ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፤ ቢገኝም ዋጋው የሚቀመስ አይደለም። በርካታ የስኳር፤ የደም ግፊት፣ የነርቭ ታማሚዎች ያለ መድሃኒት የማይኖሩ ሰዎች በመድሀኒት ማጣት እንደ ቅጠል እየረገፉ ነው። ለዚህም የትግራይ ህዝብ ይጠይቃል። መንግስት ሊስማማ እንኳን ቢችል ግፍ የተፈፀመባቸው የትግራይ ህዝቦች ለሕወሓት ጥያቄ ማቅረባቸው አይቀረም። አሁን ጦርነት የሚጎስሙት ተሰባብሮ የተጠጋገነ ሰራዊት ይዘው ነው።

ህዝቡ ያለበትን አስቸጋሪ ሁኔታ እንኳን በመሸሽ በጎረቤት ክልሎች አፋርና አማራ በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ኤርትራ እንዳይሰደድ እንደ ውሻ ከሁሉም እያናከሱት ይገኛሉ። ያም ሆኖ በየትኛው በኩል ያለው ህዝብ ችግሮችን ይረዳልና ስደተኞችን ከመቀበል አልተቆጠበም።

ሕወሓቶች በአሁኑ ወቅት ለሁለት ከመከፈላ ቸውም በላይ ህዝቡ የሚጠይቃቸውን ጥያቄ ላለመመለስ በቅድመ ሁኔታ ግንብ እያበጁ የሰላምን መንገድ እያደናቀፉ ነው። አሁን ልባቸውን መልሰው ለህዝቡ የሚጠቅመውን የሰላም አማራጭ መውሰድ አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፤- የሰላም አማራጭ በመንግስት በኩል ያስ ምንም ቅድመ ሁኔታ ቢቀረብም ሕወሓት ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀመጧል። እርሶም ሕወሓቶች የቀደመ ታሪካቸውም የሚያ ሳየው ሰላም ፈላጊ አለመሆናቸውን ነው ብለዋል፡፡ ድጋሚ ጦርነት ቢመጣ ለትግራይ ህዝብም ሆነ ለተቀረው የአገሪቱ ህዝብ ላይ ምን የሚፈጠር ይመስሎታል?**

**አቶ ሙዑዝ፡-** በአሁን ሰአት ሕወሓቶች በትግራይ የጦርነት ቅስቀሳ እያደረጉ ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው እዛው የተራረፉ ምሁራን፤ ሀኪሞች፤ ገበሬዎች የተወሰኑ ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የቀሩ ሰዎች አሉ፤ ከእነዚህ ውጪ ወጣቶቹን አስጨርሰዋል። እነዚህን የተቀሩትን ሰዎችና የተረፉትን የትግራይ ልጆችን ለማስጨረስ እየተዘጋጁ ነው።

ህዝቡ አሁን ላይ « የትግራይ ህዝብ ወደ ጨለማ እያስገባችሁን ነው፤ ከአሁን በኋላ ጦርነት አንፈልግም» በማለት የሕወሓትን የጦርነት ቅስቀሳ መቀበል አቁሟል። «በሚለዮኖች የሚቆጠሩ ወጣቶቻችንን ጨረሳችሁ ከእንግዲህ ልጆቻችንን አንሰጥም እያለ ነው»፡፡ ነገር ግን አሁን ችግር የሆኑት እነዚህ መሀል ከተማ የተደላደለ ኑሮ ላይ ተቀምጠው፤ ልጆቻቸውን ከጉያቸው ሳያወጡ በውጪ አገራት ያሉት ናቸው የድሃ ልጆችን የሚያስጨርሱት፤ እነሱ በምቾት እየኖሩ ድሃው የትግራይ ህዝብ ላይ የፖለቲካ ቁማር የሚጫወቱት ሀይ ባይ ያስፈልጋቸዋል።

እዛ ያለው ህዝብ በረሃብ አጥንትና ቆዳው ተጣብቆ፤ እናት ሞታ ልጅ የደረቀ ጡቷን እየጠባ፤ እናት ልጇቿ በውሃ እንዲሞላ ትንሽ ምግብ በብዙ ጨው እያበላቻቸው፤ ህይወት በመኖርና በመሞት መካከል ተቀምጦ ባለበት የጦርነት ነጋሪት መጎሰም የሚያዋጣ አይደለም። ይልቅ የሚሉትን ያህል ህዝቡን የሚወዱት ከሆነ ለትግራይ ህዝብ የሚያስቡለት ከሆነ የቀረበላቸውን የሰላም ጥሪ ተቀብለው ወደ ሰላም አደባባይ መቅረብ ይኖርባቸዋል። የኢትዮጵያ መንግስትም የያዘውን ሰላም ማስቀጠል ይኖርበታል። ካልሆነ ግን በተለይም የኢትዮጵያ አንድነት

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

የሚያሳስባቸው የትግራይ ተወላጆችን በመያዝ ትግራይን ነፃ ማውጣት ተገቢ ነው።

የትግራይ ህዝብም ሰቆቃው ይብቃን በማለት ይህን ቡድን ወደ ሰላም እንዲመጣ ግፊት ማድረግ ይኖርበታል። ያ ካልሆነ ግን ህዝቡ ራሱ የተያዘበትን ልጓም ፈቶ በገዛ አፉ በቃችሁ ሊላቸው ይገባል። የትግራይ ህዝብ ለበርካታ ሺህ ዓመታት በነፃነት ኢትዮጵያዊነቱን አምኖ ኖሯል፤ ወደፊትም ይኖራል። እነሱ ግን ፓርቲ ናቸውና ህዝብን አይወክሉም። የትግራይ ህዝብ ልጆቹን ለእኩይ ተግባራቸው መፈፀሚያ መስጠት የለበትም። ይህ ፕሮፖጋንዳቸው ያለቀ መሆኑን ምላሳቸው ብቻ መቅረቱን በመረዳት በቃ ማለት ይገባዋል።

**አዲስ ዘመን፤ ሕወሓት በሚያሰራጨው ፕሮፖጋንዳ የአለም አቀፍ ማህበረሰቡን እያሳሳቱ ነው፤ ሕወሓትን ለሚደግፉ የውጭ ኃይሎችና ለዲያስፖራ የትግራይ ተወላጆች ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልእክት ካለ ቢነግሩን?**

**አቶ ሙዑዝ፡-** ከላይ እንደገለፅኩት ውጪ አገር ያሉ ሰዎች በምቾት የሚኖሩ ናቸው፡፡ ድሃውን የትግራይ ህዝብ፣ እየተጎዳ ያለውን የትግራይ ማህበረሰብ በቅርበት አያውቁትም። በፊት ለለውጥ በሚል ለአስራ ሰባት አመታት የትግራይ ልጆች እንደ ቅጠል ረግፈዋል፤ በአሁኑ ጦርነትም አምስት አመት ውስጥ የበርካቶች የሰው ህይወት አልፏል። በሌሎች ክልሎች ያሉ የትግራይ ተወላጆች ከዚህ ቡድን ጋር እንቆጠር ይሆን በማለት እየኖሩ ያሉት በስጋት ነው።

በእርግጥ እነሱን የሚደግፉ አሉ፡፡ በተለያዩ የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ከሕወሓት ጎን የቆሙ ትግራዋይ ያልሆኑም በርካቶች ጥቅማቸው የተነካባቸው ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ‹‹ሕወሓት ይመጣል›› ብለው እቅፍ አበባ አዘጋጅተው የሚጠብቁ እንዳሉ ሁሉ፤ ከሌላው ብሔር ብሔረሰብ ጋር በሰላም ለመኖር የሚያስቡ ፍፁም ኢትየጵያዊነት በደማቸው ውስጥ ያሉ ትግራይዋይ በርካታ ሰዎችም እንዳሉ ግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል። ያለ ኢትዮጵያ መኖር የሚያስፈራ ህልም ያህል የሚያሰጋቸው፤ ከኢትዮጵያዊነት መነጠል ማለት የሞት ያህል የሚከብዳቸው ትግራዋይነት ኢትዮጵያዊነት የሚል ትርጉም ብቻ በልባቸው ይዘው ስለ አገር ሰላም ሲፀልዩ የሚኖሩ የአንድነት መምጫው ቀን የሚናፍቃቸው ብዙ የትግራይ ተወላጆች አሉ።

በውጭ አገራት ላሉ ለትግራይ ተወላጆች የማስተላልፈው መልእክት ‹‹ የሚሻላችሁ ብታርፉ ነው። ትግራይ ለብቻዋ አገር መሆን አትችልም። ዝም ብላችሁ የትግራይን ልጆች እያስጨረሳችሁ ነው፡፡ እያለቁ ያሉት የትግራይ ልጆች እንጂ አሜሪካ ያሉ የባለስልጣን ልጆች አይደሉም፡፡ እያለቁ ያሉት የትግራይ ልጆች እንጂ ጉያችሁ የደበቃችኋቸው ልጆቻችሁ አይደሉም። ›› ማለት እፈልጋለሁ፡፡

የፈለጉትን እየበሉ ሶፋ ላይ ቁጭ ብለው ሲያሻቸው የተንጣለለ አልጋ ላይ ተኝተው እየተናገሩ ነው፡፡ እዚህ ግን ደም ይፈሳል፤ እነሱ እየተንከባለሉ እየጠረጉ ያሉት የአሜሪካን አስፓልት ነው። ለስሙ ለኢትዮጵያ አንድነትና ክብር የተማሩ ናቸው፡፡ ለአገሪቱ አንድነት ማሰብ አለባቸው። በረሃብ በጦርነት ለሚያልቀው ለትግራይ ህዝብ ማሰብ አለባቸው።

እዛ ሆኖ የሚፎክረውና ትግራይ ውስጥ እየተጎዳ ያለው ማህበረሰብ አንድ አይደለም። የትግራይን የአንድነት ታሪክ ማበላሸት አይገባም። በርካቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው አገራቸውን እያገለገሉም ቢሆን በሁለት ቢላ የሚበሉ ነውረኞችም አሉ። ለሁሉም የሚበጀው አገር አንድ የምትሆንበትን መንገድ መከተል ነው። አገር ከመፍረስ ስትድን ሌሎች ችግሮችን ቀስ እያሉ መፍታት ይቻላል።

አንዳንዶች የአገርን ሀብት ለሽፍታ አሳልፎ የሚሰጡ መኖራቸው በጣም ይገርመኛል። አገር ለሚያፈርስ ኃይል እገዛ ማድረግ ያስተዛዝባል። እነዚህ እኩይ አላማ ይዘው የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ትግራይ ክልል እንጂ አገር መሆን እንደማትችል አውቀው ይሄንን አስተሳሰብ ከልቦናችሁ ውስጥ አውጡ እላለሁ።

በማንኛውም አካባቢ እና በውጪ አገር ለሚኖር ለትግራይ ተወላጅ ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት በትግራይ ክልል ሰላም የሚኖረው አንድም ሕወሓት ወደ እርቅ ሲመጣ ወይም ደግሞ ከምድረ ገፅ ሲጠፋ ነው። ይህ እንዲሆን በተቻለ መጠን ሕወሓት ላይ ግፊት ማድረግ ይገባል።

መናገር የቻለ፤ መደመጥ የሚገባው፤ በተለያዩ



መድረኮች ሊታይ የሚችል የትግራይ ተወላጅም ሆነ የትግራይ ህዝብ ተቆርቋሪ ሕወሓቶች ያለ ምንም ቅደመ ሁኔታ ወደ ሰላም ድርድሩ መቅረብ እንደሚገባቸው ግፊት ሊያደርግ ይገባል። ይህ የሰላም ማጣት ሁኔታ በረዘመ ቁጥር እየተከሰተ ያለው ሰብአዊ ጉዳት ከቁጥጥር ውጪ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ የግድ አንደኛ አማራጭ ሊሆን የሚገባው የሰላም መፍትሄ ነው እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- እርሶ የአገር ሽማግሌ ነኝ ብለዋል የሰላሙ መንገድ እንዴት ይሁን ይላሉ? እስኪ ምክሮዎትን ለግሱን፡ ፡**

**አቶ ሙዑዝ፡-** የሰላም ጉዳይ መነሳት የሚችለው ቅድሚያ ሰላም የሚል ህዝብ ሲኖር ነው። የሰላም ዋጋው ከምንም ጋር አይወዳደርም። የሰላም ዋጋ በምንም መስፈርት አይተመንም። የሰላምን ዋጋ የሚረዳው በጦርነት ውስጥ ያለ ህዝብ ብቻ ነው። ጦርነት ህዝብ ይጨርሳል፤ ጦርነት ኢኮኖሚ ያደቃል፤ ጦርነት የአገርን ኢኮኖሚ አቀጭጮ የአገርን እድገት ወደ ኋላ ይመልሳል። ጦርነት ያፈናቅላል፤ ህዝብን ከህዝብ ይለያያል። ጦርነት ካለ እንኳን ሀብት ንብረት የራስ አካልም የራስ ስለመሆኑ ዋስትና የለም።

የጦርነትን አስከፊነት በዘመናችን ያስተናገድናቸው በርካታ ጦርነቶች ካደረሱብን ጥፋቶች መገንዘብ ሳንችል አንቀርም። ጦርነት ለምድር ፍጥረታት ለሰዎች፣ ለእፅዋቱ እና ለእንስሳቱም በአጠቃላይ ለሁሉም አይጠቅምም፤ አውዳሚ ነው። በጦርነት የሚታመሱ የዓለም አገራትን አይተናል። ወደፍርስራሽነት ተለውጠዋል። ከሞት የተረፉት ዜጎቻቸው ለስደት ተዳርገዋል። እኛም ይሄንን እያስተናገድን ነው፤ ስለዚህ ከሌላውም ከራሳችንም ስህተት መማር አለብን።

ስለዚህ ሕወሓቶች አማራጫቸውን ሰላም ማድረግ አለባቸው። ሰላማዊ ቦታ ተቀምጠው የሚያጋግሉ አርፈው መቀመጥ አለባቸው፡፡ ከሰላም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር የለም። ኢትዮጵያ በክብር እንድትኖር፤ የለፋንበት፣ መስዋዕትነት የከፈልንበት የአባይ ግድባችን እንዲያልቅና አገራችን በእድገት ጎዳና እንድትጓዝ ለሁሉም ሰላም ያስፈልጋል።

አበባ ጉንጉን አዘጋጅተው፤ ሹርባ ተሰርተው፤ ከበሯቸውን ፀሃይ አስመትተው ሕወሓትን ለመቀበል የሚጠብቁ ሰላም ጠሎች ለሰላም ቅድሚያ ሰጥተው በእኩልነት አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ አንድንኖር

**የሰላም ማጣት ሁኔታ በረዘመ ቁጥር እየተከሰተ ያለው ሰብኣዊ ጉዳት ከቁጥጥር ውጪ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ የግድ አንደኛ አማራጭ ሊሆን የሚገባው የሰላም መፍትሄ ነው**

ለማድረግ የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል።

ሌላው የምክክር ኮሚሽን በተቻለው ፍጥነት ሰላም ወደ ማምጣቱ ስራ መግባት ይኖርበታል። ምክንያቱም በተለያየ ቦታ ሰው እያለቀ ይገኛል። ሕወሓት ደግሞ በጣም መጥፎ ነው። በቤኒሻንጉል፣ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በሱማሌና በተለያዩ አካባቢዎች ለሚፈጠሩት የሰላም መደፍረሶች የእነሱ እጅ እንዳለበት መገንዘብ ይኖርብናል። ስለዚህ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ርብርብ ማድረግ የሚገባው ይህን ቡድን ወደ ሰላም ማምጣት ላይ መሆን አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- የትግራይ ህዝብ ከኢትዮጵያ ዊነቱ ተለይቶ በአንድ ክልል አስተሳሰብ ውስጥ እንዲታጠር ለማድረግ እየሠሩ ይገኛሉ፤ እዚህ ላይ ምን አስተያየት አለዎት?**

**አቶ ሙዑዝ፡-** የሚፈልጉት ትግራይ ለብቻዋ አገር እንድትሆን ነው፡፡ በዚህም ብቻ ሳይበቃ ኢትዮጵያ እንድትገነጣጠልም ፍላጎት አላቸው። ቀደም ሲል ጅቡቲ፤ ኤርትራ የኛ አገር አካል ነበሩ፤ ሀምሳ አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሌላ አገር ሆኑ። ኃይልና ጥንካሬ የሚኖረው አብሮ በመሆን ነው። ትግራይም ከኢትዮጵያ ጋር በመሆን እንጂ ብቻዋን በመሆን አታተርፍም።

ትግራይ ተገንጥላ እንድትኖር ለሚፈልጉት ‹‹በምንም አይነት ትግራይ አትገነጠልም፤ ተገንጥላም አገር አትሆንም›› በማለት ላሳስብ እወዳለሁ። ሁለተኛ እነሱ እንደሚያስቡት ከወሎ መሬት ቆርሰው ከአፋር መሬት ቆርጠው፤ ከኤርትራ መሬት ቆርሰው አገር ለማድረግ ያስባሉ፤ ይሄንን ደግሞ በአስራ ዘጠኝ ሰማኒያ ሶስት ዓመተ ምህረት ኢትዮጵያ ከመምጣት እዛው ማድረግ ይችሉ ነበር። ምክንያቱም ትግራይ በእጃቸው ነበረች። አልቻሉም፤ አሁንም ይሄ እንደማይሆን ያውቁታል።

አሁን ሀሳባቸው በሁመራ በር ተከፍቶ በሱዳን በኩል ግብፅ ኢትዮጵያ መጥታ አገር እንድትረብሽ የማድረግ ሴራ ነው። እነዚህ ኢትዮጵያን አፈራርሰው ትግራይ ለብቻዋ ትኑር ሲሉ በርካታ ሤራዎችን እየሰሩ ናቸው። ለምሳሌ ባለፈው ሰዎች እስር ቤት ይገቡ በነበረ ጊዜ ያልሆነ ጥቆማ በመስጠት ሁሉም ትግራዋይ መንግስትን እንዲጠላ የማድረግ ሴራ ሲሠሩ ነበር። ሕወሓቶች ባልና ሚስት መካከል ገብተው እርስ በእርስ የሚያሰልሉ ናቸው። ለተንኮል ሲሆን እጃቸው ረጅም ነው።

የትግራይ ህዝብ ግን ሀሳቡን ሰብስቦ ለአሁኑም ሰላም፤ ለወደፊትም ከታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን ትግራዋይነት ኢትዮጵያዊነት መሆኑ ላይ ምንም አይነት ድርድር ውስጥ ሳይገባ ለሰላም በተቻለው አቅም ጥረት ማድረግ አለበት። እነዚህንም ኃይሎች ወደ ሰላም መድረክ እንዲመጡ ግፊት ማድረግ ይገባዋል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ሙዑዝ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## በኢትዮጵያ የተመረቱ መኪኖችን ለገበያ የማቅረብ እቅድ

**አንተነህ ቸሬ**

ለኢንዱስትሪው ዘርፍም ሆነ ለአጠቃላይ አገራዊ ምጣኔ ሀብቱ ተጨማሪ አቅም የሚፈጥሩ አምራቾች በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ወደሚገኙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እየገቡ በማምረት ስራ ላይ መሰማራታቸውን ቀጥለዋል፡፡ በዚህም ምርቶቹን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ እያስገኙም ናቸው፡፡

‹‹ኤልአውቶ ኢንጂነሪንግ›› (Elauto Engineering) የተሰኘ ኩባንያም ሰሞኑን እነዚህን አምራች ኢንዱስትሪዎች ተቀላቅሏል፡፡ ይህ ፋብሪካ ስራውን የጀመረው የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጠና እንዲሆን በተደረገው የድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ነው፡፡

የኩባንያው መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፡- ድርጅቱ ሰሞኑን ከተመረቀው የድሬዳዋው ፋብሪካ በተጨማሪ ዱከም፣ ኢስተርን ኢንዱስትሪ ዞን (Eastern Industry Zone) ውስጥም የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ አለው። ይህኛው ፋብሪካ መኪናዎችን መገጣጠም ከጀመረ ሁለት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ እስካሁን ድረስም አንድ ሺ መኪኖችን መገጣጠም ችሏል፡፡ ሰሞኑን የተመረቀውና በድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና (Dire Dawa Free Trade Zone) ውስጥ አሁን ስራ የጀመረው የኩባንያው ፋብሪካም ለቤትና ለመስሪያ ቤቶች አገልግሎት የሚውሉ አነስተኛ ተሽከርካሪዎችን የሚገጣጥም ነው፡፡

የ‹‹ኤልአውቶ ኢንጂነሪንግ›› ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ በቀለ አበበ እንደሚናገሩት፣ ኩባንያው የላዳ ታክሲዎችን የመቀየር ፕሮጀክትን ጨምሮ አነስተኛ ተሽከርካሪዎችን የመገጣጠም ተግባራትን ያከናውናል፡፡ የሚገጣጠሙት ተሽከርካሪዎች የከተሞችን ገፅታ በበጎ መልኩ በመቀየርና በስራ እድል ፈጠራ ረገድ ፋይዳ ያላቸው በመሆኑ መንግሥት ለፋብሪካው የሚያስፈልጉ የመኪና አካላት ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ፈቅዷል፡፡

ድሬዳዋ ላይ ስራ የጀመረው የ‹‹ኤልአውቶ ኢንጂነሪንግ›› ፋብሪካ በከፊል የተበተኑ መኪኖችን የሚገጣጥም ሲሆን፣ አጠቃላይ ኢንቨስትመንቱ 700 ሚሊዮን ብር ነው፡፡ የፋብሪካው የመጀመሪያ ምዕራፍ፣ የግብዓቶቹ (የሚገጣጥማቸውን ተሽከርካሪዎች)፣ የሥራ ማስኬጃ እና አጠቃላይ የሰው ኃይል ወጪን ጨምሮ፣ የ400 ሚሊዮን ብር ኢንቨስትመንት ነው፡፡

ፋብሪካው በመጀመሪያው ምዕራፍ በአንድ ፈረቃ ለ80 ሰዎች የስራ እድል ይፈጥራል፡፡ በሙሉ አቅሙ ማምረት ሲጀምርና ሙሉ የሎጂስቲክስ ሰንሰለቱ ተቀናጅቶ ወደ ስራ ሲገባ ደግሞ ለ300 ሰራተኞች ቋሚ የስራ እድል የሚፈጥር ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፋብሪካው በሚያመርታቸው ተሽከርካሪዎች አማካኝነት ተሽከርካሪዎችን ለሚገዙ ሰዎችና ለአሽከርካሪዎች፣ ለጥገና ባለሙያዎች፣ ለመለዋወጫ እቃዎች አቅራቢዎችና አከፋፋዮች እና ተዛማጅ ባለሙያዎችም ተጨማሪ የስራ እድሎችን ይፈጥራሉ፡፡

ፋብሪካው አሁን ባለው አቅም በቀን፣ በሦስት ፈረቃዎች 35 ተሽከርካሪዎችን የመግጠም አቅም አለው። በመጀመሪያው ምዕራፍ፣ ከአራት እስከ አምስት ወራት ባሉ ጊዜያት ሦስት ሺ መኪናዎችን ለማምረት እቅድ አለው። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ደግሞ ፋብሪካው በሙሉ አቅሙ እንዲያመርት ይደረጋል ተብሏል፡፡ በዚህም በከፊል የተበተኑ ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ የተበተኑ ተሽከርካሪዎችን ለማምረት የሚያስችለው የአምራችነት ቁመና ላይ ለማድረስ እንደታቀደም ተገልጿል፡፡

ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ ኩባንያው አሁን ስራ ከጀመረው ፋብሪካ ጋር በጥምረት የሚከናወን የማስፋፊያ ግንባታ አለው፡፡ በከፊል የተበተኑ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ የተበተኑ መኪኖችን ለመገጣጠም እንዲችል የብየዳ፣ የቀለምና የዝገት መከላከያ ቅብ ስራዎች የሚከናወኑባቸው ሶስት የመስሪያ ስፍራዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ስለሆነም አሁን ስራ ከጀመረው ፋብሪካ የሚወጣውን ምርት የተሟላ አድርጎ ለማጠናቀቅ የእነዚህ ስራዎች መሟላት አስፈላጊ በመሆኑ ስራ ከጀመረው ፋብሪካ ጎን ለጎን፤ በሙሉ አቅሙ ለማምረት የሚያስችሉትን ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

ፋብሪካው እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጊዜ



**ፋብሪካው አሁን ባለው አቅም በቀን፣ በሦስት ፈረቃዎች 35 ተሽከርካሪዎችን የመግጠም አቅም አለው**

ውስጥ የእሴት ሰንሰለቱ ላይ ብዙ ጭማሪ የሚኖራቸውን በኢትዮጵያ የተመረቱ (Made in Ethiopia) ተሽከርካሪዎችን ለማምረት አቅዶ እየሰራ እንደሚገኝ ነው አቶ በቀለ የሚናገሩት፡፡

የ‹‹ኤልአውቶ ኢንጂነሪንግ›› መኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ ስራውን የሚያከናውነው ባለፈው ሳምንት በተመረቀው የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ውስጥ ነው። ነፃ የንግድ ቀጠናን ማቋቋም የንግድ ዘርፍ ችግሮችን ለመቀነስና የኢንቨስትመንት ፍሰትን ለማሳደግ አወንታዊ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ነፃ የንግድ ቀጠናዎች የምርትና የሎጂስቲክስ ተግባራት ተቀናጅተው በቀልጣፋ አሰራር የሚከወኑባቸው ስፍራዎች በመሆናቸው ለኢንቨስትመንት ማደግ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ፡፡

ነፃ የንግድ ቀጠና ኢንቨስትመንትን የሚጨምር፣ አዳዲስ የሥራ ዕድሎች ለመፍጠር የሚያግዝ፣ ቢሮክራሲያዊ የአሰራር ውጣ ውረዶችን የሚቀንስ አማራጭ ነው፡፡ ይህ ቀጠና የንግድ እንቅፋቶች የሌሉበት እንዲሁም ቀረጥና ግብር ያነሰበት የንግድና ኢንቨስትመንት ማሳለጫ አካባቢ እንደሆነም ይገለፃል፡፡ በነፃ የንግድ ቀጠናዎች ውስጥ የሚተገበሩ ህጋዊ አሰራሮች በሌሎቹ አካባቢዎች ከሚተገበሩት ጋር ሲነፃፀሩ የላሉና አንፃራዊ ነፃነትን የሚያጎናጽፉ ናቸው፡፡

የ‹‹ኤልአውቶ ኢንጂነሪንግ›› መኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሞች ያስገኛል ተብሎ ተስፋ በተጣለበት የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ የነፃ ቀጠናው ትሩፋቶች ተጠቃሚ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ፋብሪካው ነፃ የንግድ ቀጠናው ውስጥ መገኘቱ ነፃ የንግድ ቀጠናው የሚስገኛቸው እድሎችና መልካም አጋጣሚዎች ሁሉ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ የሚናገሩት አቶ በቀለ፣ ‹‹ነፃ የንግድ ቀጠናው ውስጥ እንደሚገኝ አንድ አምራች ኢንዱስትሪ ምርቶቻችንን ለማሳደግ ያስችለናል፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ነጻ የንግድ ቀጠናው በከፊል የተበተኑ መኪናዎችን ከማምረት ሙሉ በሙሉ የተበተኑ ተሽከርካሪዎችን ወደማምረት ለመሸጋገር ያግዛል፡፡ በዚህም የምናመርታቸው ተሽከርካሪዎች ተኪ ምርቶች በመሆናቸው የውጭ ምንዛሬን ለማዳን እገዛ ያደርጋል፡፡ የሎጂስቲክስ ወጪያቸው የቀነሰ ተሽከርካሪዎችን ለአገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብም ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡ በብዙ የአፍሪካ አገራት በርካታ ተሽከርካሪዎችን የሚያመርቱ ብዙ ፋብሪካዎች ስለሌሉ ምርቶችን ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ለመላክ እድል ያስገኛል፤ ይህም ለውጭ ምንዛሬ ግኝት ተጨማሪ አቅም ይፈጥራል፡፡ ከፋብሪካው ምርቶች ከፊሉን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ከመንግሥት ጋር ስምምነት ተፈርሟል፡፡

የኢንቨስትመንት ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ የባለድርሻ አካላት ቅንጅትና ትብብር እንደሚያስፈልግ እሙን ነው፡፡ በዚህ ረገድ ‹‹ኤልአውቶ ኢንጂነሪንግ ፋብሪካ›› የድሬዳዋ ፋብሪካው እውን እንዲሆን እገዛ ያደረጉለት ተቋማት እንዳሉ የፋብሪካው ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ በቀለ ይገልፃሉ፡፡ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከሁለት ዓመታት በፊት፣ ኩባንያው ድሬዳዋ ላይ ስራውን ለመጀመር ሲዘጋጅ፣ ጀምሮ ብዙ ድጋፎችን እንዳደረገላቸው የሚያስረዱት አቶ በቀለ፤ ‹‹ተሽከርካሪዎችን ሙሉ በሙሉ ለማምረት ለተሽከርካሪው አካላት መስሪያ የሚሆኑ ግብዓቶችን ለማሟላት ለምናከናውናቸው ስራዎች እገዛ እያደረገልን ነው›› ብለዋል፡፡ የድሬዳዋ ከተማ ከንቲባ አቶ ከድር ጁሀርም በፋብሪካው ምርቃ ላይ የከተማ አስተዳደሩ በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ድጋፍ እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ‹‹የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የተከራየነው የማምረቻ ሼድ በኃይል አቅርቦትም ሆነ በሌሎች ግብዓቶች የተሟላ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር፣ ለፓርኩ የሚከፈለውን ኪራይ ለጊዜው በብር እንድንከፍልና ምርቶችን ለውጭ ገበያ አቅርበን የውጭ ምንዛሬ በምናገኝበት ጊዜ ኪራዩን በውጭ ምንዛሬ የምንከፍልበትን እድል በማመቻቸት ከፍተኛ ድጋፍ አድርጎልናል›› በማለት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽንም ከፍተኛ እገዛ እንዳደረገላቸው ይገልጻሉ፡፡

የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትም የምርት ደረጃዎችን በማውጣትና ፋብሪካው በደረጃው መሰረት እንዲተከል እገዛ እንዳደረጉላቸውና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም ለኩባንያው አስፈላጊ ድጋፎችን እንዳደረገ ተናግረዋል፡፡

የ‹‹ኤልአውቶ ኢንጂነሪንግ›› ኩባንያ የቀጣይ ጊዜ ዋነኛ እቅድና ትኩረት ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ የተመረቱ (Made in Ethiopia) ተሽከርካሪዎችን ለገበያ ማቅረብ እንደሚሆን አቶ በቀለ ይጠቁማሉ፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፣ በኢትዮጵያ የተመረቱ ተሽከርካሪዎችን አምርቶ ለገበያ ለማቅረብ የእሴት ጭማሪ ሰንሰለቱ የራሱ የሆነ አሰራር አለው፡፡ በኢትዮጵያ የተመረተ የሚል ማረጋገጫ ለማግኘት የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ደረጃዎችን ማሟላት ያስፈልጋል። ‹‹ኤልአውቶ ኢንጂነሪንግ›› ኩባንያም በኢትዮጵያ የተመረቱ ተሽከርካሪዎችን አምርቶ ለገበያ የማቅረብ እቅዱን ለማሳካት እሴት ጭማሪው (ተፈላጊው ደረጃ) ምን ያህል መሆን እንዳለበት ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

በኢንቨስትመንት ዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚገጥሟቸው ተግዳሮቶች ብዙ እንደሆኑ ተደጋግሞ ይገለፃል፡፡ ከእነዚህም መካከል በግብዓት (ጥሬ ዕቃ)፣ በሰው ኃይል፣ በቦታ፣ በኃይል፣ በፋይናንስና በውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ረገድ ያሉ ችግሮች በተደጋጋሚ ይጠቀሳሉ፡፡

‹‹ኤልአውቶ ኢንጂነሪንግ›› በስራው ሂደት ስላጋጠሙት ችግሮች አቶ በቀለ ሲያስረዱ፣ ‹‹በእኛ አገር በተለይ ለምርታቸው የውጭ ግብዓቶችን የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች የሚያጋጥማቸው ዋነኛው ችግር የውጭ ምንዛሬ እጥረት ነው፡፡ በእርግጥ እኛን በተመለከተ ታክሲዎችን ለመቀየር በተያዘው እቅድ መሰረት መንግሥት ለስራው የውጭ ምንዛሬ ስለፈቀደ ለጥቂት ጊዜ ያህል እፎይታ ይሰጠናል ብለን እናምናለን፡፡ በሌላ በኩል ኩባንያው ምርቶቹን ለውጭ ገበያዎችም ስለሚያቀርብ የማሽንና የጥሬ እቃ ፍላጎቶቹን ከምርቶቹ የውጭ ገበያ ሽያጭ በሚያገኘው ገቢ ለመሸፈን እየሰራ ነው›› ይላሉ፡፡

ካለፉት ሁለት ወራት ወዲህ መፍትሄ ያገኘ ቢሆንም፣ በሕግ ማዕቀፎች አለመስተካከል ምክንያት የታክሲ ቅያሬ ስራውን ለማሳለጥ የሚስችለው የቀረጥ ነፃ ውሳኔ በመዘግየቱ ኩባንያው ለሰባት ወራት ያህል መኪና ሳይገጣጥም መቆየቱና ለከፍተኛ የማከማቻ ኪራይ ወጪ መዳረጉ ሌላው ኩባንያውን ያጋጠመው ችግር እንደነበርም አቶ በቀለ ጠቅሰዋል። ስለሆነም እንዲህ ዓይነት የሕግ ማሻሻያ ተግባራት አምራቹን፣ የገዢውን እንዲሁም የአጠቃላይ ኢኮኖሚውን ታሳቢ ሊያደርጉ እንደሚገባም አቶ በቀለ ይናገራሉ፡፡ ‹‹እቃዎች ወደብ ላይ ተከማችተው እንዲቆዩ በመደረጋቸው በአገራዊ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ኢንዱስትሪውን በሚያግዙ የሕግ ማዕቀፎች ላይ ፈጣን ውሳኔ ማካሄድ ያስፈልጋል። ያን ማድረግ ከተቻለ በአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ ብቁና ትኩስ ኃይል ያላቸው ወጣቶች ስላሉ በስፋት ለማምረትና ለአገራዊ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ በጎ አስተዋፅኦ ማበርከት ይቻላል›› ይላሉ፡፡

ኢትዮጵያ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ እምቅ አቅም ያላት አገር ናት፡፡ አገሪቱ የአምራች ኃይል አቅም፣ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ፣ ሕጋዊ ማዕቀፎችና ለዘርፉ እድገት አወንታዊ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ሌሎች መልካም አጋጣሚዎችና አስቻይ ሁኔታዎች አሏት፡፡ በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ ሽግግር እውን ለማድረግ ባለፉት ዓመታት በርካታ ተግባራትን ብታከናውንም በዓይነትም ሆነ በብዛት በርካታ የዘርፉ ችግሮች፤ ከዘርፉ የሚፈለገውን ያህል ውጤት ማግኘት እንዳይቻል ስለማድረጋቸው በተደጋጋሚ ሲነገር ቆይቷል፡፡

የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጠና የዘርፉን ችግሮች ለማቃለል ከተተገበሩ የመፍትሄ አማራጮች መካከል አንዱ ተደርጎ ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ ነፃ የንግድ ቀጠናው አዳዲስና ሰፊ የሆኑ የሥራ እድሎችን ለመፍጠር፣ ተኪ ምርቶችን ለማምረት፣ የእውቀት ሽግግርን ለማሳደግ እንዲሁም ለአገር ውስጥ የቀረቡ ምርቶችን ለማከማቸትና የሎጀስቲክስ ወጪን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ይህም አገራዊ የሎጂስቲክስ ተወዳዳሪነትን ትርጉም ባለው መልኩ ሊለውጥ የሚችል በመሆኑ የአገሪቱን የገቢና ወጪ ንግድ ስርዓት ለማቀላጠፍ ያግዛል፡፡ አሰራሩ የሚያስገኛቸው ጥቅሞችና የሚፈጥራቸው እድሎች የምርት ወጪን በመቀነስ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋትም ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ጥቅሞች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለጥቅል አገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ዓይነተኛ ፋይዳ አላቸው፡፡

በነፃ የንግድ ቀጠናዎች ውስጥ የሚተገበሩ ህጋዊ አሰራሮች ቀለል ያሉና ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶችን የሚቀንሱ በመሆናቸው ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሰማራት የሚያደርጉትን ጥረት በአንፃራዊነት ቀላል ያደርጉላቸዋል፡፡ በነፃ የንግድ ቀጠናው ውስጥ ገብተው የሚሠሩ ባለሀብቶች፣ አስመጪና ላኪዎችም ሆኑ ድርጅቶች የልዩ ልዩ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ይህ ደግሞ የአገር ውስጥ እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይኖረዋል፡፡

ስለሆነም ሰሞኑን በቀጠናው ውስጥ ስራውን የጀመረውን ‹‹ኤልአውቶ ኢንጂነሪንግ››ን ጨምሮ ሌሎች አምራቾችም ነፃ የንግድ ቀጠናው የፈጠራቸውን እድሎች ተጠቅሞ፤ የወጪና ገቢ ንግዱን በማቀላጠፍና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ውጤታማነት በማሳደግና አገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገቱ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲያስመዘግብ ማድረግ ይገባል፡፡

# ጎሜ

# ነጋሪት ጉሰማው ስልማት ቢሆንሳ!

**ምሕረት ሞገስ**

ዝናብና ብርድ ያንገበገባቸው የመጠጥ ቤቱ ደንበኞች ከምሽት ሱሰኞቹ ውጭ ሁሉም ወደየቤቱ በመግባቱ ግሮሰሪው ጭር ብሏል። ብዙም መጠጥ ቤት የማያዘወትረው ገብረየስ ገብረአምላክ ግን ከስድስቱ ሱሰኛ ጠጪዎች ተነጥሎ ጥግ ይዞ የጠርሙሱን ቢራ ብርጭቆ ላይ እየቀዳ እየተጎነጨ ይተክዛል። አካሉ እዛ ቢሆንም በሃሳብ ርቆ ሔዷል። ክልሎችን አቋርጦ ነጉዷል። ጭንቀቱን ፊቱ ያሳብቅበታል። አይኑን ቡዝዝ አድርጎ አንዴ ወደመሬት ፤ አንዴ ወደጣሪያው ያያል።

አይኑ ቢፈጥም እየተመለከተ ግን አይደለም፤ እያስተዋለም አይደለም። እያሰበ ያለው ጨካኞቹ ጭራቆች የተረፉለትን ጥቂት ዘመዶችን ሳያስቀሩ ሁሉንም በጦርነት ለማስፈጀት ነጋሪት እየጎሰሙ መሆኑን በመስማቱ ተሳቅቋል። ‹‹የነብር ዓይን ከፍየል፤ የፍየል ዓይን ከቅጠል እንደሚባለው ማንኛውም ፍጡር በሚወደው ላይ ያተኩራል። እነርሱ ድሎት እና ስልጣን ይወዳሉ። ከስልጣን ልነቅንቃችሁ የሚል ካለ ይተናነቃሉ። ይህ መለያ ባህሪያቸው ነው። ሕዝብ እነርሱን ወገኔ ቢላቸውም እነርሱ ግን ወገኔ የሚሉት የሰው ልጅን እና ሕዝብን ሳይሆን ልክ እንደነበሩ የሁልጊዜ ሃሳባቸው ፍየልን ወይም ልክ እንደፍየሏ ቅጠልን ብቻ ነው። የቀን የሌሊት ሃሳባቸው ድሎታቸው እና ምቾታቸው እንዳይጓል ብቻ ነው። የስልጣን ጥማት፤ ሱስ ላይ ነው።

ምቾታቸውን ለማስጠበቅ የሰው ልጅ ደም እንደጎርፍ ቢወርድ አያስጨንቃቸውም። የቅርባቸው ወገኔ የሚላቸው ሕዝብ በሰላም እየኖረ እየጠገበም ባይሆን እየቀመሰ፤ እየተማረና እየታከመ እነርሱ በልክ ከሚኖሩ ወገን እያስፈጁ በድሎት ተንደላቀው የህልም እንጀራ ስለሆነው ስልጣናቸው የምቾት ፈረስ ቢጋልቡ ይመርጣሉ። ካብ የማይገባ ድንጋይ ሆነው ለምንም እንደማይስማማና እንደማይመች ለዚህ ሥራ ይውላል እንደማይባል ከንቱ የሚቆጠሩ መናኛዎች ቢሆኑም ተስፋ አይቆርጡም። ዛሬም እነርሱን የሚፈራ ወይም እነርሱን አሁንም የሚወድና የሚያከብር በመኖሩ አሁንም በምቾት ዓለም ውስጥ በመዋኘት ላይ ናቸው። ይሄ አሁን ላይ ማብቃት አለበት።›› አለ ገብረየስ ለራሱ። ዞር ዞር ብሎ ሲመለከት በቅርቡ ማንም የለም። ይሄ ሃሳቡን ከጭንቅላቱ አልፎ በአንደበቱ ስለመለፍለፍ ስላለመለፍለፉ እርግጠኛ አልነበረም። ነገር ግን ዋናው ነገር የሰማው የለምና ደስ አለው።

በድጋሚ ከብርጭቆው ላይ ቢራውን ተጎነጨ። እንደገና በሃሳብ ባሕር ውስጥ ሰጠመ። ‹‹ ከፎከረ ይሻላል የጠረጠረ፤ እንዲሁ ቸኩሎ እነርሱን ደግፎ ጦርነት ውስጥ ከመግባት እና ስሕተት ውስጥ ከመውደቅ ይልቅ ነገሮችን መርምሮና ተከታትሎ በእውነት ላይ መድረስ አስፈላጊ ነበር። ግን እንዴት ይህ ሁሉ ሕዝብ ሴራቸውን መረዳት አቃተው? ›› አለና መልስ የሌለው ጥያቄ ለራሱ አቀረበ።

ለደቂቃዎች ጭንቅላቱ ውስጥ የሚመላለሰውን ሃሳብ ለማስቆም አይኑን ጨፍኖ በረዥሙ ተነፈሰ። መልሶ አይኑን ገለጠ። በራሱ የፀጥታ ዓለም ውስጥ ለመስጠም ተመኘ። አልሆነለትም፤ ተመልሶ ከሰመመኑ ወጣ። እንደገና ማብሰልሰል ቀጠለ። ቢተውት የማይተው የነፍስ ስቃይ። ‹‹እነዚህ መጥፎዎች መጥፎ ጓደኛ አጉል ልምድ ያስተምራል፤ ብዙውን ሰው አሳስተው አጉል ልማድ አስተማሩት። ‹ተገፍተናል የግድ ስልጣን ይገባናል፤ መሬታችንን ልንነጠቅ ነው› ብለው ወጣቱን ብቻ ሳይሆን ሽማግሌውን ሳይቀር ሁሉንም አታለሉት፤ አሳሳቱት። ከጦጣ ጋር የዋለች ጉሬዛ እህል ፈጅታ ትገባለች፤ እነርሱን አምኖ የተከተላቸው እህል እንደፈጀችው ጉሬዛ እነርሱን የሰሙ ሁሉ አገር ፈጁ፤ ንብረት አወደሙ፤ እኛን አሳቀቁ፤ እንድንሸማቀቅ አደረጉ። በገዛ ወገኖቻችን ድርጊት አፈርን ተሳቀቅን።›› አለ ለራሱ በድጋሚ።

ገብረየስ የልቡን ለሰው መተንፈስ ቢያቅተው ለራሱ መንገር በመቻሉ ተደሰተ። ራሱን ሁለት አድርጎ ሙግት ውስጥ ገባ። ‹‹ እነዚህ ሰዎች ሕዝባችንን ይዘው ማጥፋት እና መጥፋት ከጀመሩ ሁለት ዓመት ሊመላ ሁለት ወር ብቻ ቀረ። በእነዚህ ዓመታት ስንቶች ሞተው ይሆን? ›› አለ። ‹‹በጦርነት ካለቀው ሌላ የልብ ሕመምተኛ፤ የደም ግፊት ወይም የስኳር መድሃኒት በቋሚነት በተከታታይ የሚወስዱ ስንት ሰዎች ሞተው ይሆን? ስንቱ ልጅ በመማሪያ ዕድሜው ሁለት ዓመት አቃጥሎ ይሆን? ስንቱ ከትግራይ ወደ ሌላ አካባቢ እሰደዳለሁ ብሎ በመንገድ ላይ ቀርቶ ይሆን? ይህንን ሁሉ የልጆቿን መከራ በማየት አንጀቷ ቆስሎ ሃዘን አድክሟት ወደ ጉድጓድ የገባች ስንት የትግራይ እናት ትኖር ይሆን?›› አለና አይኑን እንባ ሞላው። በወፍራም የእጁ ጣቶች የሁለቱንም አይኖቹን እንባ ሲያብስ ዘውዴ መታፈሪያ ወደ መጠጥ ቤቱ ገባ። ሰላምታ ተለዋወጡ።

> **ዘመናቸውን ሁሉ በጦርነት ለማሳለፍ የወሰኑ ይመስለኛል። ምናልባት ዓላማ ከተባለ ዓላማቸው ሊሆን የሚችለው ይህ ብቻ ነው። ያደሩበት ጭቃ ከጭድ ይሞቃል ከተለመደው መጥፎ የሰዎችን ሕይወት ከሚቀጥፍ ተግባር መውጣት ተስኗቸዋል። ጦርነት እንኳን ለሕዝቡ ለእነርሱም ቢሆን የማይመች ቢሆንም የሚመች መስሎ ታይቷቸዋል። ለእነሱ ግን ይሄ ልክ ነው የስልጣን ማቆያ መንገድ አይደል**

ዘውዴም ገብረየስም የመጠጥ ቤቱ በሰው አለመሞላት አስከፍቷቸዋል። በየምሽቱ ከሃምሳ እስከ ሰባ አንዳንዴም መቀመጫ እስኪጠፋ ስማኒያ እና ዘጠና ሰው የሚተራመስበት ቤት ጭር በማለቱ እንደተለመደው ተራርቆ ከመቀመጥ ይልቅ ተቀራርቦ በአንድ ጠረጴዛ ላይ እየጠጡ ለመወያየት ፈልገዋል። ገብረየስ በሃሳብ ራሱን ከራሱ ጋር መሞገቱ ደስታ ቢሰጠውም እየፈጠረበት ያለው የሃዘን ስሜት ማስጨነቅ ስለጀመረው ለመቀጠል አልፈለገም። ዘውዴን ‹‹ተቀመጥ›› አለው። ዘውዴ አልተግደረደረም። ብዙ ጊዜ ገብረየስ ከሩቅ ያየውና ቀርቦ ማነጋገር እየፈለገ ሳያናግረው ስለቀረ ዕድሉን ለመጠቀም ፈጠን ብሎ ‹‹እሺ እቀመጣለሁ። አንድ ጓደኛዬም ይመጣል›› ብሎ ጠረጴዛውን በመጋራት በቀኝ በኩል ያለውን ወንበር ይዞ አስተናጋጅ ጠራ። እርሱም ቢራውን አዞ ተቀመጠ።

ሁለቱም ተያዩ፤ ዘውዴ ‹‹ከዚህ ቤት ውጭ ሌላም ቦታ የምንተዋወቅ መሰለኝ።›› አለ። አዎ! በትክክል አለ፤ ገብረየስ። ዘውዴ ‹‹የክፍለ ከተማው ሊቀመንበር ነበርክ? ›› ሲል ጠየቀው። ገብረየስ አልዋሸም፤ በትክክል እንዳወቀው ተረድቷል። ‹‹ አዎ!›› አለ። ‹‹ታዲያ አሁን የት ነህ? ›› የሚል ጥያቄ አቀረበለት በአንድ የመንግስት ተቋም ውስጥ እየሠራ መሆኑን ገለፀና መወያየት ቀጠሉ። ቀስ በቀስ ሳያስቡት የሰሞኑን የፖለቲካ ወሬ ውስጥ ገቡ።

ዘውዴ ጥያቄ አቀረበ። ‹‹ ገብረየስ መቼም ትግራይ ዘመዶች አሉህ አይደል? ›› አለው። ገብረየስ ‹‹ይኑሩ አይኑሩ፤ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ አላውቅም እንጂ መኖርስ ነበሩኝ።›› አለ። ዘውዴ በየጊዜው ውስጡ የሚመላለሰውን እና ግልፅ ያልሆነለትን ጥያቄ ለገብረየስ አቀረበ። ‹‹ እነዚህ በየጊዜው ጦርነትን ብቻ እያሰቡ ያሉ ሰዎች ዓላማቸው ምን እንደሆነ ካወቅክ እባክህ ንገረኝ ? የሚፈልጉት ምንድን ነው? መቼም ኢትዮጵያን የመምራት ዓላማ ይኖራቸዋል ብዬ አላስብም ምክንያቱም ይሄ በድጋሚ ሊሆን የሚችል አይደለም። ይህንን እነርሱም ጠንቅቀው የሚያውቁት ይመስለኛል። ትግራይን እንደ አገር መመስረትም ከሆነ በጦርነት እና ሰው በማስፈጀት ሊሆን የሚችል አይደለም። በዛ ላይ እንዴት ሕዝቡስ ልጁን ይሰጣል? በእርግጥ እኔ ያልገባኝ ቡድኑን እና ሕዝቡን የገባው ሊሳካ የሚችል ዓላማ ይኖራቸው ይሆን?›› አለ።

ገብረየስ በረዥሙ ተነፈሰና ትንሽ ዝም አለ። ቢራውን በስሱ ተጎንጭቶ መልሶ በቀስታ ብርጭቆውን አስቀመጠ። ወንበሩ ላይ ተደላድሎ ተቀምጦ ‹‹ ዓላማ የላቸውም፤ ግባቸው ምን እንደሆነ እንኳን ሕዝቡ እነርሱ ራሳቸው እርግጠኞች አይደሉም። ካልሰጡ አይሰደቡ እንደሚባለው የትግራይ ሕዝብ ልጁን እየሰጠ እየተሰደበ የታሪክ ተወቃሽ እየሆነ ነው። ዓላማ የሌለው ዝግጅቱ ያላማረ ግብዣ በኋላ ማስነቀፉ አይቀርም። ዓላማ ለሌለው እና ዝግጅቱ ላላማረ ድግስ ነጋሪት ሲጎሰም ከኋላ ሆኖ የሚያጨበጭብ ቢኖርም ግብዣው ያልተሟላ በመሆኑ በኋላ ተደናቅፎ መውደቅ ብቻ ሳይሆን ያለምንም ትርፍ እንደውም በብዙ ኪሳራ የታሪክ ተወቃሽ ሆኖ መቅረት ይመጣል። ይሄንን ብዙ የትግራይ ተወላጅ ቢያውቅም እስከ አሁን ሙሉ ለሙሉ ጦርነቱን ማስቆም አልተቻለም።

እባክሽ ያሏት ጎረቤት ትሆን እመቤት እንደሚባለው አንዳንድ ሰው ሲያከብሩት ኩራት ይሰማዋል። ሙቱልኝ ተሰውልኝ ይላል። የቡድኑም ነገር ተመሳሳይ ነው። ህዝቡን በሙሉ ለእኔ ምቾት ስትሉ ዋጋ ክፈሉ እያለ ነው። ህዝቡም እያንዳንዱ ሰው ዋጋ እየከፈለ ነው። እስከ መሰዋዕትነት በመድረስ ብዙዎች ዋጋ ከፍለዋል። አንዳንዱ ራሱ ሲሞት፣ አንዳንዱ አባቱ፣ አንዳንዱ ወንድም እህቱ አንዳንዱ እናቱ ሳይቀር በእነርሱ ፍላጎት በተጀመረ ጦርነት ምክንያት ሞተውበታል።

ቡድኑ ትግራዋይ በከፋ ረሃብና እርዛት ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓል። ከእርዛት ከፉ ሱሪ ማጣት ከአካላት ከፉ የሆድ ጅማት እንደሚባለው ቡድኑ ትግራዮች ሱሪ ታጥቀው እነርሱን እንዳያስቆሙ ከፉ እርዛት እንዲያጋጥማቸው አድርገዋል። የትግራይ አካል ነን ቢሉም የቡድኑ አባላት በምንም መልኩ ከትግራይ ሕዝብ አይበልጡም። የትግራይ አካል ቢሆኑም ክፉ ጅማት ሆነው ከሕዝቡ ተነጥለው ከመውጣት ይልቅ ትግራይን ለማፍረስ ታጥቀው ተነስተዋል።

ዘመናቸውን ሁሉ በጦርነት ለማሳለፍ የወሰኑ ይመስለኛል። ምናልባት ዓላማ ከተባለ ዓላማቸው ሊሆን የሚችለው ይህ ብቻ ነው። ያደሩበት ጭቃ ከጭድ ይሞቃል ከተለመደው መጥፎ የሰዎችን ሕይወት ከሚቀጥፍ ተግባር መውጣት ተስኗቸዋል። ጦርነት እንኳን ለሕዝቡ ለእነርሱም ቢሆን የማይመች ቢሆንም የሚመች መስሎ ታይቷቸዋል። ለእነሱ ግን ይሄ ልክ ነው የስልጣን ማቆያ መንገድ አይደል። ወንድሜ እንግዲህ እነዚህን ሰዎች ምን ማድረግ ይቻላል? ›› ሲል ገብረየስ ዘውዴ መታፈሪያ የጠየቀውን ጥያቄ በጥያቄ መለሰለት።

ዘውዴ በበኩሉ ‹‹ያደፈ በእንዶድ ይፀዳል፤ የጎለደፈም በሞረድ ይሞረዳል። ጭቃ ውስጥ ገብቶ በቅዝቃዜ ከመታገል፤ ይቅርታ ጠይቆ ፍርድን መጠበቅ እና ጥፋትን መቀነስ ሲገባ በጥፋት ላይ ጥፋት መደራረብ እንደልማድ መወሰዱ በምንም መልኩ የሚደገፍ አይደለም። እኛ በሃይማኖትም ሆነ በስነልቦና በብዙ መልኩ እርስ በእርስ የተጋመድን የማንለያይ ሆነን ስለምን በጦርነት ለመጠፋፋት መሳሪያ እንደምንሆን ግልፅ አይደለም። በእርግጥም ማንም ቢሆን የጦርነቱን ዓላማ የተረዳ አለ የሚል እምነት የለኝም። መፍትሔው ግን ምንም ሆነ ምን ጦርነት እንዳይቀጥል የተቻለውን ሁሉ ማድረግ ነው።›› አለው።

በዚህ ጊዜ ገብረየስ አቀረቀረ፤ ቀና ብሎ ብርጭቆውን አነሳና ቢራውን ከጠርሙሱ ወደ ብርጭቆ አንጠፍጥፎ፤ እያገላበጠ በብርጭቆ የተገኘችውን ቢራ ጨልጦ ጠጣ። መሃላቸው ዝምታ ሰፈነ። ዘውዴ ገብረየስ የሚለውን ለመስማት ጓጉቷል። ገብረየስ ውስጡ ጭንቀት በመኖሩ አካሉ ላይ የሚንበለበለውን እሳት ለማብረድ በረዥሙ ተንፍሶ ‹‹ምናለበት ጦርነትን ማስቆም አሁን እኔና አንተ እንደምንነጋገረው ቀላል ቢሆን ደስ ይለኝ ነበር። ችግሩ ጦርነቱ መቆም የሚችለው በእኔ እና በአንተ ፍላጎት ሳይሆን፤ በሌሎች በሰው ሕይወት መጥፋት በሚደሰቱ ሰዎች ውሳኔ ነው። እርግጥ ቢዘገይም አሁንም ጦርነት ባይቀጥል የወደፊቱን ጥፋት የሚቀንስ በመሆኑ ተፈላጊ ነው። ግን በምን መንገድ ይቁም ከተባለ መልሱን መመለስ ከኔ አቅም በላይ ነው።›› ሲል ተነፈሰ።

ዘውዴ መታፈሪያ ወደ ደጃፍ እየተመለከተ ‹‹ ወዳጄ መጣ። እንደውም መልሱን እርሱ ይሰጠናል።›› በማለት ሰላምታ እየሰጠው መሳቅ ጀመረ። ተሰማ በበኩሉ ነገሩን ስላላወቀ ‹‹በቅድሚያ ጉዳዩ ይብራራልኝ።›› አለ። ዘውዴ ገብረየስን እና ተሰማ መንግስቴን አስተዋውቆ ‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ ጦርነት እንዳይኖር ምን ይሠራ እያልን እየተጠያየቅን ነበር።›› አለው። ተሰማ ‹‹ እንግዲህ መንግስት ማንም ቢሆን ማን መወያየት እና መነጋገር እንችላለን። ከጦርነት ይልቅ ልማት ላይ እንረባረብ ለጦርነት ከበሮ ከመደለቅ ነጋሪት ከመጎሰም ይልቅ ፊታችንን ወደ ልማት እናዙር እያለ ነው። ነገር ግን ጦርነትን ስራ የስልጣን ማቆያ ያደረጉ ሰዎች ደግሞ ከልማዳቸው መውጣት አቅቷቸዋል። ስለዚህ መፍትሔው መንግስት ጋር ወይም ጦርነትን ልማዱ ያደረገ ቡድን ጋር ሳይሆን ሕዝብ ጋር ነው። ጦርነት የለመዱትን ‹ይህንን ክፉ ልማዳችሁን ተው፤ በቃን፤ ይብቃችሁ፤ ከዚህ በላይ መሞት አንፈልግም› ማለት አለበት ካለበለዚያ ሌላ መፍትሔ ማግኘት በጣም አዳጋች ነው።›› አለ። ሶስቱም በዚህ ሃሳብ ቢስማሙም መቼ እና እንዴት ይህ ሊባል ይችላል የሚለው ላይ መግባባት ሲያቅታቸው ገብረየስ ‹‹ጉዳዩ ለይደር ይቆይ ከመጣሁ ስለቆየሁ ወደ ቤቴ ልሒድ።›› ብሎ ወጣ። እሱ ከግሮሰሪው ወጣ እንጂ ሀሳቡ ግን በግሮሰሪው ቤት ተጠንስሶ አብሮት ቀጠለ። ገና በእንቅልፍ ዓለም ጭምር ይብላላል። ምክንያቱም ሰላም አገር ላይ ካልሰፈነ የአእምሮም ሰላም የለማ፤ የሚያልቀው ህዝብ ነዋ። እና ምን እረፍት አለ የሚቆይ የሚቀመጥ ሀሳብ የለም። ሀሳብ ሰብሰብ ብሎ፤ አእምሮ አርፎና እረፍት አግኝቶ ሀሴት የሚያገኘው ጦርነቱ በልማት ሲተካ ነው። ሰው ሆዱ ብቻ ሳይሆን አእምሮም በልቶና ጠግቦ ሲያድር ነው። ካልሆነ ያው በሀሳብ መዋዠቅ፤ በቃ በሀሳብ መዋተት ነዋ !።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# አሸንዳ፣ ሻደይ፣ አሸንድዬ፣ ሶለል፣ ከሴ አጨዳ





ዋለልኝ አየለ

በሰሜን ኢትዮጵያ የልጃገረዶች ጨዋታዎች ናቸው። ከልዩነታቸው አንድነታቸው ይበልጣል። ልዩነታቸው በየአካባቢው የአለባበስና የአዘፋፈን ባህል ይከወናል። አንዳንድ የሥርዓተ ክዋኔ ልዩነቶችም አሏቸው። አንድነታቸው ሁሉም የልጃገረዶች ጨዋታዎች ናቸው። ሁሉም በነሐሴ ወር የሚከወኑ ናቸው። በሁሉም ጨዋታዎች ዘንድ ልጃገረዶች ነፃነት አላቸው፤ ልጃገረዶች በጉጉት ይጠብቁታል።

እነዚህ ጨዋታዎች በትግራይ ክልል አሸንዳ፣ በአማራ ክልል ደግሞ፤ ሻደይ በዋግህምራ፣ አሸንድዬ በላስታ ላሊበላ፣ ሶለል በራያና ቆቦ፣ ከሴ አጨዳ ደግሞ በጎጃም እና የጎጃም አዋሳኝ በሆነው ሰሜን ሸዋ ደራ አካባቢዎች ይከበራሉ። ምናልባት ‹‹ከሴ አጨዳ›› የሚባለው የልጃገረዶች በዓል ብዙም የመገናኛ ብዙኃን ላይ ስለማይደጋገም በጥቂቱ እናስተዋውቃችሁ።

ይህ የልጃገረዶች በዓል በብዛት በምሥራቅ ጎጃም እና ከምሥራቅ ጎጃም ጋር በሚዋሰነው የሰሜን ሸዋ አካባቢ እና በደቡብ ወሎ ‹‹ከሴ አጨዳ›› ተብሎ ይጠራል። ከሴ ጥሩ መዓዛ ያለው የተክል አይነት ሲሆን ነሐሴ 16 ቀን ልጃገረዶች ይህን ተክል አጭደው በየመንደሩ እየዞሩ ይጥላሉ። ከሴ አጨዳ የተባለው በዕለቱ ልጃገረዶች ከሴ የተባለውን ተክል ስለሚያጭዱ ነው። ይህን ያጨዱትን ጥሩ መዓዛ ያለው ተክል (ከሴ) በዕለቱ በየቤቱ እየዞሩ ይጥላሉ። እናቶችና አባቶች ይመርቋቸዋል። ይህን ከሴ በየመንደሩ እየጣሉ ከጨረሱ በኋላ አንድ ቦታ ሆነው ይጫወታሉ። የሚጫወቱበት ቦታ በየዓመቱ ተመሳሳይ ነው። ቦታውም የከሴ አጨዳ መጫወቻ መሆኑ ይታወቃል። የጨዋታው መጀመሪያ ያ ቦታ ይሁን እንጂ ጨዋታው ግን አንድ ቦታ ብቻ አይሆንም፤ በተለይም መሸት ሲል ወደ መንደር እየተጠጉ ሲሄዱ ቦታ ሊቀያይሩ ይችላሉ። ሥርዓተ ክዋኔው ሰፊ ማብራሪያ ስለሚፈልግ ለዛሬው ሌሎች በዓላትን ጨምረን የቃል ግጥሞች ላይ ብቻ ነው የምናተኩር። ለቃል ግጥሞች እና ለአንዳንድ ማብራሪያዎች የዝቋላ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ያሳተመውን መጽሔት በምንጭነት ተጠቅመናል።

ስለከሴ አጨዳ ልጃገረዶቹ እንዲህ እያሉ ይጫወታሉ።

**ከሴ አጨዳ መጣ፤ አይምጣ ይመለስ**
**እንቁጣጣሽ መጣ፤ አይምጣ ይመለስ**
**መስቀልም መጣ፤ አይምጣ ይመለስ**
**ቆንጆቹ አልቀዋል ጨፌውም ይታረስ!**

‹‹ቆንጆ›› ማለት በጎጃም አካባቢ ያላገባች (ልጃገረድ) ማለት ነው። የዚህ ቃል ግጥም መልዕክት፤ ቆንጆቹ በልጅነታቸው እየተዳሩ ተቸግረናል፤ እነ ከሴ አጨዳ፣ እንቁጣጣሽና መስቀል ሲመጡ ብዙ ቆንጆ በሌለበት ማክበር አይቻልም፤ ለጨዋታ የሚሆነው አበባና ጨፌ እየባከነ ነው፤ ስለዚህ ካልተጫወትንበት ይታረስ የሚል እልህ የሚመስል መልዕክት ነው። ልጃገረዶቹ በዘፈኖቻቸው መልዕክት ያለዕድሜ ጋብቻን እየተቃወሙ ነው ማለት ነው።

**አበባው አበበ ንቡም ገባልሺ**
**እንግዲህ የአገር ልጅ ማር ትበያለሺ**

የሰምና ወርቅ ባህሪ አለው። በአበባ ወቅት ንብ በብዛት ይታያል። ንብ በዛ ማለት ያው ማር ይበላል ማለት ነው። በሌላ በኩል ግን እነዚህ ልጃገረዶች ከፍቅረኞቻቸው ጋር የሚገናኙት በእንዲህ አይነት ጨዋታዎች ነው። በሰኔ እና በሐምሌ ወራት አበባና ንብ አይኖርም፤ ልጃገረዶቹም ሥራ ስለሆነ አይገናኙም። ከነሐሴ ወር አጋማሽ ጀምሮ ግን አበባ ያብባል፤ እነዚህ የልጃገረዶች በዓላትም ይመጣሉ። በእነዚህ በዓላት ሥራ የለም፤ ነፃነት ይሰጣቸዋል። አበባ ማበብ ሲጀምር እነዚህ በዓላት የሚመጡበት ነውና ፍቅረኛቸውን ይናፍቃሉ። ፍቅረኛ ተገኘ ማለት ማር ተበላ ማለት ነው።

ወደ ሌሎች የሰሜን ኢትዮጵያ ጨዋታዎች ስንሄድ፤ የአሸንድዬ ባህላዊ ጨዋታ መገለጫ የሆነው አሸንዳ፤ እንደ ቄጤማ ረጅምና እንደ ቅጠል ሰፋ ያለ ነው። ቁመቱ ከ80 እስከ 90 ሴንቲ ሜትር ይሆናል። ለምለም ነው። በወገብ እንደ ሽብሽቦ (የልብስ አይነት) ሆኖ ይታሰርና ከግጥሙና ከዜማው ጋራ ተዋሕዶ በዳሌያቸው ላይ ይዞራል፤ ይሽከረከራል። መሽከርከር ካልቻለች እንዲህ እያሉም ወረፍ ያደርጓታል።

**እቴ አይዞርም ወገብሽ**
**ባቄላን ነው ቀለብሽ**

ተቀባዮቹ ደግሞ የመሽከርከር ችሎታቸውን ለመግለጽ እንዲህ ይላሉ።

**አሸንዳዬ አሸንዳ አበባ**
**እርግፍ እርግፍ እንደወለባ**

አሸንድዬ የክረምቱን (ጨለማው፣ ጭቃው፣ ጎርፉ፣ ዶፉ፣ ብርዱ) መውጣትና የበጋውን (ብርሃኑ፣ ፀሐዩ፣ የወንዙ ጥራት፣ የአዝዕርቱ ማሸት፣ የአበባው ማበብ) መግባት ምክንያት በማድረግ ዕንቁጣጣሽ ሁለት ሳምንት ሲቀረው ጀምሮ አዲሱን ዘመን በደስታና በሐሤት ለመቀበል በብሩህ ተስፋ ውስጥ ሆነው የሚጫወቱት ነው።

**አሸንዳዬ አሸንዳ አበባ**
**እርግፍ እርግፍ እንደወለባ**
**አደይ አበባ አደይ አበባ**
**ነሽ ውባ ውባ**
**አደይቱ መስከረሚቱ**
**መውደድ እንደሴሲቱ**

እያሉ አበባንና መስከረምን ሲያነሱና ሲያወድሱ፣ የታጠቁትንም ቅጠል ሲያወሱ እውነትም ከአዲሱ ዘመንና ከዕንቁጣጣሽ በዓል ጋር ግንኙነት እንደነበረው ያሳያል።

እነዚህ የልጃገረዶች ጨዋታዎች ሃይማኖታዊ ይዘትም አላቸው። በሃይማኖታዊ ይዘቱ ከሊቀ ነቢያት ሙሴ ጋር ያያይዙታል። ከሕግ ባለቤት ከልዑል እግዚአብሔር ሕግን ተቀብሎ ያስተላለፈው ሙሴ እስራኤላውያን በግብጽ በባርነት በነበሩበት ጊዜ ዕብራዊት እናቱ በዚያ ስለወለደችውና ማንኛውም ወንድ ዕብራዊ ሲወለድ እንዲገደል በግብጽ አዋጅ መውጣቱ እናቱ እግዚአብሔር እንዳደረገ ያድርገው ብላ ከዓባይ ወንዝ ዳርቻ በቄጤማ ውስጥ አስቀምጣዋለች። ኋላ የፈርዖን ልጅ ገላዋን ልትታጠብ ወደ ወንዝ (ዓባይ) ስትሄድ ደንገጡሯን ልካ አውጥታ በእናቱ ሞግዚትነት አሳድጋው እስራኤልን ከተገዙበት የ430 ዓመት ባርነት ነጻ አውጥቷቸዋል። ለዚህም ይመስላል በልጃገረዶች ዘፈን ውስጥ ይሄ ይገኛል።

**አሸንድዬ አሸንዳ ሙሴ**
**ፍስስ በይ በቀሚሴ**

የሚለው ባህላዊ ጨዋታ መነሻው ልጃገረዶች በጀርባቸው አስረው ከሚወዘውዙት ቄጤማ መሰል ሳር ስያሜ የመጣ ሲሆን ይህ ሳር(ቅጠል) ሙሴ የተጣለበትን ቄጤማ ስያሜ ወስዶ አሸንዳ ሙሴ ተብሎ ይጠራል፤ በጨዋታቻው ውስጥ አበ ሙሴ፣ ወርቃበ ሙሴ እያሉ ደጋግመው ማንሳታቸው ለዚህ ማስረጃ ነው ይላሉ።

ነሐሴ 16 ልጃገረዶች በየአጥቢያቸው በቡድን ይሰባሰቡና በመጀመሪያ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ። ይሄ ጨዋታ በተለይም ከሴ አጨዳ የሚባለው በዓል በሚከበርባቸው አካባቢዎች ሲሆን እነ አሸንዳ፣ ሻደይ፣ አሸንድዬና ሶለል ከነሐሴ 16 በፊትና በኋላም ይከበራሉ። ነሐሴ 16 ቤተ ክርስቲያኑን ሦስት ጊዜ እየዞሩ በመዘመር እዚህ ላደረሳቸው አምላክ ምስጋና ያቀርባሉ። ዝማሬያቸውም እንደሚሄዱበት ቤተ ክርስቲያን ሊለያይ ይችላል። ይሄ ማለት መድኃኔዓለም፣ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ማርያም... ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው። ለምሳሌ የሄዱበት ቤተክርስቲያን መድኃኔዓለም ከሆነ

**እስከ በስመ አብ ብዬ ልጀምር ሰላምታ**
**ስመድኃኔዓለም ስአዳኙ ጌታ**
**ውስጡ አረንጓዴ ነው የሚያምር**
**የመድኃኔዓለም ደብር**

ይላሉ። ሌሎች ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ጨዋታዎችንም ይጫወታሉ። በተለይም በላሊበላ አካባቢ በሶለል ጨዋታ እንዲህ ይላሉ።

**አሸበረቀች ጨረቃ ተወረወረች ኮከብ**
**በጊዮርጊስ ጫንቃ በአማኑኤል ክበብ**
**በሚካኤል ጫንቃ በገብርኤል ክበብ**
**በእመብርሃን ጫንቃ በሲባኖስ ክበብ**

እያሉ የመዝሙር ይዘት ያለው የባህል ጨዋታ ይጫወታሉ። የበዓሉና የደስታቸው መግለጫ ከሆነው አሸንዳም በየቤተክርስቲያኑ ደጃፍ ላይ ያስራሉ፤ ይጥላሉ፤ ይጎዘጉዛሉ። ከቤተክርስቲያን መልስም በቆየው ዘመን መጀመሪያ ታላላቅ ከሚባሉና ከሹመኞች ቤት በመሄድ የደስታ መግለጫቸውን ያሰማሉ። ከዚያ ወደ ሌላው ሰው ቤት ያመራሉ። በሳምንቱ ቀናት ውስጥ ያደርሳሉ፤ እስከ ዕንቁጣጣሽ ድረስም የሚቆዩ አሉ። ሀብታም ነው፤ ድሃ ነው ብለው የሚተውት ሰው አይኖርም። የመንገድ (የጉዞ) ዜማም አላቸው፤ አጀባዬ ይባላል።

**አጀባ ሆኗል ጅብጀባ አጀባ ሆኗል ፈረሱ**
**በየት ልንገባ ወዴት ነው እሱ**

እያሉ በመቀባበል ካዜሙና ዜማውን ተከትለው እርግፍ እርግፍ እያሉ ወደ ላይም እየዘለሉ ከጨፈሩ በኋላ ካባወራው ወይም እማወራዋ ጋ ሲደርሱ ከግቢው ውጭ ሆነው እንዲህ ይላሉ።

**አስገባኝ በረኛ**
**አስገባኝ ከልካይ**
**እመቤቴን ሳይ**
**ጌታው አሱ ወይ አሱ ወይ**
**አሱ እንጂ ግቡ ይሳሉ እንጂ**
**አሱ እንጂ፣ ተዘንብሷል ጠጂ**

እያሉ በትህትና መልክ አወድሰውና አስፈቅደው በር ካስከፈቱ በኋላ ወደ ግቢው ይገባሉ። ከዚያም በጥዑም ዜማ በሰናይ ቃና ይጫወታሉ። የጨዋታቸው ስንኞች ፍቅርን፣ ጀግንነትን፣ የሥራ ክቡርነትን፣ ሙያን፣ ውበትን. . . የሚያወድሱበት፣ በተለያየ ጣዕመ ዝማሬ የሚያሸበሽቡበት ነው። ባለቤቱ ሞቅ ያለ ስጦታ እንዲያበረክትላቸው ሲገፋፉትም ደግሞ እንዲህ ይሉታል።

**ጌታው ስም ይሻል ስም ይሻል**
**አንድ ብር እንኳ ጠፍቶ ያመሻል**
**በሬ ከጋጡ ሞቶ ያመሻል**

እያሉ አመስግነውና ተመስግነው፣ ተሸልመው ከቤት ይወጣሉ። ወደ ሌላ ቤት ይሄዳሉ። ሽልማቱ ቀደም ሲል እህል፣ ዳቦ፣ ጠላ፣ እንጀራ፣ በግ፣ ፍየል፣ እርጎ ነበር፤ ይህ አሁንም በገጠሩ ይኖራል። በከተማው ግን እንየአቅሙ በብር ነው። ምርቃቱንም ቢሆን እንደቀላል ነገር አይቆጥሩትም። በተለይም ደሃ አዛውንት ከሆኑ ለምርቃታቸው ሲሉ ነው የሚያወድሷቸው። እንደዚሁ እያሉ ቀኑን ያገባድዱና ወደማታው ወደ ሜዳ ይወጣሉ። በየቡድናቸው ተሰባስበው በግጥምና በዜማ ሲተቻቹ አምሽተው እንደተነፋፈቁ ቀኑ መሽቶ ጨለማው ይገላግላቸዋል። በዚህ አይነት ሰንብተው በዓሉ በአንዳንድ አካባቢዎች ነሐሴ 21 ቀን ያበቃል። በመስቀል ከሆያ ሆዬ ባዮች ጋር ደግሰው የሰጧቸውን ሰዎች አብልተው አጠጥተው ተጫውተው ፍጻሚው ይሆናል።

በአንዳንድ የልጃገረዶች ጨዋታዎች ውስጥ ወንዶች የሚገኙባቸው አጋጣሚዎችም አሉ። ለምሳሌ በከሴ አጨዳ ጨዋታ ላይ ልጃገረዶች ከሴ ከጣሉ በኋላ ሲጫወቱ ጎረምሶች ያጅቧቸዋል። ወቅቱ የሆያ ሆዬ ነውና ከወንዶች ልጆች የሆያ ሆዬ ጨዋታም አንድ እንጨምር።

**እሆይ ሲራራ**
**እገሌ ሲፈራ**
**ከምድጃው**
**እናቱ ተነሺ**
**ያንን አብሺ**
**እሱ በመፍራቱ**
**ከኛ መለየቱ**

በዚህ እነዚህ ጨዋታዎች ውስጥ የተጠቀምነው የአማርኛ ግጥሞችን ነው። የትግርኛ እና የኽምጣኛ ግጥሞች በብዛት ይገኙበታል። እንዲያውም ሻደይ ማለት በኽምጣኛ ለምለም ማለት ሲሆን ሴቶች የሚታጠቁት ቅጠል መሰሉ ቅጠል ነው። የሻደይ ታሪካዊ አመጣጥም ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ነው መሆኑን የሃይማኖት አባቶችና የአካባቢው ነዋሪ የሆኑ አዛውንቶች ይናገራሉ።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የያዩ አወቀ ትዝታ


**ሰላማዊት ውቤ**

ብርድ ብርድ ይለኝና እራሴን ለመቆጣጠር እስከ ማልችልበት ድረስ አቅም ያሳጣኛል።ድንገት ጉልበቴ ድክም ይልና ሰውነቴ ሁሉ ይዝላል። በነዚህ ምክንያቶች ብዙ ጊዜ በየሆስፒታሎቹ ተመላልሻለሁ። በግሌም መድሃኒቶችን እየገዛሁ እውጥ ነበር። ቢበዛ ለሦስት ቀን ሕመሙ ታገስ ይልልኝና እንደገና ደ ተመልሶ በሽታዬ ያገረሽብኛል። ቢቸግረኝ ለአንዱ የልብ ጓደኛዬ ነገርኩት። ለምን ኤች አይቪ አትመረመርም አለኝ፡፡

በወቅቱ የኤች አይቪ ኤድስ ምርመራ ይሰጥ የነበረው መቅድም ኢትዮጵያ ሄደና የኤች አይቪ ኤድስ ቫይረስ በደሜ ውስጥ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ የሚያስችለኝን ምርመራ አደረኩ።በእርግጥ ለበሽታው ተጋላጭ በመሆኔ ቫይረሱ በደሜ ውስጥ ላይገኝ ይችላል የሚል ዕምነት አልነበረኝም።ሆኖም ያኔ የምርመራ ውጤት ወዲያው አይገለፅም ነበርና ተመርምሬ ወደ ቤቴ ተመለስኩ።ይሄ ወቅት በፍፁም አይዘነጋኝም። ዓመተ ምህረቱ 1998 አካባቢ ሲሆን ወሩ ደግሞ የካቲት የሚባለው መዘዘኛ ወር ነበር።

ይህን ሁሉ ታሪክህን የምትዘረዝረው አንተ ማነህ ለምትሉኝ እያዩ አወቀ እባላለሁ። ዘንድሮ 48ኛ ዓመቴን ጨርሼ 49ንኛውን ለመቆናጠጥ ዳር ዳር እያልኩ ነው። ቫይረሱ በደሜ በመገኘቱ ምክንያት 16 አመታት በሙሉ ፀረ ኤች አይቪ መድሃኒት እየወሰድኩ ኖርያለሁ።ከዚሁ ጎን ለጎንም ሰዎች በቫይረሱ እንዳይያዙ ትምህርት በመስጠት ላይ እገኛለሁ።በሕይወት እስከቆየሁ ድረስም ይሄው ሆኖ ነው የሚቀጥለው።ወጣትነቴን በጭንቀት ነው ያሳለፍኩት። ቢሆንም ብዙ ጓደኞቼ በቫይረሱ ምክንያት የገቡበት ጉድ ጓድ ከመግባት ድኘ ታሪኬን ለእናንተ ለማካፈል ያቆየኝን ፈጣሪዬን ሳላመሰግነው አላልፍም፡፡

ወዳጆቼ ታሪኬ እንዲህ ነው። ተወልጄ ያደኩት በደቡብ ጎንደር ዞን ወረታ ከተማ ውስጥ ሲሆን መጠጥ የለመድኩት ገና በታዳጊነቴ ነው።ልማዴ የትምህርት ጊዜየን አባከኖብኛል።በመጠጡ ምክንያት ለትምህርት የምሰጠው ትኩረት በመቀነሱ በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ዩኒቨርሲቲ መግባት የሚያስችለኝ ነጥብ አላመጣሁም።በዚህ ምክንያት ገና በአፍላ ዕድሜዬ ሥራ አጥ ሆንኩና የወላጆቼ ጡረተኛ ለመሆን ተገደድኩ፡፡



ይሄ ደግሞ በእጅጉ ተስፋ እንድቆርጥ አደረገኝ።በሱሱ የበለጠ እንድገፋበትና ዝሙተኛ እንድሆንም ምክንያት ሆነኝ።ለመኖር ብቻ ሳይሆን ለመጠጣትም መሥራት ነበረብኝና ያገኘሁትን ሥራ እሰራ ነበር።በርካታ የጉልበት ሥራዎችን ስሰራ ቆይቻለሁ።ሁለትና አንድ ዓመት የሚቆዩና የሚያልቁ የፋብሪካ ሥራዎች እየሰራሁ እድሜን ስገፋ ቆይቻለሁ፡፡

1991 ዓ.ም እዚህ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ያሉ ዘመዶቼ ጋር የመጣሁትም ይሄንኑ ሥራ ተማምኜ ነበር።ሥራውን ሰርቼ ብገባም ከዝሙተኛና ከጠጭነት የሚያወጣ የባህርይ ለውጥ አላደረኩም። አዘውትሬ የተለያዩ ሴት አዳሪዎች ጋር መሄድ፤ በጉልበትም ሆነ በሌላ ቦታ ካገኘኋቸው ሴቶች ጋር ወሲብ መፈፀሜን አጠናክሬ ቀጠልኩበት፡፡

ለሰባት ዓመታት በሰራሁበት በአንድ ፋብሪካ ውስጥ በጥበቃ ሥራ መቀጠሬና የወር ደሞዝተኛ መሆኔ ከድርጊቴ እንድቆጠብ ከማድረግ ይልቅ እንድገፋበት ሳያደርገኝ አልቀረም።በኤች አይቪ ቫይረስ ለመያዝ ምልክት የሆነው ሕመም የጀመረኝም እዚህ ፋብሪካ ውስጥ በጥበቃ ሥራ እሰራ በነበረበት ጊዜ እንደሆነ አልዘነጋውም።የተለያዩ ምርመራዎችን አድርጌ መድሃኒት ብወስድም በሽታዬ አልታወቀም።የታወቀው በቅርብ በጓደኛዬ አማካኝነት በቀጥታ የኤች አይቪ/ኤድስ ምርመራ ካደረኩ በኋላ ነው።ይሄ ቀን በፍፁም አልዘነጋውም፡፡

ዕውነታው ምጠብቀውና በውስጤ ያለ ቢሆንም አምኜ ልቀበለው አልቻልኩም። ደጋግሜ በተለያዩ ቦታዎች የኤች አይቪ ኤድስ ምርመራ አደረኩ።ባይገርማችሁ ከሰባት ጊዜ በላይ ደጋግሜ ተመርምሪያለሁ።ግን ሁሉም ጋር ቫይረሱ በደሜ ውስጥ እንዳለ ነው የተነገረኝ።እንደምንም ራሴን አሳመንኩና በመጀመሪያ ቫይረሱ በደሜ ውስጥ መኖሩን ወደ አረጋገጠልኝ መቅድም ኢትዮጵያ ተመልሼ ሄድኩ።ህመሜም ተባብሶ ነበር።

ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ሪፈር ላከኝ።ሆስፒታሉ የተለያዩ ምርመራዎችን አደረገልኝ። በምርመራው የቲቪ በሽታ ተገኘብኝ። ለ20 ተከታታይ ቀናት የቲቪ መድሃኒት ስወስድም ቆየሁ።ከዚህ በኋላም በቀጥታ ፀረ ኤች አይቪ መድሃኒት መውሰድ ጀመርኩ።በበሽታው ሰውነቴ በጣም ተጎሳቁሎና አቅሜ ራሴን መቆጣጠር እስኪሳነኝ ድረስ ተጎድቶ ስለነበር ለሁለት ወራት ያህልም በመቅደም ኢትዮጵያ የሚሰጠውን ወተት እየጠጣሁ እንዲሁም ራሴን የተለያዩ ምግቦችን በመመገብ ሳገግም ቆየሁ።በዚህም ከሞት አፋፍ ላይ ተመልሼ ይሄው ዛሬ ላይ ታሪኬን ለእናንተ ለመንገር በቃሁ።

ክብር ይግባውና ለፈጣሪዬ አሁን ላይ በአንድ የኤች አይቪ ኤድስ ጥምረት ማዕከል ውስጥ በኬዝ ማናጀርነት እየሰራሁ የራሴ ገቢና ወራዊ ደሞዝ ተከፋይ ሆኜ ለመኖር በቅቻለሁ።እንደኔው ቫይረሱ በደሟ ውስጥ ከሚገኝ ሴት ጋርም በትዳር ተጣምሪያለሁ። አንድ ልጅም ለመውለድ በቅተናል። ደስ የሚለው የወለድናት ልጅ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የሚያደርገውን ሕክምና በአግባቡ ተከታትላና መድሃኒት ወስዳ ስለወለደቻት ከቫይረሱ ነፃ ነች፡፡

በመሆኑም ቫይረሱ በደማችን መኖሩ በሕይወታችን ላይ እንቅፋት ሳይሆንብንና ተፅዕኖ ሳያደርግብን እንደማንኛውም ሰው በሰላም እየኖርን እንገኛለን።ቫይረሱ በደማችን በመኖሩም የቀረብን ነገር የለም።ዕድሜ ለፀረ ኤች አይቪ መድሃትና እኛም ቫይረሱ በደሙ ከሌለው የሕብረተሰብ ክፍል እኩል እንኖራለን።እኛ ቫይረሱ በደማችን ውስጥ የሚገኝ ወገኖች ቫይረሱ በደሙ ከሌለበት የሕብረተሰብ ክፍል የምንለይበት አንድ ነገር እንዳለ እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ።እሱም የምንኖረው ለሌሎች ጭምር መሆኑ ነው።እናም አሁን ላይ በዙርያዬ ያሉት ወዳጆቼና ብዙ ሰዎች መድሃኒት ባልተገኘለት በኤች አይቪ ኤድስ ቫይረስ እንዳይያዙ እያደረኩ በመገኘቴ ደስተኛ ነኝ።በመጨረሻም ከጤና በላይ ምንም ነገር የለምና ጤናችሁን ጠብቁ በማለት ሃሳቤን እቋጫለሁ፡፡

# ዓለም አቀፍ



## በአውሮፓ በ500 ዓመታት ውስጥ የከፋ ድርቅ መከሰቱ ተገለጸ

በአውሮፓ በ500 ዓመታት ውስጥ የከፋ የተባለው ድርቅ መከሰቱን የአውሮፓ ህብረት ኤጀንሲ አስታወቋል።ህብረቱ በነሐሴ ወር ባወጣው ሪፖርት÷ በድርቁ ምክንያት በተፈጠረው የአፈር እርጥበት መቀነስ 47 በመቶው የህብረቱ ክፍል የድርቅ አደጋ ስጋት እንደተደቀነበት አመላክቷል። ከዓመቱ መጀመሪያ ጀምሮ በብዙ የአውሮፓ ግዛቶች የተከሰተው ከባድ ድርቅ እስከ ነሐሴ ወር መጀመሪያ ድረስ እየተባባሰ መምጣቱ ነው የተገለጸው፡፡

የሜዲትራኒያን ባህርም እስከ ቀጣዩ ህዳር ወር ድረስ ሞቃታማ እና ደረቅ ሊሆን እንደሚችል በሪፖርቱ ተመላክቷል።በድርቁ ሳቢያ በርካታ ወንዞች እና ሐይቆች የውሃ መጠን መቀነስ እና መድረቅ እንዳጋጠማቸውም ኤጀንሲው አስታውቋል። ይህን ተከትሎም በባህር ትራንስፖርት መስተጓጎል ሲፈጥር÷ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትም በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል ብሏል ኤጀንሲው።

በተጨማሪም በግርብርና ምርቶች በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሰዋልም ነው ያለው። ከዚህ ጋር ተያይዞም በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት የማሽላ ምርት ካለፉት አምስት አመታት አንጻር በ16 በመቶ፣ አኩሪ አተር በ15 በመቶ እንዲሁም የሱፍ ዘይት ምርቶች በ12 በመቶ እንደሚቀንሱ የአጄንሲው ትንበያ ያመላክታል።

ይህ የከፋ የድርቅ አደጋ አንዣቦባቸዋል አገራትም በደራሽ ዝናብ በቀላቀለው አውሎንፋስ ሊመቱ እንደሚችሉ ስጋት ፈጥሯል። በአንዳንድ የአውሮፓ አገራትም የደኖች ቃጠሎ እየተከሰተ ነው።ድርቁ ባስከተለው ተጽእኖ ምክንያትም ኢኮኖሚው ላይ ጫና መፍጠሩ እንዳማይቀር ምሁራን እየገለጹ ይገኛሉ፡፡

በአውሮፓ የተከሰተው ድርቅ በ500 ዓመታት ውስጥ የከፋ መሆኑን መረጃችን በማጣቀስ የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን መግለጹን ሺንዋ እና ሲ ጂ ቲ ኤን ዘግበዋል፡፡

## የዓለም ዋንጫ አዘጋጇ ኳታር ክፍያ የጠየቁ ሠራተኞችን አባረረች



በዓለም ዋንጫ ዝግጅት ላይ የምትገኘው ኳታር ክፍያቸው እንዲፈጸምላቸው የጠየቁ ሠራተኞችን ከአገር አባረረች። ከ60 ያላነሱ ሠራተኞች አደባባይ ወጥተው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው የጠየቁ ሲሆን ከእነዚህ መካከል እስከ የ7 ወራት ደሞዝ ያልተከፈላቸው ይገኙበታል ተብሏል። ከእነዚህ መካከል አብዛኛዎቹ የታሰሩ ሲሆን በውል ቁጥራቸው ያልታወቁ ደግሞ ከአገር ተባረዋል።

የኳታር መንግሥት ከአገር የተባረሩት “የደኅንነት ሕጎችን ስለጣሱ ነው” ብሏል። ኳታር እአአ በ2010 ላይ የ2022 የዓለም ዋንጫ እንድታዘጋጅ ከተመረጠች በኋላ በርካቶች በአገሪቱ የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ያላቸውን ጥያቄ ሲያነሱ ቆይተዋል።

በስታዲየሞች እና በመሠረተ ልማት ግንባታዎች ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች አያያዝም በባሕረ ሰላጤዋ አገር ላይ ጥያቄ ሲያስነሳባት ቆይቷል። ሠራተኞቹ ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ድምጻቸውን ያሰሙት የግንባታ እና ምህንድስና ኩባንያ በሆነው ዘ አል ባንዳረይ ኢንተርናሽል ግሩፕ በተባለ ኩባንያ ዋና ቢሮ ፊት ለፊት ነበር።


ለተቃውሞ አደባባይ ከወጡት መካከል ምን ያህሉ በዓለም ዋንጫ ስታዲየሞች እና መሠረተ ልማቶች ላይ የተሰማሩ ስለመሆናቸው የተባለ ነገር የለም። የኳታር መንግሥት ግን ለቢቢሲ በሰጠው ምላሽ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች የአገር ደኅንነት ሕጎችን በመተላለፋቸው በቁጥጥር ሥር ውለዋል ብሏል።

“ሰላማዊ ያልነበሩ” ሠራተኞች ግን ከአገር እንዲባረሩ መደረጋቸው የተመለከተ ሲሆን ክፍያ እና ጥቅማ ጥቅማቸው ላልተሰጣቸው ሠራተኞች የኳታር መንግሥት ክፍያ እንደሚፈጽም አስታውቋል። ኢኩይደም የተባለ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት እንደሚለው ከሆነ ክፍያ የጠየቁት ሠራተኞች የባንግላዴሽ፣ ሕንድ፣ ኔፓል፣ ግብጽ እና ፊሊፒንስ ዜግነት ያላቸው ናቸው።

የሰብአዊ መብት ተሟጋቹ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ሙስጠፋ ቃድሪ ሠራተኞቹ በሞቃታማ የአየር ጸባይ ተቃውሞ ለማሰማት አደባባይ የሚወጡ ከሆነ ምሽት ላይ ያለ አየር ማቀዝቀዣ እንዲተኙ ሊደረጉ እንደሚችሉ ፖሊስ ነግሯቸዋል ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

“በ42 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ሙቀት አደባባይ ወጥተው ተቃውሞ ሲያሰሙ ምን ያህል አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ ያሳያል” ሲሉ ሙስጠፋ ቃድሪ ተናግረዋል። ከጥቂት ወራት በፊት ቢቢሲ ኳታር በከፍተኛ ሙቀት ምክንያት ሕይወታቸው የሚያልፉ ሠራተኞች ቁጥርን አሳንሳ ሪፖርት እያደረገች ነው የሚል ሪፖርት ይዞ ወጥቶ ነበር።

# ስፖርት



## «ምርጫው ከስፖርቱ ባለፈ ለአገራዊ ምርጫ ምሳሌ እንዲሆን እንፈልጋለን»

**- አቶ ኢሳያስ ጅራ**

ቦጋለ አበበ

የፊታችን ቅዳሜና እሁድ በአዲስ አበባ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (ኢሲኤ) መሰብሰቢያ አዳራሽ ሊካሄድ በታቀደው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ስፖርቱን ለቀጣይ አራት አመታት የሚመሩ ግለሰቦች ለፕሬዚዳንትነትና ለስራ አስፈጻሚነት የሚያደርጉት የምርጫ ፉክክር በጉጉት ይጠበቃል። የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴውም ባለፈው ሳምንት ለፕሬዚዳንትነት የሚፎካከሩ ሶስት የመጨረሻ እጩዎችንና ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት የሚወዳደሩ ሃያ ስድስት እጩዎችን ይፋ ማድረጉ ይታወቃል። በዚህም መሰረት ባለፉት አራት አመታት ፌዴሬሽኑን ሲመሩ የቆዩት አቶ ኢሳያስ ጂራ ከኦሮሚያ ክልል ተወክለው ለፕሬዚዳንትነት የሚፎካከሩ ሲሆን፣ አቶ መላኩ ፈንታ ከአማራ ክልል እንዲሁም ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር አቶ ቶኩቻ አለማየሁ በፕሬዚዳንታዊ ምርጫው እጩ ሆነው መቅረባቸው ይታወሳል። ይህንንም ተከትሎ ለፕሬዚዳንትነት የሚፎካከሩ እጩዎች ምርጫውን ቢያሸንፉ የሚሰሯቸውን ስራዎችና እቅዶቻቸውን ከወዲሁ ማስተዋወቅ ጀምረዋል። በምርጫው ጠንካራ ተፎካካሪ ይሆናሉ ተብለው የሚጠበቁት የአማራ ክልል ተወካዩ አቶ መላኩ ፈንታ ባለፈው ሰኞ በሰጡት መግለጫ ምርጫውን ካሸነፉ ለማከናወን ያቀዱትን እቅዶች ማቅረባቸው ይታወሳል። በትናንትናው እለት ደግሞ ሌላኛው ጠንካራ ተፎካካሪ አቶ ኢሳያስ ጅራ በስካይ ላይት ሆቴል ተመሳሳይ መግለጫ ሰጥተዋል።



**አቶ ኢሳያስ ጅራ በድጋሚ ከተመረጡ የአሰልጣኞች ስልጠናና የአሰለጣጠን ስርዓቱን ለማዘመን እንደሚሰሩ ተናግረዋል፤**

የአገልግሎት ዘመናቸውን አጠናቀው ዳግም ለመመረጥ እየተፎካከሩ የሚገኙት አቶ ኢሳያስ፣ ባለፈው የስራ ዘመናቸው ፌዴሬሽኑን በፕሬዚዳንትነት እየመሩ ያከናወኗቸውን አበይት ተግባራት፣ የስራ ስኬቶች እና ስለነበራቸው የአመራርነት ቆይታ እንዲሁም በቀጣይ አራት ዓመት ቢመረጡ ዋነኛ የስራ የትኩረት አቅጣጫዎችን በተመለከተ በመግለጫቸው ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የኦሮሚያ ክልልን በመወከል የሚወዳደሩት አቶ ኢሳያስ፣ የፕሪሚየር ሊግ ካምፓኒው ምስረታ በእሳቸው የአመራርነት ዘመን እውን መሆኑን በማስታወስ፤ ፌዴሬሽኑም የራሱ ህንፃ እንዲኖረው ማስቻላቸውን አስረድተዋል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን (ዋልያዎቹ) ከስምንት ዓመታት በኋላ ወደ አፍሪካ ዋንጫ መመለሳቸውም በአስተዳደር ዘመናቸው ከተመዘገቡ ስኬቶች መካከል እንደሚጠቀስ አስረድተዋል። አቶ ኢሳያስ አክለውም፤ የተለያዩ የእግር ኳስ ፓይለት ፕሮጀክቶች ጅማሮ፤ የፌዴሬሽኑ ተቀማጭ የባንክ ሂሳብ ማደጉ በስራ ዘመናቸው ካስመዘገቧቸው ስኬቶች መካከል እንደሚጠቀሱ ገልፀዋል።

በአጠቃላይ አቶ ኢሳያስ ባለፉት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ሶስት የአመራርነት ዘመናት በጣም የተሻሉ ስራዎች በእሳቸው የአመራርነት ዘመን መከናወናቸውን በመግለጫቸው አብራርተዋል። እንደ አቶ ኢሳያስ ማብራሪያ የአገሪቱ የሰላም ሁኔታ፤ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በስራ ዘመናቸው ከገጠሟቸው አስቸጋሪ ፈተናዎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

አቶ ኢሳያስ በቀጣይም በድጋሚ ከተመረጡ የአሰልጣኞች ስልጠናና የአሰለጣጠን ስርዓቱን ማዘመን ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩበት ጉዳይ እንደሚሆን ተናግረዋል። የብሄራዊ ቡድን ግንባታም በተመሳሳይ ትኩረት የሚሰጡት ጉዳይ እንደሚሆን የጠቆሙ ሲሆን፤ የስፖንሰሮችን አቅም ማሳደግ የፌዴሬሽኑን አቅም መገንባት፤ ፌዴሬሽኑ ከስፖርት መሃበራት ጋር ያለውን ግንኙነት በተሻለ መልኩ በማጠናከር የሴቶች እና የታዳጊዎች እንዲሁም የከፍተኛ ሊግ ውድድሮች የብሮድካስት የስርጭት ሽፋን እንደሚያገኙ ለማድረግ ማቀዳቸውን አብራርተዋል። በዚህም የተሻለ የፋይናንስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥረት እንደሚያደርጉ ነው የተናገሩት።

በተጨማሪነት አቶ ኢሳያስ ምርጫውን በተመለከተ "ግልፀኝነት እና ታማኝነት ይጎለዋል" በሚል ቀድሞ የሚነዛው አሉባልታ መስተካከል እንደሚኖርበት መልዕክታቸውን አስተላለፈዋል። "በቀጣይ የአራት ዓመት ጉዟችንን ገምግመን ተቋማዊ ለውጥ ላይ እንሰራለን። የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ምርጫ ከስፖርቱ ባለፈ ለአገራዊ ምርጫ ምሳሌ እንዲሆን እንፈልጋለን" ያሉት አቶ ኢሳያስ ስለሁለቱ ተፎካካሪያቸውም አስተያየት ሰጥተዋል። "ሁለቱ ተወዳዳሪዎቹ መልካም ኢትዮጵያውያን ናቸው፣ ይሰሩበት በነበሩበት ኢንደስትሪ ስኬታማ ናቸው። ወደዚህ ስራ መጥተው ውጤት ያመጣሉ ካላችሁኝ ግን ጉባኤተኛው ምላሽ ይስጥበት" ሲሉ ተናግረዋል።

ምርጫውን የሚያስተናግደው ጠቅላላ ጉባኤ ቀደም ሲል ሊካሄድ የታቀደው በጎንደር ከተማ ቢሆንም ከሳምንት በፊት የቦታ ለውጥ ተደርጎበት አዲስ አበባ ላይ እንዲካሄድ መወሰኑን ፌዴሬሽኑ ማሳወቁ ይታወሳል። ይህንን በተመለከተ አቶ ኢሳያስ ማብራሪያ ሲሰጡም "ምርጫውን የማስተዳደር ስልጣን ያለው ፌዴሬሽኑ ነው፣ ከጎንደር ወደዚህ ምርጫው ሲመጣ ምክንያት አለው፣ የጉባኤውን ደህንነት መጠበቅ አለብን" ብለዋል።

በመጨረሻም አቶ ኢሳያስ "በምርጫው ከተሸነፍኩ ወደ እግር ኳስ እንደምመለስ እና እንደማልመለስ የሚያውቀው ፈጣሪ ብቻ ነው" በማለት ተናግረዋል።


## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

**ቁጥር፡- 01/2015**

በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 6 አስተዳደር ጽ/ቤት በ2015 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውሉ አላቂ የጽሕፈት መሣሪያ፤ ልዩ ባህሪ ያላቸው ፣ የጽዳት እቃዎች፣ የሠራተኞች የደንብ ልብስ፣ የህትመት ሥራ አገልግሎት፤ መስተንግዶ አገልግሎት፤ የኤለክትሮኒክስ መገልገያ እቃዎች (ኮፒውተር፤ ፕሪንተር፤ ፎቶኮፒ ማሽን እና ላፕቶፕ ጥገና) አገልግሎት፤ ኤሌትሮኒክስ መለዋወጫ እቃዎች፣ ስፔርፓርት / (ኮምፒውተር፤ የፕሪንተር፤ የፎቶ ኮፒ ላፕቶፕ ማሽን ፣ የመኪና ኪራይ፣ የጉልበት አገልግሎት እና ዲኮር በ1ኛው ዙር ግልፅ ጨረታ አወዳድረን መግዛትና ማሠራት እንፈልጋለን፡፡

**በዚህ መሰረት በጨረታው መሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች፡-**

1. በዘርፉ አግባብነት ያለው የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የከፋይነት መለያ ቁጥር ቲን ነበር፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላቸው፣
2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
3. ተጫራቶች ለጨረታው የተዘጋጀውን ሰነድ በየሎቱ የማይመለስ ብር 100 /አንድ መቶ ብር | በመክፈል የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ፋይናንስ ጽ/ቤት መውሰድ ይችላሉ፡፡
4. በተጨማሪ ተጫራቾች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባዘጋጀው የእቃና አገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ መካተታቸውን መዘገባቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
5. በጨረታው ላይ ያወጣናቸውን እቃዎች በሙሉ ኦርጅናል እና ጥራቱን የጠበቁ ሆነው ማቅረብ የሚችሉ
6. ተጫራቾች የጨረታ ፖስታ በሚያስገቡበት ጊዜ ለተወዳደሩበት እቃ ሳንፕል የሚያቀርቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት መ/ቤቱ ድረስ ማምጣት የሚችሉ፡፡
8. ተጫራቾች በገዙት ሰነድ ብቻ የተወዳደሩበትን ዋጋ ቫት በመጨርና በእያንዳንዱ ገጽ ፊርማና የድርጅቱ ማህተም በማኖር በታሸገ ኤንቨሎፕ ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 /አስር/ ተከታታይ የሥራ ቀናት በተጠቀሰው ቢሮ ለጨረታው በተዘጋጀ ውሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡
9. የጨረታው ማስከበሪያ በእያንዳንዱ ሎት 5000 /አምስት ሺ ብር በባንክ በተረጋገጠ CPO ብቻ ማቅረብ አለባቸው።
10. ተጫራቾች የጨረታ አሸናፊ ሆነው የተገኙባቸው እቃዎች አጠቃላይ ዋጋ 10 % የውል ማስከበሪያ በማስያዝ ከጽ/ቤቱ ጋር የግዢ ውል ስምምነት መፈፀም ይኖርበታል፡፡
11. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን በ11ኛው ቀን የሥራ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ የጨረታው አከፋፈት ላይ ለመገኘት ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በተመሳሳይ ቀን በ11ኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት በወረዳው አስተዳደር አዳራሽ ውስጥ ይከፈታል፡፡
12. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
13. ተጫራቶች ለሳንፕል ናሙና ማቅረቢያ የሚያገለግላቸውን በተጫራቹ ድርጅት ቅጽ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

**በተጨማሪ፡-** ጫማ፣ ሸሚዝ፣ ቱታ በሚቀርብበት ወቅት በተቋሙ ፍላጎት መሆን አለበት፡፡

**አድራሻ፡-** የካቲት 12 ሆስፒታል ጀርባ በሚገኘው ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መንገድ ይዞታ ከኢትዮጵያ አይነ ስውራን ማህበር ፊት ለፊት በሚገኘው በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 አስተዳደር ስልክ ቁጥር፡ 0111262899/0111580697

**በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 06 አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት**

## የጨረታማስታወቂያ

በሱሉልታ ወረዳ ጫንጮ ሆስፒታል ለሆስፒታሉ በ2015 የበጀት ዓት የሚገዙ የዕቃ ዝርዝሮች

1.የሠራተኞች ደንብ ልብስ አቅርቦት፣

2.የሠራተኞች ደንብ ልብስ ስፌት፣

3.የጽህፈት መሣሪያዎች፣

4.የተለያዩ ህትመቶች፣

5.የሕክምና መድኃኒቶች፣

6. የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች፣

7. የጽዳት ዕቃዎች፣

8. የፋይል መደርደሪያ ሼልፍ በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ዕጩ ተጫራቾች ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል

* ተጫራቾች በዘርፉ ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉና ፍቃዳቸውን ያሳደሱ መሆን አለባቸው፡፡
* የጨረታው ሰነድ ዘወትር በሥራ ሰዓት የማይመለስ ብር 100 ( አንድ መቶ ብር) በመክፈል ከጫንጮ ሆስፒታል መግዛት የምትችሉ፡፡
* በሚወዳደሩበት ዕቃዎች ከጨረታ ሰነድ ጋር ናሙና (ሳምፕል) ማቅረብ የሚችሉ፡፡
* ጨረታ ማስከበሪያ የሚመለስ 5000 ብር በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ (C.P.O) ማቅረብ የምትችሉ፡፡
* በተጠየቁበት ዕቃዎች ናሙና (ሳምፕል) ያላቀረበ ተወዳዳሪ ከጨረታው ይሠረዛል፡፡
* ጨረታው የሚከፈተው ይህ ማስታወቂያ በወጣ በ15ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በሱሉልታ ወረዳ በጫንጮ ሆስፒታል ይሆናል ::
* መሥሪያ ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡- በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ጫንጬ ሆስፒታል**

**ስልክ ቁጥር፡- 0118713542/0111880953/0913247067**

**በኦሮሚያ ጤና ጥበቃ ቢሮ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ጫንጬ ሆስፒታል**